# ትግላችን

ኣለም አቀፍ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበራት ህብረት
ወርሃዊ መፅሔት

በአውሮፓ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማህበር የተዘጋጀ

## የዓለም አቀፍ ወዝአደሮች ንቅናቄ

## አጭር ታሪክ

ክፍል 1

የመፅሄት አዘጋጅ ቦርድ፣
P.O.BOX 3198
103 64 STOCKHOLM 3
SWEDEN

ቁጥር 2 ሐምሌ 1971

# የዓለም ወዝአደሮች እንቅስቃሴ ታሪክ ባጭሩ፡፡

የሰው ልጅ ታሪክ በ1840ዓ.ም ገደማ ማርክሲዝምን ወለደ፡፡ ማርክሲዝም ሳይንሳዊ የሆነ የወዝአደር አብዮት ቲዎሪ በመሆኑ ወዝአደሩና የዓለም ጭቁን ሕዝቦች ዓለምን ለማወቅ፣ ለመመርመርና ለመቀየር የሚጠቀሙበት መሣሪያ ነው፡፡ ማርክሲዝም የተፈጥሮንና የሕብረተሰብን አስተዳደግ ሕጋጋትን የሚገልጽ ሳይንስ ነው፡፡ ወዝአደሩንና ጭቁኖችን ወደነፃነት የሚያመራውን የትግላቸውን ጎዳና የሚያሳይና ሶሻሊዝምንና ኮሙኒዝምን እንዴት መመስረት እንደሚችሉ የሚያሳይ መሣሪያ ነው፡፡ ለዚህም ነው ማርክሲዝም ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም ወይም ኮሙኒዝም የሚባለው፡፡

የማርክሲዝም መፈጠር ዓለም አቀፍ የወዝአደር እንቅስቃሴ መኖርን ያመለክታል፡፡ የዓለም ወዝአደሮች ማርክሲዝምን በመጠቀም ወደር በሌለው ትግላቸው በሰው ልጅ ታሪክ ውስጥ አዲስ ምዕራፍ ለመክፈት ችለዋል፡፡

በ1840ዓ.ም የተወለደው የማርክሲዝም አስተሳሰብ ድንገተኛ ዱብ ዕዳ አልነበረም፡፡ የማርክሲዝም መወለድ የሶሻልና የታሪክ መሰረት ያለው ነው፡፡ ይኸውም በአስራ ዘጠነኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ላይ በምዕራብ አውሮፓ በአንዳንዱ አገሮች ውስጥ የካፒታሊዝም ስልተ ምርት ተስፋፍቶ ነበር፡፡ እንግሊዝ አገር ካፒታሊዝም በአረጋጋ ሁኔታ አደገ፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት በእንግሊዝ አገር በ1840 ዓ.ም ተጧልቶ ነበር፡፡ በፈረንሣይም የኢንዱስትሪው አብዮት ወደፊት ገስግሶ ነበር፡፡ በጀርመን አገር ምንም እንኳን የካፒታሊዝም እድገት ከሁለቱ አገሮች ጋር ሲወዳደር ዝቅተኛ ቢሆንም የመሣሪያ ምርቶች በመስፋፋቱ በተለይ የሬይን አካባቢ ትልቅ የኢንዱስትሪ ከተማ ሊሆን ችሏል፡፡ የኢንዱስትሪ አብዮት የወዝአደሩን መደብ በብዛት መፈጠር አስከተለ፡፡ የኢንዱስትሪ ማሽን መፈጠር ወዝአደሩን ሰበሰበ፤ አጠናከረ፡፡ በየጊዜው እየተጠናከረ የመጣው የኢንዱስትሪ መሣሪያ ምርትን ማባዛት ብቻ ሳይሆን ወዝአደሩ በካፒታሊስቶች የበለጠ እንዲበዘበዝና እንዲጨቆን ምክንያት ሆነ፡፡ ይህም ሁኔታ የወዝአደሩን ተቃውሞ አስከተለ፡፡

በ1825ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በእንግሊዝ አገር የኢኮኖሚ ቀውስ ፈነዳ፡፡ የተቀሩትም የአውሮፓ አገሮች ይህን የኢኮኖሚ ቀውስ አንዱ ከአንዱ በበለጠ ሁኔታ ይቀምሱት ጀመር፡፡ የኢኮኖሚው ቀውስ በወዝአደሩ ኑሮ ላይ ትልቅ ጉዳትን አደረሰ፡፡ ይህ ሁኔታ በወዝአደሩና በካፒታሊስቶ መካከል ያለውን ቅራኔ በበለጠ አባባሰው፡፡

ገና ከተወለደበት ቀን አንስቶ ከካፒታሊስት ጋር መታገል የጀመረው የወዝአደሩ መደብ ትግሉ ገበታዊ በመሆኑ መኪናዎችን በመሰበርና ገለበብ ካፒታሊስቶችን በመታገል ላይ ያተኮረ ሆነ፡ ይህ ሁኔታ ተስበተስ በወዝአደሩ ቁጥር መጨመር፣ የንቃትና የድርጅት ከጊዜ ወደ ጊዜ ከፍ ማለት ወዝአደሩ ከካፒታሊስቶች ጋር የሚያደርገውን ትግል በዚያው መጠን መቀየር ጀመር፡፡

ከ1830ዓ.ም እስከ 1840 ድረስ በምዕራብ አውሮፓ ሦስት ትላልቅ የወዝአደር እንቅስቃሴዎች ተካሄዱ፡፡ አንደኛው በፈረንሳይ የሊዮን ወዝአደሮች ሁለት ጊዜ መሣሪያ በካፒታሊስቶች ላይ ያነሱት ሲሆን ሁለተኛው የእንግሊዙ ቻርቲስት እንቅስቃሴና ሦስተኛው ደግሞ የሸሌዝ ሸማኔዎች እንቅስቃሴዎች ነበሩ፡፡ እነዚህ እንቅስቃሴዎች የወዝአደሩ ትግል አዲስ የትግል ደረጃ ላይ መድረሱን የሚያስረዱ በመሆናቸው መላው አውሮፓን አንቀጥቅጠውት ነበር፡፡

በኖቬምበር 1831 ዓ.ም የሊዮን ወዛደሮች መሣሪያ ይዘው ተነሡ፡፡ እነዚህ ወዛደሮች በፋብሪካው ባለቤትና በነጋዴዎች ይበዘበዙ ነበር፡፡ እነዚህ ወዛደሮች በቀን ለ15-18 ሰዓት ሥራቸው ይከፈላቸው የነበረው ለዳቦ መግዣ እንኳን በቂ አልነበረም፡፡ ንብረት የሌላቸው ወዛደሮች ወን ካሬ ናቸው በማለት ካፒታሊስቶቹ ከባድ ሥራ ይሰጧቸው ስለነበር በበሽታ እየተሰቃዩ ብዙዎቹ ይሞቱ ነበር፡፡ ሕፃናት በበሽታ ሲያልቁ ትናንሽ በሳቴናዎች ደገም ገና በልጅነታቸው ሥራ በመስራታቸው አስረኛውን ዓመታቸውን ሳያከብሩ ይሞቱ ነበር፡፡ ኑሮ ያስቆጣቸው ስድስት ሺህ ወዛደሮች በከተበር ላይ የደመወዝ ጭማሪ ጠየቁ፡፡ ከበርቴውን ግን እንዳችም መልስ አልሰጠም፡፡ በኖቬምበር 11 ሥራቸውን አቁመው በሰላማዊ ሰልፍ አደረጉ፡፡ ከበርቴውም በወታደሮች አስደበደባቸው፡፡ ወዛደሮችም በመሣሪያ አፀፋውን መለሱ፡፡ ባንዲራቸውም ላይ "ተርቦ ከመሞት ታግሎ መሞት" የሚለውን መፈክር በመጻፍ ሦስት ቀን ከተዋጉ በኋላ ማዘጋጃ ቤትን ያዙት፡፡ ወዛደሮች በቅንነታቸው ቢሸለሙም አስ ተባበሩ ተርክዘው ስለነበረ ሥልጣን ለመጨበጥ አልታደሉም ነበር፡፡ የመከር ቤትን አጥሮች ከሥልጣናቸው ባያወርዱ መንግሥት ለመቆጣጠር የወዛደር ኮሚቴ ብቻ አቋቋሙ፡፡ ከበርቴውም ይህን እንደ ሁኔታ በመጠቀም ከፓሪስ በአስቸኳይ ወታደሮች አስመጥቶ እንቅስቃሴውን በኃይል ደመሰሰ፡፡

ለሁለተኛ ጊዜ የሊዮን ወዛደሮች በአፕሪል 1834 ዓ.ም የታሰሩት መሪዎቻቸው እንዲፈቱ የመሰብሰብ፣ የመደራጀትና ማሕበር የማቋቋም መብታቸው እንዲታወቅላቸው አመፁ፡፡ ዲሞክራቲክ ሪፐብሊክ ይቋቋም በማለት እንቅስቃሴአቸውን የፖለቲካ ጥያቄ አደረጉት፡፡ ነገር ግን ከበርቴው የታጠቀና የጠነከረ በመሆኑ ይህን እንቅስቃሴ በመሣሪያ ኃይል ለመደምሰስ ቻለ፡፡ ወዛደሩም አስበ መጨረሻው ከጠላት ጋር ታግሎ ወደቀ፡፡

እነዚህ ሁለት የሊዮን ወዛደሮች እንቅስቃሴዎች ወዛደሩና ከበርቴው በሚያደርጉት ትግል ወዛደሩ ለመጀመሪያ ጊዜ ነፃ የሆነ የፖለቲካ እንቅስቃሴ እንዳካሄደ ያሳዩናል፡፡

እንግሊዝ፡- በጁን ወር 1836 ዓ.ም በእንግሊዝ አገር የእጅ ሙያ ሠራተኞችና ወዛደሮች በአንድነት "የለንደን ወዛደር ማሕበር" የሚባለውን አቋቋሙ፡፡ ይህ ማሕበር በፕሮግራሙ ላይ ለሁሉም የመምረጥ መብት እንዲሰጥ ይጠይቅ ነበር፡፡ በሜይ 1838 ዓ.ም ላይ ይህ ፕሮግራም "ሕዝባዊ ቻርቲ" በሚል ስም ለሕዝቡ ተገለጸ፡፡ ከዚያን ወዲህ የመምረጥ መብትን እንደ ዋናው ጥያቄ በማድረግ ወዛደሩ ሌሎች የሕብረተሰቡ ክፍሎች እንዲሳተፉበት አደረገ፡፡ ይህን እንቅስቃሴም የፕሮግራም ሰነድ ላይ እንደወሰዱ የታገሉት ቻርቲስት በመባል ታወቁ፡፡

የቻርቲስት እንቅስቃሴ ሦስት ደረጃዎችን ያለፈ ነበር፡፡ በ1838፣ በ1842 እና በ1848 የተካሄደ ነበር፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ጠቅላላውን አገር በማዳረሱ የነሳስን ወዛደሮች "ዳቦ ወይም አብዮት" በማለት ሲያምፁ፣ የበር ኒንገሃም፣ የማንቼስተር፣ የሊቨርፑልና በተለያዩ አካባቢ የሚገኙ ወዛደሮች በጠነከረ የታጠቀ ሰልፍ ተካሂደውበታል፡፡ በጠቅላላው ከ1830-1840 ገደማ ድረስ አስር ዓመት በሙሉ በተከታታይ በተደረገው የወዛደሮች ተቃውሞ ከእንግሊዝ ሚሊዮን በላይ ወዛደሮች ተካፍለውበታል፡፡ የቻርቲስት መሪዎች ገን ወላዋዮች በመሆናቸው መንግሥት በቀላሉ ሊደመስሳቸው ችሏል፡፡ ይህ እንቅስቃሴ ቀደም በለው ከነበሩት የወዛደር እንቅስቃሴዎች የተለየ ነበር፡፡ ወዛደሩ በእንግሊዝ ፋብሪካዎች ማቋም፣ ገለበብ ካፒታሊስቶች መታገልና በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ብቻ ያተኮረ ሳይሆን ራሱን የቻለ የፖለቲካ ጥያቄዎችን አንስቶ ወዛደሮችን በሙሉ ሰብስቦ ካፒታሊስቶችን መደብ የታገለ በመሆኑ ነው፡፡ ሌኒን ይህንን እንቅስቃሴ "የመጀመሪያው ሰፊ በርግጥም ሰፊውን ሕዝብ ያቀፈ በፖለቲካ የበሰለ የወዛደሩ እንቅስቃሴ ነበር" ብሎታል፡፡

ጀርመን፡- በጀርመን አገርም በ1844 የሸለዚ ሸማኔዎች ከፋብሪካ ባለቤቶች ጋር የታጠቀ ትግል ጀመሩ፡፡ ይህ ከተማ በዚያን ጊዜ በፕሩሲያ ንጉስ አገዛዝ ስር ከሌሎች ከተሞች በጠርዋጠርቅና በጥቃቅ ሥራዎች ወደሬት የተራመደ ነበር፡፡ በዚህ አካባቢ ይገኙ የነበሩ ወዛደሮች በፋብሪካ ባለቤቶችና በነጋዴዎች ብቻ ሳይሆን በባለመሬቶችም ጭምር ይበዘበዙ ነበር፡፡ ባለመሬቶች ወዛደሮችን በሸማኔነት ተረጥ ያስከፍሉት ነበር፡፡ በዚህም የተነሣ ወዛደሩ ድርብ ጭቆና እንደም በባለመሬቶች እንደም በካፒታሊስቶች ይደርስበት ነበር፡፡ ከዚያም በላይ የጀርመኑ ካፒታሊስት ከእንግሊዝ ካፒታሊስቶች ጋር በሚያደርገው ውድድር የወዛደሩን ደመወዝ በመቀነሱ በርካብ ከ36ሺ ወዛደሮች ውስጥ 6ሺህ ለምቶ ቻሉ፡፡

ወዛደሩ በጁን 4 "የደም ፍርድ ቤት" በሚል ተራ "የበው ሥጋ በዪዎች" በማለት ካፒታሊስቶችን ለመቃወት ወደ መኖሪያ ቤታቸው አመሩ፡፡ በተደረገው ትግልም ብዙ ወታደሮችን ማርከው በማስር የካፒታሊስቶችን ቤት በየቀኝራቸው ስር በማድረግ ዶክሜንቶችን አወደሙት፡፡ በተከታታይ ቀናቶም ከሦስት ሺህ በላይ የሚሆኑ ወዛደሮች በመሰብሰብ ፋብሪካዎችንና መዝገቦችን አቃጠሉ፡፡ በጁን 6 የፕሩሲያ ወታደሮች ደርሰው የወዛደሩን እንቅስቃሴ በአመጽ ደመሰሱ፡፡

እነዚህ ሦስት ትላልቅ እንቅስቃሴዎች በአውሮፓ የነበረው የወዛደር ትግል አዲስ ምዕራፍ ላይ መድረሱን ያሳዩናል፡፡ ወዛደሩ የበርጆው ተቀጥያ ሳይሆን ራሱን የቻለ ነፃ የሆነ የፖለቲካ ኃይል በመሆን የፖለቲካ ትግል መድረክ ላይ መውጣቱን ያሳያሉ፡፡ በነታቸው በኩል የኑሮ ሁኔታውን ብቻ ለማሻሻል የሚታገል ሳይሆን የፖለቲካ ሥልጣን ለመጨበጥም ትግል እንደሚያደርግ እንገነዘባለን፡፡ የትግል ስልቱን ስንመለከት የፋብሪካ ዕቃዎችን ከመሰባበርና ገለ በበ ካፒታሊስቶችን ከመታገል አልፎ ወደ ሕዝባዊ እንቅስቃሴና የመሣሪያ ትግል እንደተሸጋገረ እንረዳለን፡፡ በድርጅት አነጋገር ደግሞ ወዛደሩ ራሱን በማደራጀት የመጀመሪያውን የወዛደር የፖለቲካ ድርጅት መመስረቱን እናያለን፡፡

በሌላ በኩል እነዚህ ትላልቅ ሦስት የወዛደር እንቅስቃሴዎች በአጭሩ መደምሰሳቸው የሚያሳየው ወዛደሩ ለትግሉና ለአብዮቱ መሪ የሆነውን በቲዎሪ የታጠቀ አብዮታዊ ፓርቲ እንደሚያስፈልገው ነው፡፡ አብዮታዊ ቲዎሪና ፓርቲ አስፈላጊ እንደሆኑ እንገነዘባለን፡፡

በጊዜው የነበረው የነውጥ ከበርቴው ቡርዧዚም ቲዎሪ ግለ ኑሮ ቀንነታዊ ቡርዧዚም ወዛደሩን ለነፃነት በሚያደርገው ትግል ለመራውና ሊያሳየው አልቻለም፡፡ አይችልምም፡፡ እንዲያውም በተቃራኒው ለጠላት እጋፍጦ ይሰጠው ነበር፡፡ በዚህ ሁኔታ ወዛደሩ ፀረ-ከበርቴ ትግሉን ከግቡ ለማድረስ የሳይንሳዊ ኮሙኒዝም ማደግና ከወዛደሩ እንቅስቃሴ ጋር መዋሃድ አስፈላጊነቱ ገልጽ እየሆነ መጣ፡

በ1840 ገደማ በአውሮፓ የካፒታሊዝም ማደግ ለሳይንስ፣ ለባሕል፣ ለፍልስፍና፣ ለተፈጥሮ ሳይንስ፣ ለታሪክና ለኢኮኖሚ ቃርሞሮች አዲስ መሠረት እየሰፋ ሄዶ አመቺ ሁኔታን ፈጠረ፡፡

በተፈጥሮ ሳይንስ የጋይል ማከማቻትና መቀየር፣ የሕዋት መገኘት፣ የዳርዊን ኢቮሉሽን ቲዎሪ ...ወዘተ በምርምር ተገኙ፡፡ ለሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መፈጠር የማቴሪያሊዝና የሶሻል ሁኔታው አመቺ ነበር፡፡ ማርክሲዝም በዚህ የሶሻልና የታሪካዊ ሁኔታ መሠረት ተፈጠረ፡፡

ሳይንሳዊ ሶሻሊዝም በአንዱ በተወሰነ የሕብረተሰብ እድገት ታሪክ የሚፈጠር ነው፡፡ ማርክስና ኢንገልስ በመጀመሪያ ትግል ውስጥ በተግባር በመሳተፋቸው፣ ሳይንሳዊ ምርምር በማድረጋቸውና በአብዮታዊ ተግባር አካባቢያቸውን ለመቀየር በመታገላቸው ከአይዲያሊስት ወደ ማቴሪያሊስት፣ ከአብዮታዊ ዴሞክራት ወደ ኮሙኒስት በመቀየራቸው የሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን መሠረት ለመጣል ቻሉ፡፡

ማርክስ፡- /1818-1883/ በሜይ 5/1818 ቲየር በሚባል ከተማ በጀርመን አገር ከሃብታም ቤተሰብ ተወለደ፡፡ አባቱ ጠበቃ ነበር፡፡ ማርክስ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በ1835 እንደጨረሰ አንዱ ዓመት በቦን ዩኒቨርሲቲ በኋላም ወደ በርሊን በመሄድ በበርሊን ዩኒቨርሲቲ የህግ ትምህርት፣ ታሪክና ፍልስፍና ተከታተለ፡፡ በርሊን ዩኒቨርሲቲ ቀደም ሲል ሄገል በሕይወት በነበረበት ጊዜ ያስተምርበት ስለነበረ የሄገል ፍልስፍና በጣም ተስፋፍቶ ነበረ፡፡ ማርክስም የሄገልን ሥራዎች ማጥናት ጀመረ፡፡ ከጥቂት ጊዜ በኋላም ወጣት ሄገሊያን ከሚባሉት የግራ ክንፍ ቡድኖች ጋር ተደባለቀ፡፡ይህ ቡድን በዚያን ጊዜ ከነበረው የፖለቲካ እንፃር ሲታይ ተራማጅ ቡድን ስለነበረ የፊውዳሊዝምን ፊሳጭ ተራማጅነትንና አበርዮት የተያያዘውን ቤተክህነት የሚቃወሙ ሃሳቦች ያቀርብ ነበር፡፡ ማርክስ ከሄገል ሥራዎች ውስጥ ቀናና /ዲንግ/ ያልሆነውን አብዮታዊ ጉኑን ብቻ በመውሰድ ለቡርዧ ዴሞክራሲ መታገል ጀመረ፡፡

ወጣቱ ማርክስ በፋህ አስተሳሰብ የነበረው አርጌውን ዓለም የሚቃወም ነበር፡፡ በ1842 ማርክስ የራይን ጋዜጣ ተባባሪ አዘጋጅ ሆኖ ከሠራ በኋላ በዚሁ ዓመት በኦክቶበር ላይ ዋና አዘጋጅ ሆነ፡፡ ማርክስ በዚህ በጋዜጠኝነት ሥራው የፕሩሲያን ፊሳጭ ፊውዳል መንግሥት ለማጋለጥ ቢችል በሌላ በኩል ደግሞ የሕዝቡን ኑሮና የሕብረተሰቡን ሁኔታ በበለጠ ለመረዳት በቃ፡፡ የመሬት ከበርቴዎች ካፒታሊዝም እያደገ በመምጣቱ ገበሬውን ማባረር ጀመሩ፡፡ከመሬት ተነቅለው ወደ ተራራማ አካባቢ የተበደደው ገበሬ እንጨት ቆርጦ እንዳይጠቀም፣ ዓሣ ጠምዶና አደን እንዳይመገብ መንግሥት "በህጋዊ" መንገድ ጫካዎችንና ወንዞችን በቀጥታ ስር የሚያደርጉ ሕጎችን በምክር ቤት ውስጥ አጸደቀ፡፡ እንጨት ቆርጦ መጠቀም "ስርቆት" እንደሆነ የሚገልጽ ህግ ወጣ፡፡ ማርክስ ከወዝአደሩና ከገበሬው ጎን በመቆም በጋዜጣው ላይ ይህን ህግ የሚቃወም ጽሑፍ አወጣ፡፡ መንግሥት በማርክስ ጽሑፍ ላይ ሳንሱር ማድረግ ጀመረ፡፡ ሁለተኛም እንደዚህ ዓይነት ጽሑፍ እንዳይጽፍ ተገበፀ፡፡

ማርክስ በ1843 የጋዜጣ ዋና አዘጋጅነቱን በመተው በመንግሥትና በመብት መሃከል ስላለው ግንኙነት የሚያወራው የሄገል አይዲያል ፍልስፍና በተግባር አንፃሩ አድሃሪ አስተሳሰብ በመሆኑ ይህንን አስተሳሰብ መተቸት ጀመረ፡፡ ለዚሁም ትችቱ ይረዳው ዘንድ የሄገልን ፍልስፍና የሚቃወሙትን የፊዩርባክን ሥራዎች እንደ "የክርስትና ሃይማኖት ውስጣዊ ይዘት" የሚባሉትን ጽሑፎች ማጥናት ጀመረ፡፡ ለአጭር ጊዜ ኢንገልስ እንዳለው ሁላችንም ማርክስና ኢንገልስ የፊዩርባክ ተከታዮች ነበሩ፡፡ ማርክስ በትግል ተግባር ውስጥ በመሳተፉና በሕዝቡ ትግል ጎራ የሰሯ አለ



የሚ ግንኙነትና የፖለቲካ ሕይወቱ ቀና እንዲያደርግ ሁኔታው አስገደደው፡፡

በ1843 ወደ ፓሪስ በመሄድ በዚያን ጊዜ ከፍተኛ የትግል ደረጃ ላይ ደርሶ በነበረው የወዝአደር እንቅስቃሴ ውስጥ ይሳተፍ፡፡ የሚኖርበትም አካባቢ የወዝአደር አካባቢ በመሆኑ የወዝአደሩ ኑሮ ኑሮው ሆነ፡፡ በዚያን ጊዜም በወቅቱ ይሰራ ከነበሩት የጀርመንና የፈረንሣይ ወዝአደሮች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት በማድረግና ስብሰባቸውም በመሳተፍ ትምህርት ይሰጣቸው ጀመር፡፡ ከነዚሁም ወዝአደሮች ፍላጎታቸውን፣ ትግላቸውንና ኑሮአቸውን በበለጠ ለመማር ቻለ፡፡

ማርክስ በፓሪስ የፈረንሣይን የቡርዧ አብዮት ታሪክ በማጥናት ሳይንሳዊ ምርምርን ማድረግ ጀመረ፡፡ የእንግሊዝን ቡርዧ ኢኮኖሚስቶች የአዳም ስሚዝንና የዳቪድ ሪካርዶን ሥራዎችም መከታተል ጀመረ፡፡ በተጨማሪም የፈረንሣይን ማቴሪያሊስት ፍልስፍናና የተለያዩ የሶሻሊስቶችን ትምህርት ማጥናት ጀመረ፡፡

በ1844 "በጀርመን-ፈረንሣይ ዓመታዊ" መጽሔት ውስጥ "የሄገል የነፃነት ፍልስፍና ትችት" በሚል ጽሑፍ ለመጀመሪያ ጊዜ ወዝአደሩ የሕብረተሰቡ እንቅስቃሴ ኃይልና የአብዮት መሪ መሆኑን ገለጸ፡፡ ማርክስ ማቴሪያሊስት እንደሆነ አሳያን፡፡ ሌኒን ይህንን የማርክስን ሥራ ተመልክቶ ማርክስ ፈረንሣይ አገር ውስጥ አብዮተኛ መሆን እንደጀመረ ይገልጻል፡፡

እንገልስ፡- /1820-1895/ በኖቬምበር 28/1820 በጀርመን ከተማ ከትልቅ ከበርቴ ቤተሰብ ተወለደ፡፡ በ1838 የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቱን በማጠናቀቅ በአባቱ ፋብሪካ ውስጥ በብሬመን ከተማ ተቀጥሮ ሥራውን ጀመረ፡፡ ቀንም እንኳን ሥራው በዛውን ጊዜ ቢወስድበትም ለመጀብ ትግልና ለሳይንሳዊ ምርምር ያለውን ፍላጎት አልቀነሰበትም ነበር፡፡

እንገልስ በዚህ በኢንዱስትሪ ከተማ የወዝአደሩ መደብ እንዴት እንደሚበዘበዝ በዓይኑ ለመመልከት ቻለ፡፡ በአስራ ዘጠኝ ዓመቱ "የቬበርታል" ደብዳቤ በሚለው ጽሑፍ ላይ በበዝበዛ ላይ የተመሠረተውን ሕብረተሰብ አጋለጠ፡፡

ዘመነኛውን የጀርመን አብዮት ዓመት ቀከንያት በማድረግ በጻፈው ግጥም ላይ "የአብዮት እንቅስቃሴ ነፋስ የንጉሡን ዘፋን ለመገልበጥ እየመከረ ነው" የሚሉ ሃሳቦች አሰፍሮ ነበር፡፡ በንጉሡ ላይ ባለው ተሳትፎ የፕሩሲያው ንጉሥ ጨቋኝ ሠሰተኛው የጋው ቀት እንደሆነ በመግለጽ ይጽፍ ነበር፡፡ እንገልስ በዚህ ጽሑፍ አብዮታዊ ዴሞክራት እንደነበረ ለመገመት አያዳግትም፡፡

እንገልስ በ1841 የወታደር ግዳጁን ለማሟላት ወደ በርሊን ሄደ፡፡ በርሊን በነበረበት ጊዜም ተመልካች የዩኒቨርሲቲ ተማሪ በመሆን ትምህርቱን መከታተል ጀመረ፡፡ በወጣት ሄገሊያን ቡድንም ውስጥ መሳተፍ ጀመረ፡፡ በዩኒቨርሲቲው ውስጥ በወጣት ሄገሊያን መካከል ትልቅ የፍልስፍና ክርክሮች ይካሄዱ ነበር፡፡ እንገልስ የፊዩርባህን አስተሳሰብ ማቴሪያሊዝምን መከታተል ጀመረ፡፡ የፕሩሲያውንም ፊሳጭ ፊውዳል መንግሥት ማጋለጥ ቀጠለ፡፡

በበርሊን የውትድርና ግዳጁን እንደጨረሰ በአባቱ ፋብሪካ ውስጥ ለመስራት ወደ ማንቸስተር ሄደ፡፡ ይህ ከተማም የጨርቃ ጨርቅ ኢንዱስትሪ መናኸሪያ ብቻ ሳይሆን የቻርቲስት እንቅስቃሴም የመነ ከረበት ከተማ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ ለእንገልስ ከወዝአደሩ ጋር አብሮ ለመኖር፣ ለመታገልና የትግል ጓደኛቸው ለመሆን አመቺ ሆነለት፡፡

እንገልስ የካፒታሊስቶችን ሕብረተሰብ ቀፊነና የወዝአደሩን ዕድገት በማጥናት ኮሙኒስት ለመሆን ቻለ፡፡ በወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ የተለያዩ የእንግሊዝ ከተማዎችን በመጎ

በኋት የበሻል ቀርቀሮችን አደረገ፡፡ በቻርቲስ አንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ ከግራ ክንፍ ጋር ግንኙነት በማድረግ የ"ከዋን ክበብ" በሚባለው ጋዜጣ ላይ የቻርቲስን እንቅስቃሴ የሚደግፍ ጽሑፍ ይጽፍ ነበር፡፡

በ1844 በጻፈው "የናሽናል ኢኮኖሚ ትችት" በሚለው ጽሑፍ የታሪካዊ ማቴሪያሊዝምን ትንተና በማድረግ የመደቦችን ቅራኔ መኖር፣ የግል ሃብት ለፖለቲካና ለኢኮኖሚ ቀውስ መነሻ እንደሆነ፣የወዝአደሩ ሚና በኅብረተሰብ ውስጥ ምን እንደሆነ፣...ወዘተ የሚሉትን አብራርቶ ገለጸ፡፡

የኤንግልስን እንደ ማርክስ ከአይዲያሊስት ወደ ማቴሪያሊስት፣ ከሬዲካል ዴሞክራት ወደ ኮሙኒስት መቀየሩን ይህ ጽሑፍ ይገልጽልናል፡፡ ሌኒን ኤንግልስ ለመጀመሪያ ጊዜ ሶሻሊስት የሆ ነው እንግሊዝ አገር ነው ያለውም ለዚሁ ነው፡፡

በ1844 ኤንግልስ ከማንቸስተር ወደ ጀርመን በመመለስ ላይ ማርክስን ፓሪስ ላይ በመገናኘት አስር ቀን ሙሉ ሃሳብ ይለዋወጣሉ፡፡ ከዚያን ቀን ጀምሮ ሁለቱ የዓለም ወዝአደር መሪዎች አብዮታዊ ጓደኝነታቸውን መሰርተው ዕድሜ ልካቸውን ወዝአደሩን ነፃ ለማውጣት ለመታገል ቃል ይገባሉ፡፡ ይህንንም በተግባር አስመስክረዋል፡፡

ማርክስና ኤንግልስ ከተገናኙበት 1844–1848 ድረስ በአንድ በኩል በወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ በመሳተፍ ለወዝአደሩ እንቅስቃሴ ትጁ የሆነውን የተሟላ አይዲዮሎጂ በመታገል ለወዝአደር ፓርቲ መመስረት ሲታገሉ፣ በሌላ በኩል ደግሞ የወዝአደሩን ልምዶች/ኤክስፒሪያንስ/ በመከታተልና በማጥናት የሳይንሳዊ ቲዎሪ መርሆዎችን ይቀምሳሉ፡፡ ማርክስና ኤንግልስ ከሰው ልጅ የማሰብ ታሪክ ውስጥ ትልቁን ግን በመተው ተራውን ግን በመውሰድ ወደ አብዮታዊነት በመቀየር አበረከቱ፡፡

እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት የማርክሲዝም ቲዎሪ ምንጮች ናቸው፡፡ የማርክሲዝም ምን ክፍሎች ደግሞ ሦስት ናቸው፡፡ እነርሱም የማርክሲዝም ፍልስፍና ማለትም ዲያሌክቲካዊና ታሪካዊ ቁስ አካልነት፣ የማርክሲዝም ፖለቲካዊ ኢኮኖሚና ሳይንሳዊ ኮሙኒዝም ናቸው፡፡
ወደ ማርክሲዝም የቲዎሪ ምንጮች እንመለስ፡-

<u>የጀርመን ክላሲካል ፍልስፍና</u>፡- ይህ ፍልስፍና የሚጀምረው በካንት ነው፡፡ ሆኖም የዚህ ፍልስፍና ዋና ተወካዮች የነበሩት ከ1770–1831 ድረስ የኖረው ሄገልና ከ1804–1872 ድረስ የኖረው ፌየርባክ ናቸው፡፡ የጀርመን ክላሲካል ፍልስፍና ስንልም የሄገልን ዲያሌክቲክስና የፌየርባክን ማቴሪያሊያሊዝም ማለታችን ነው፡፡

ሄገል /ዲያሌክቲክስ/ ዓለም የሚንቀሳቀስ፣ የሚያድግና የሚለወጥ ነው ይላል፡፡ ማንኛውም ነገር በማያቋርጥ እንቅስቃሴ ላይ እንደሚገኝና ቅራኔ የነገሮች ዕድገት መሠረት እንደሆነ ይገልፃል፡፡ ሄገል ዓለምን እንደ ዘለዓለማዊ መንፈስ ይገዛታል ወይም ያዛታል ይላል፡፡ ሄገል በአይዲያሊስት አስተሳሰብ በመወሰኑ በዲያሌክቲክሱ እስከ መጨረሻው አልገፋበትም፡፡

ፌየርባክ የሄገልን አይዲያሊስት አስተሳሰብ በመተቸት ማቴሪያሊዝምን ይመሠርታል፡፡ ዓለም ማቴርያል እንደሆነና ማተር መንፈስን እንደሚወስንና መንፈስ ግን ማተርን እንደማይወስን ይገልፃል፡፡ሆኖም እንጂ ፌየርባክ ሄገልን ቢተቸውም የፌየርባክ ማቴርያሊዝም ሕብረተሰቡን በሚያስረዳበት ጊዜ ሜካኒካዊ፣ ሜታፊዚካዊ የሚያወላውል ነበር፡፡



ማርክስና ኤንግልስ ከሄገል ዲያሌክቲክስና ከፌየርባክ ማቴሪያሊዝም ተራውን ግን በመውሰዱ ላይ ትችት ከአቀረቡ በኋላ ወደ አብዮታዊነት በመቀየር ዲያሌክቲካዊንና ታሪካዊ ማቴሪያሊዝምን መሰረቱ፡፡

<u>የእንግሊዙ ፖለቲካል ኢኮኖሚ</u>፡- የክላሲካል እንግሊዝ ኢኮኖሚ ተወካዮች አደም ስሚዝና ዴቪድ ሪካርዶ ነበሩ፡፡ እነዚህ ኢኮኖሚስቶች ለመጀመሪያ ጊዜ የእቃውን ዋጋ የሥራው ብዛት እንደሚወስን ቢያስረዱም ይህ ዋጋ የወዝአደሩና የካፒታሊስት አገልግሎት ውጤት ነው በማለት በዘበዛን የሚሸፍን ቲዎሪ አፈለቁ፡፡ ማርክስና ኤንግልስ ከነዚህ የሥራ ዋጋ ቲዎሪን በመውሰድና የተቀረውን አስተሳሰብ በመተቸት ሳይንሳዊ በሆነ መንገድ ወዝአደሩ ከካፒታሊስቱ የሚያገኘው ደመወዝ ቀርሱ ወዝአደሩ ለካፒታሊስቱ የሰራለት የሥራ ዋጋ በቀሰም በእውነተኛ ይዘቱ ከሚቀርበው ዋጋ ትንሹ ክፍል እንደሆነ ገለጹ፡፡ የተቀረው ወዝአደሩ ለሰራው ስራ ማግኘት የሚገባው ዋጋ ግን ካፒታሊስቱ ኪስ የሚገባው የትርፍ ትርፍ መሆኑን ገለጹ፡፡ የማርክስ የትርፍ ትርፍ ቲዎሪ ሚስጥር የነበረውን የካፒታሊስት በዝበዛ ገልጦ በማውጣት አጋለጠው፡፡

<u>ምኞታዊ ሶሻሊዝም</u>፡- የዚህ ፍልስፍና ተወካዮች የፈረንሳዮቹ ሴንት ሲሞን፣ ፉሪየርና የእንግሊዙ ኦወን ናቸው፡፡እነዚህ ፈላስፋዎች በ19ነኛው ክፍለ ዘመን መጀመሪያ ላይ የካፒታሊዝምን በዘበዛ፣ ግፍና ጭካኔ የተመለከቱ ነበሩ፡፡ "ሕንገሥት በምድር ለሃብታሞች ገነት ለደሆች" ይህ የሰው ልጅ የሚኖርበት ዓለም የተገላቢጦሽ መሆኑን አዩ፡፡ እነዚህ ሰዎች ምንም አንኳን የሰው ልጅ እኩልነት የሚረጋገጥበት የምኞት ሕብረተሰብ ለመመስረት የሚያስቡ ቢሆንም አንዳንድ ትክክለኛ አስተሳሰብ ያዘሉ ፍልስፍናዎች ነበሯቸው፡፡ አንዳንዶቹን ለምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፡- ማንኛውም ሰው የጉልበት ሥራ መስራት አለበት፣ የከተማና የገጠር ልዩነት መቅረት አለበት፣ ...ወዘተ ይሉ ነበር፡፡ ይህ አቋማቸው ትክክለኛ ነው፡፡ እነዚህ ፈላስፋዎች በዘበዛ የሌለበትን ሕብረተሰብ ይመኙ እንጂ የካፒታሊዝም ሕብረተሰብን ያስተዳደሩ ሕጎችን፣ እንደ የወዝአደሩን ታሪካዊ ተልእኮ፣ እንደ የመደብ ትግልን፣ እንደ አብዮታዊ አመጽና የመሳሰሉትን የማይቀበሉና እንዲያውም በጠቅላላው የሚቃወሙ ነበሩ፡፡ የገዢ መደብ ሙሉ ፍላጎት፣ በአጠቃላይ ካፒታሊስቱና ባላባቱ ከሕዝቡ ጋር ቢተባበሩ በዘበዛ የሌለበትን ሕብረተሰብ ለመመስረት እንችላለን በለው ያምኑ ነበር፡፡

ማርክስና ኤንግልስ ታሪካዊ ማቴሪያሊዝምን፣ ዲያሌክቲካል ማቴሪያሊዝምንና የትርፍ ትርፍ ቲዎሪን የደረሰ በሰው በማወቃቸው ይህን ምኞታዊ ሶሻሊዝም በጊዜው ለመጀመሪያ አመጽ ሁኔታ ፈጠረላቸው፡፡ ማርክስና ኤንግልስ የካፒታሊስት ሕብረተሰብ ሕጎችን በመፈለግ ወዝአደሩ የከበርቴው መቃብር ቆፋሪ እንደሆነ፣ የመደብ ትግል የሕብረተሰብን እድገት እንቅስቃሴ ሞተር እንደሆነና ሶሻሊዝምና ኮሙኒዝም በአብዮታዊ አመጽ ቡርዥውን በመደምሰስ የሚመሰረት ሕብረተሰብ እንደሆነ በመግለጽ ምኞታዊ ሶሻሊዝምን በመታገል ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን መሰረቱ፡፡

ማርክስና ኤንግልስ የሳይንሳዊ ኮሙኒዝምን ቲዎሪ ለማስፋፋት የከበርቴውንና የገጠሩ ከበርቴውን አይዲዮሎጂ የግድ መዋጋት ነበረባቸው፡፡ በአርግጥም ተዋግተዋል፡፡ አንዳንዶቹን ለመጥቀስ፡-

ማርክስና ኤንግልስ የቶትሊንን ምኞታዊ ሶሻሊዝምን፣ የጀርመኑን "እውነተኛ ሶሻሊዝም"

እና የፕሩደንን አስተሳሰብ በመቃወት የወዛደሩን አንቀሳቃሽ ከአድርባይነት ለማጽዳት ብዙ ትግሎችን አካሂደዋል።

<u>የዌትሊንግ ምኞታዊ ሶሻሊዝም</u>፡— ይህ ሰው ከ1808 —1871 ድረስ የኖረ ነው። በ1836 "የሃቀኞች ማሕበር" የሚባለው ድርጅት አባልና መሪ የነበረ ሰው ነው። የካፒታሊስት ሕብረተሰብን በጣም የሚጸየፍና የዚህን ሕብረተሰብ በአመጽ መደምሰስ አጥብቆ የሚፈልግ ነበር። ሆኖም ግን የካፒታሊዝም ሕብረተሰብ ሕጋጋትን ባለማወቅ የኮሙኒስት ሕብረተሰብን ለመመስረት የሚቻለው በወዛአደሩ አብዮታዊ አመጽ ሳይሆን በለማኞች፣ በነፍስ ገዳዮች፣ በዱርዬዎችና በተወቀሱ ሰዎች በቻነው የሚል እምነት ነበረው። አብዮት ገብታዊ ነው ከሚለው የግል አስተሳሰቡ በመነሳት የመደብ መደራጀትንና የወዛአደር ፓርቲ መኖርን አጥብቆ ይቃወም ነበር። ማርክስና ኤንግልስ ይህን የወዛአደሩን መደብ አንቀሳቃሽ የሚጎዳ አስተሳሰብ አጥብቀው ታገሉ። ዌትሊንግ ማርክስና ኤንግልስ አጥብቀው ስለታገሉት ከትግሉ ሜዳ ተሸንፎ ወደ አሜሪካ አገር ተሰደደ። በዚህም ሁኔታ ከመደብ ትግሉ እራሱን አገለለ።

<u>የጀርመኑ "እውነተኛ ሶሻሊዝም"</u> ፡— ማርክስና ኤንግልስ ዌትሊንግን እንደ ተዋጉት ሁሉ እነዚህንም የንዑስ ከበርቴ አብዮተኞች መቃወት ተገደዱ። የዚህ የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም አራማጆች ሄስ፣ ክሪግና ግሩን የሚባሉ ሰዎች ነበሩ። የእነዚህ ሰዎች ዋና አስተሳሰብ የመደቦች ትግልንና አብዮታዊ አመጽን በመካድ "ወንድማማችነት"፣ "ሰብአዊነት" እና "ዘለዓለማዊ እኩልነት" በሚሉት — አስተሳሰብ ላይ የተመሰረተ ነበር። የወዛአደሩ የመደብ ጠላት የሆነውን ከበርቴ "ወዳጅ" በሚለው ቃል ተኩት።

ማርክስና ኤንግልስ ይህን አደገኛ አስተሳሰብ አጋለጡ። በተለይ "ዝቀሬ ደብዳቤ በክሬገ ላይ" በሚለው ጽሑፋቸው ካፒታሊስት "ወዳጅ" ነው የሚለውን የቅኝ ፈሊጥ ደበደቡ። ክሬገም በዚህ ጽሑፍ በመጋለጡ ከፖለቲካ መድረክ ላይ ወረደ። እራሱን ደበቀ። ኤንግልስም ግሩን የሚባለውን "የእውነተኛ ሶሻሊዝም" መሪ ፓሪስ ላይ ሦስት ቀን ሙሉ ባደረገው ክርክር አርያውን አስተፋው። ኤንግልስ የኮሙኒዝምን መሰረታዊ ፕሪንሲፕሎች ክክለኛ ትርጉም በመስጠት "በእውነተኛ ሶሻሊዝም" ላይ ድል ተገኘ።

<u>ፕሩደን</u>፡— /1809–1865/ ይህ ሰው ከአንድ ደሃ የገበሬ ቤት የተወለደ ነው። ወጣቱ አታሚነት ስለነበረ ማተሚያ ቤት ከፍቶ ይተዳደር ነበር። "የግል ሃብት ምንድነው?" በሚል መጽሐፉ ላይ "የግል ሃብት ሌብነት ነው" በሚለው አስተሳሰቡ ቀረ ስሙን አትርፎ ነበር። በ1846 ላይ በጻፈው "የችግር ፍልስፍና" በሚል መጽሐፉ ላይ የአድርባይነት አቋሙን ማስፋፋት ጀመረ። ፕሩደን በጽሑፉ ላይ ትናንሽ ካፒታሊስቶችን ቢቃጋ የአነስተኛ የግል ሃብት ዘለዓለማዊ በመሆኑ ለማቆረት አይቻልም በማለት በዘበዛ ለሌለበት የካፒታሊስት ሕብረተሰብ መታገል ያስፈልጋል አለ። በአጠቃላይ ፕሩደን መንግሥትና ኃይል አስፈላጊ እንዳልሆኑ ለማሳየት ባደረገው ሙከራ የአናርኪስቶችን አስተሳሰብ በማስፋፋት "ፓርቲና መንግሥት ይውደሙ" ለነሰቦች በሙሉ "ነፃነት" በማለት ጮኸ።

ማርክስ በ1847 ለዚህ ፕሩደን ጽሑፍ መልስ "የፍልስፍና ችግር" በሚለው ጽሑፉ የፕሩደንን የፖለቲካ፣ የፍልስፍናና የኤኮኖሚ አመለካከት አጋለጠ። የዚህን ሰው አድርባይነት



አሳየ።

ማርክስና ኤንግልስ ሳይንሳዊ ሶሻሊዝምን በወዛአደሩ ውስጥ ለማስፋፋት አድርባዮችን እያታገሉ የወዛአደሩን ፓርቲ ለመፍጠር ከወዛ አደሩ ጋር ተዋሃዱ። በቤልጅግ አገር በብራሰል ከተማ ውስጥ ከተለያዩ አገር ወዛአደሮችና ሶሻሊስቶች ጋር ግንኙነት ለመመስረት "የኮሙኒስት ወኪሎች ኮሚቴ" የሚባለውን ድርጅት በ1846 አቋቋሙ።

በ1836 በፈረንሳይና ጀርመን ወዛደሮች በጋራ የተቋቋመው "የሃቀኞች ማሕበር" የተባለውን ድርጅት ማርክስና ኤንግልስ በውስጡ የሚገኙትን አድርባዮች በማጋለጥ በ1847 በውስጡ ገብተው በሳይንሳዊ ሶሻሊዝም የሚመራ የወዛአደሩ አብዮታዊ ድርጅት አደረጉት።

በ1847 ለመጀመሪያ ጊዜ በለንደን ከተማ በተደረገው የዴሌጌቶች ጉባኤ ላይ ኤንግልስ የድርጅቱን ሕግ ነደፈ። በዚህ ሕግ የመጀመሪያው አንቀጽ ላይ "የዚህ ድርጅት ዓላማ ቡርዧውን በመጣል የወዛአደሩን አምባገነንነት ለመመስረት፣ የአረጀውንና በመደቦች የተከፋፈለውን ሕብረተሰብ በአዲሱና መደብአልባ ሕብረተሰብ ከለ ግል ሃብት ለመተካት ነው።" የሚል ሰፍሮ ነበር። በሌላው የሕጉ አንቀጽ ላይ ዴሞክራቲክ ሴንትራሊዝምን የድርጅቱ ፕሪንሲፕል በማድረግ ክፍሎችንና የድርጅቱን ሕልውና ለማቆረት የሚደፈሩትን እንደሚያስወግዱ ይገልጻል። ጉባኤው የድርጅቱን ስም በ"ሃቀኞች ማሕበር" ፈንታ "የኮሙኒስቶች ድርጅት" በሚለው ቀየረ "የሰው ልጆች ወንድማማችነት" የሚለው መፈክር "የዓለም ወዛአደሮች ተባበሩ" በሚለው ተቀየረ።

በኖቬምበር 1847 የኮሙኒስቶች ቡድን በለንደን ሁለተኛ የወኪሎች ጉባኤውን ማርክስና ኤንግልስ በተገኙበት አካሄደ። የጉባኤው ዋና ዓላማ የፓርቲውን ፕሮግራም ለመንደፍ ነበር። ማርክስና ኤንግልስ ኃላፊነትን በመውሰድ የኮሙኒስት ማኒፌስቶ የሚባለውን ፕሮግራም በ1848 በለንደን በይፋ አወጡ።

<u>ማርክስና ኤንግልስ በኮሙኒስት ማሕበር ውስጥ የተነሱትን</u>
<u>የግራና የቀኝ አድርባዮች እንዴት እንደታገሉ</u>።

በ1848 በአውሮፓ ውስጥ ተፋፍሞ የነበረው የመደብ ትግል በቡድኖች መሀከል በማንፀባረቁ የግራና የቀኝ አድርባይ ኃይሎች በመነሳት ማርክሲዝምን ተፈታተኑት።

<u>የቀኝ አድርባዮች</u>፡— በማሕበሩ ውስጥ የቀኝ አድርባይነት መሰመር ወካይና መሪ የነበረው ቦርን የተባለው ሰው ነበር። ቦርን ከ1824–1898 ድረስ የኖረ ሰው ነው። ይህ ሰው በበርሊን "የወዛአደሩ ማእከላዊ ኮሚቴ" እና "የወዛአደሮች ወንድማማች ማሕበር" የሚባሉት የሁለቱ ማሕበሮች ሊቀመንበር ነበር። ለአነስተኛ ቀንና ለውጦች ብቻ የሚታገል ሰው ነበር። የቡርዧ ዴሞክራቲክ አብዮት ማካሄድ የወዛአደሩ ተግባር ሳይሆን የከበርቴው ነው ይል ነበር። ወዛአደሩ በሕብረት ከሰራና ከመንግሥት ተበድሮ የራሱን ባንክ ከአቋቋመ "ነፃ መደብ ይሆናል" ከማለቱም ሌላ ቡርዧዎች በዚህ መንገድ ቀስ በቀስ ይጠፋሉ። የሚል እምነት ነበረው። በመጨረሻም "ወዛአደሩን ከትግል መመለስ ተገቢ ነው"በማለት ጭልጥ ያለ አድርባይነቱን አረጋገጠ።

<u>"የግራ" አድርባዮች</u> ፡— በማሕበሩ ውስጥ የዚህ ክንፍ መሪ ጎትሻልክ /1815–1849/ የሚባለው የኮለን የወዛአደር ማሕበር መሪ የነበረ ነው። ይህ ሰው ገበሬውን ችላ በማለት ወዛአደሩ "ለወዛአደር ሪፓብሊክ" ብቻ መታገል አለበት ይል ነበር። የወዛአደሩ መደብ ከሌሎች

እና ከረመር ተቃረሙ፡፡ ማርክስም የዓለም አቀፉን ደንብ እንዲነበቡ ተወሰነ፡፡ ይህ ዓለም አቀፍ ከተመሰረተ ወዲህ ማርክስና ኤንግልስ አዉርጣቸዉን የታገሉበትን ወቅቶች በሁለት ከፍለን ከዚህ በታች እናያለን፡፡

<u>የመጀመሪያው ወቅት</u>፡- ይህ ወቅት ከለንደን 1865፣ ከጄኔቭ 1866፣ ከሎዛን 1867እና በመጨረሻም እስከ በራስል ጉባኤ 1868 ድረስ ከፕሩዶን፣ ከሳባሊያንና ከእንግሊዝ የሙያ ማሕበሮች ጋር የተካሄዱት ክርክሮች ናቸው፡፡

<u>ሁለተኛው ወቅት</u>፡- ሁለተኛው ወቅት ከ1869 የባስል ጉባኤ እስከ 1872 የሄግ ጉባኤ ድረስ ያለው ጊዜ ነው፡፡ በ ሁለተኛው ወቅት ውስጥ የፓሪስ ኮምን እንቅስቃሴ ተካሄዶ ስለነበረ በ1871 በለንደን ጉባኤ ተካሄዶ ነበር፡፡ ሁለተኛው ወቅት በአጠቃላይ የሚያተኩረው ማርክስና ኤንግልስ በባኩኒን ላይ ያካሄዱትን ትግል ነው፡፡

<u>በፕሩዶኒዝም ላይ የተደረገው ትግል</u>፡- በአንደኛው ዓለም አቀፍ በመጀመሪያ የተደረገው ትግል የፕሩዶኒዝምን አስተሳሰብ በሚከተሉት ላይ ያተኮረ ነበር፡፡ ፕሩዶን ንዑስ ከበርቴው ወደ ወዝአደርነት ሳይለወጥ የሚያድርበትን ጭንቀት የሚያሳይና የሚያንፀባርቅ አስተሳሰብ አስፋፊ ነበር፡፡ ይህ ሰው ንዑስ ከበርቴን ሕብረተሰብ ለመመስረት ምኞት ነበረው፡፡ ቀጥሎም እንዲሁ ፕሩዶን አንደኛው ዓለም አቀፍ እንደተመሰረተ በዋናነት በፓሪስ የሚገኙት ደቀመዛሙርቶቹ አስተሳሰቡን በአንደኛው ዓለም አቀፍ ውስጥ ለማስፋፋት በዙ ጥረቶች አደረጉ፡፡

ማርክስና ኤንግልስ ከብዙ በጥቂቱ በአንደኛው ዓለም አቀፍ ውስጥ የፕሩዶንን አስተሳሰብ ከዚህ በሚቀጥሉት ነጥቦች ላይ ታግለውት ነበር፡፡

<u>የዓለም አቀፍ አመራርን በሚመለከት</u>፡- የማርክሲዝም በወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ስር እየሰደደ መሄዱ ትልቅ ስጋት ያደረባቸው ፕሩዶኒስቶች በለንደንና በጄኔቭ ጉባኤ ላይ ምሁሮችና [illegible] ማርክሲስቶች ከዓለም አቀፍ ወዝአደር እንቅስቃሴ ማግለል ያስፈልጋል የሚል ኃሳብ ለጉባኤ አቀረቡ ነበር፡፡ ሁለትም ጊዜ ተሸንፈው በማፍረት ኃሳባቸው ውድቅ ሆነባቸው፡፡ ይህን አይነት ኃሳብ ያቀረቡት ምሁሮችን በተለይም ማርክስና ኤንግልስን ከዓለም አቀፍ በማባረር አመራሩን በእጃቸው ለማድረግ አስበው ስለነበረ ነው፡፡

<u>ወዝአደሩ እንዴት ነፃ ሊወጣ ይችላል? በሚለው መሰረታዊ ጥያቄ ላይ</u>፡- ፕሩዶኒስቶች አብዮታዊውን መስመር በመቃወም "የመደቦችን ወንድማማችነት" በማስተጋባት ወዝአደሩ የተቃውሞ አድማ ማድረግ የለበትም፣ የወዝአደሩ የሙያ ማሕበር አያስፈልገውም፣ ለስምንት ሰዓት የሥራ ጊዜ መታገል የለበትም፣ ሴቶች በምንም አይነት በምርት ላይ መሳተፍ የለባቸውም፣...ወዘተ የሚሉ አቋሞች ነበሩቸው፡፡ የሎዛን ጉባኤ በፕሩዶኒስቶች ላይ ድል በመቀዳት የወዝአደሩን የፖለቲካ ትግል በመደገፍ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ ውሳኔውም የወዝአደሩ ነፃነት ከፖለቲካ ነፃነት የማይለይ መሆኑን፣ ወዝአደሩ በፖለቲካ ትግል ላይ በመሳተፍ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መብት ነፃነት ማግኘት እንዳለበት የሚያስረዱ ነጥቦችን ያዘለ ነበር፡፡

<u>የብሔራዊ ነፃ ለመዉጣት እንቅስቃሴን በሚመለከተው</u>፡- አረመኔው የፈረንሳይ የዘር መን



ወደቦች ጋር የትግል አንድነት እንዲፈጠርም ይታገል ነበር፡፡ ማርክስና ኤንግልስ የዚህን ቡድን እጅ እየበቱ ከታገሉት በኋላ የኮሙኒስት ማሕበሩን ፍረሳ ወሰኑ፡፡

ማርክስና ኤንግልስ በ1850 በአደረጉት የኢኮኖሚ ጥናት መሰረት [illegible] የ1847 የኢኮኖሚ ቀውስ እንደከለለፈ፣ የ1848 አብዮታዊ እንቅስቃሴ እንደተሳለፈና የአብዮቱ ኃይሎች ደንገሬ ባለመሆናቸው የትግል ስልታቸውን በመለወጥ ለመጪው አብዮታዊ ጊዜ ለመዘጋጀት ኃይል መሰብሰብ አስፈላጊ እንደሆነ ገለጹ፡፡ ነገር ግን የኮሙኒስት ማህበር ማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የነበሩት ዊሊች እና ሻፐር ይህን ሐሳብ በመቃወም "ለሥልጣን እንታገል ወይስ እንተኛ" በሚል ጀብደኛ አስተሳሰብ ማሰራጨት ጀመሩ፡፡ ማርክስና ኤንግልስ በሴፕቴምበር 1850 በተደረገው ጉባኤ ላይ የዊሊ -ሻፐር ንኡስ ከማዕከላዊው ኮሚቴ ታግለው በማባረር አዲስ ማዕከላዊ ኮሚቴ በመመሥረት የኮሚቴውን መቀመጫ ቦታ ከለንደን ወደ ኮሎን ቀየሩት፡፡ በኦክቶበር 1850 መቀመጫውን ወደ ኮሎን የቀየረው ማዕከላዊ ኮሚቴ በእነ ዊሊ-ሻፐር ቡድን ጠቋሚነት የጀርመን ፖሊሶች የኮሙኒስት ቡድኑ አባላትን ይዘው አሰሩ፡፡

ይህ ድርጅት በተቋቋመ በአምስት ዓመቱ ማርክስ እንደፈረሰ ባቀረበው ሐሳብ መሠረት ፈረሰ፡፡

<u>ማርክስና ኤንግልስ በአንደኛው ዓለም አቀፍ አመራራቸውን እንዴት እንደታገሉ፡፡</u>

በ1857 ለመጀመሪያ ጊዜ [illegible] የካፒታሊስት ዓለም ውስጥ የኢኮኖሚ ቀውስ ደረሰ፡፡ ይህ ቀውስ በወዝአደሩ ጀርባ ላይ ወደቀ፡፡ በዙዎች ሥራፈት ሆኑ፡፡ ደመወዝ ተቀነሰ፡፡ በወዝአደሩና በከበርቴው መካከል ያለው ቅራኔ ተባባሰ፡፡ አዲስ ሁኔታም ተፈጠረ፡፡ በእንግሊዝ አገር የሥራ ሰዓት እንዲቀነስ ግንበኞች ጠየቁ፡፡ ይህ ተቃውሞ በሌሎች የሥራ መስክ ላይ የተሰማሩትን ወዝአደሮች ድጋፍ አገኘ፡፡ ወዝአደሮችም በዚህ የትግል ሁኔታ በሰንዐን መደራጀት ጀመሩ፡፡ የእንጨት ሥራ ማህበር ፣ የማዕድን ሠራተኞች ማህበር፣ ...ወዘተ ተመሠረቱ፡፡ በ1860 የመላው ለንደን ወዝአደሮች የሙያ ማህበር /ትሬድ ዩኒየን/ ተቋቋመ፡፡ በፈረንሳይ በ1863 በፓሪስና በማርሴል የሚገኙ ወዝአደሮች የመረዳጃ ማህበር አቋቋሙ፡፡ በኋላም የብረትና የመጋበሱ ሠራተኞች ማህበር ተቋቋመ፡፡ የቦናፓርት መንግሥት በተደረጉት የሥራ ማቆም አድማዎች ተከልክሎ የነበረውን የመሰብሰብና የሠላማዊ ሠልፍ መብቶችን የግዱ ፈቀደ፡፡ በጀርመን አገር በሌፕዚግ በ1863 ወዝአደሩ ከብዙ ትግል በኋላ አጠቃላይ የጀርመን ወዝአደሮች ማህበር የሚባለውን ለመመሥረት ቻለ፡፡ በአሜሪካም ቀጥሎ እንዲሁ የበዓኛ የደቡብ ጦርነት ቢካሄድም ወዝአደሩ የኮሙኒስቶች ከበርና በፌዴራል የወዝአደር ማህበር የሚባሉትን አቋቁሞ ነበር፡፡ በሌሎች የአውሮፓ አገሮች እንደ ኢጣሊያ ስዊዘን፣ በልጂየ፣ ኔዘርላንድ፣ ስዊድን...ወዘተ እስከ 60ኛው ዓመተ ምህረት መጨረሻ ድረስ የተደራጀ የወዝአደር ማሕበር አቋቁመው ነበር፡፡

በሴፕቴምበር 28 1864 በለንደን ከተማ በሴንት ማርቲንስ አዳራሽ ውስጥ ከእንግሊዝ፣ ከጀርመን፣ ከኢጣሊያ፣ ከአየርላንድና እንዲሁም ከሌሎች አገሮች በፈረንሳይ ወዝአደሮች ኃሳብ አቅራቢነት ስለ አንደኛው አለም አቀፍ የወዝአደሮች ማሕበር መቋቋም ተሰበሰቡ፡፡ በጉባኤው ላይ ማርክስ በአባልነት የሚገኙበትና 21 ሰዎችን የሚያቅፍ ጊዜያዊ ማዕከላዊ ኮሚቴ ተመረጠ፡፡ ለፕሬዝዳንትነትና ለዋና ጸሐፊነት የእንግሊዝ ወዝአደር ሙያ ማሕበር መሪዎች የነበሩት ኦጀር

ነሥት ፖላንድን በቅኝ ገዢነት ቁጥጥር ሥር ይዛ ነበር፡፡ የፖላንድ ሕዝብ ከዚህ ቀን እስከ ዛሬ ነፃ ለመውጣት በ1863 ተነሳ፡፡ ይህ የፖላንድ ሕዝብ እንቅስቃሴ ሲዳፈን መንግሥት የሚያሳክሙና የዓለም አቀፍ ወዛአደሩን እንቅስቃሴ የሚያደናክር መሆኑን የተረዱት ማርክስና ኤንግልስ ለትግሉ ድጋፍ ሰጡ፡፡ ፕሩዶኒስቶች ገና በለንደንና በጄኔቭ ጉባዔ ላይ የፖላንድን ሕዝብ ትግል ተቃወሙ፡፡ "የፖላንድ ሕዝብ መደብደብ አለበት፤ ከዛሬ መንግሥት የሚደርስበት ጭቆና የሚገባው ነው፡፡ ይገባቸዋል፡፡" አሉ፡፡ ጉባዔው ይህንን መሥመር በመቃወም ለፖላንድ ሕዝብ ድጋፉን በሙሉ ድምፅ በውሳኔ ላይ አሰፈረ፡፡ ድርጅቱም ለእውነተኛ ዓለምአቀፍ ዩኒቲን አስመሰከረ፡፡ ፕሩዶኒስቶችም በዚህ ጥያቄ ላይ ድል ተመቱ፡፡

<u>የግል ሀብትን በሚመለከተው</u>፡- በኮሙኒስት ማኒፌስቶ ላይ የተገለፀውን "የግል ሀብት መቀረት" የሚለውን በመቃወም ፕሩዶኒስቶች በለዛን ጉባዔ ላይ "የሥራ ዋጋ ለአምራቾች መሬት በግል ሀብትነት ለገበሬዎች" የሚል መፈክር አነሱ፡፡ በብራሰልስ ጉባዔም ላይ የመሬት ባለቤትነት "ለደሐና ለአርሶዎች" አስፈላጊ ነው የሚል ሐሳብ ይዘው ተነሱ፡፡ በባዚል ጉባዔ ላይ የማዕድን ዋሻዎች፣ መሬት፣ መጓጓዣ...ወዘተ የሕብረተሰብ ሀብት መሆን አለባቸው በሚለው የማርክስ ሪፖርት ላይ ተመርኩዞ የዓለም አቀፍ ድርጅቱ ውሳኔ አሳለፈ፡፡ ፕሩዶኒስቶችም የነበራቸው ከበርቴን ሕብረተሰብ መሰረት የሚለው ጋብቻቸው ለመወረስ ጊዜ ከሸበቸው፡፡ በዓለም አቀፉ ውስጥ በዚሁ መስመር አቋማቸው ትንሽ ጊዜ ከቆዩ በኋላ ከታሪክ ኩነት በኋላ ተበታትነው ጠፉ፡፡

<u>ማርክስና ኤንግልስ ከእንግሊዝ የሠራተኛ ማኅበር ጋር ያደረጉት ትግል</u>

ከ1850—1860 ድረስ ለወዛአደሩ ቀጥሎ ይታገል የነበረው የእንግሊዝ የወዛአደሮች የሠራተኛ ማኅበር በአድርባይነት የተሞላ ነበረ፡፡ ይህ የሠራተኛ ማኅበር ወዛአደሩ የኑሮና የሥራ ቦታው ከተሻሻለለት በቂ ነው በማለት ወዛአደሩ በኢኮኖሚ ትግል ብቻ ተወስኖ እንዲቀር ጥረት ያደርግ ነበር፡፡ "ለአንድ ቀን ሥራ የአንድ ቀን ተገቢ ደመወዝ" በማለት በዓለም አቀፍ ድርጅት ውስጥ ገብተው የትሬድ ዩኒየን ጋባዥ ለማስፋፋትና አሻጥርን ለመስራት አስበው ነበር፡፡ ማርክስና ኤንግልስ ይህ የሠራተኛ ማኅበር የቀኙ ወዛአደር መሪዎች ማኅበር ነው በማለት ውስጣዊ ይዘታቸውን አጋለጡ፡፡

ማርክስና ኤንግልስም እነዚህን አድርባዮች ዓለም አቀፍ ውስጥ ገብተው እንዲሰሩ ያደረጉበት እንደኛው ምክንያት ይህ ድርጅት በብዙ የእንግሊዝ ወዛአደሮች ዘንድ ተቀባይነት ስለነበረውና እነዚህንም ወዛአደሮች ወደ ዓለም አቀፉ ለመሳብ የሚችሉበት አመቺ ሁኔታ በመሆኑ ነበር፡፡ ይህ ማርክስና ኤንግልስ ያጋለጡት የወዛአደር መሪዎች ማኅበር የአድርባዮች መፈልፈያና መፈልፈያ ነበር፡፡ ይኸውም የእንግሊዙ ከበርቴ ከቅኝ አገሮች የሚዘርፈውን ጥሬ ሀብቶች በአገሪቱ ኢንዱስትሪ ውስጥ ያመርታል፡፡ ከዚህም ትርፍ ሽያጭ የሚያገኘውን የተወሰነ ትርፍ በእንቅስቃሴ ላይ የሚገኙትን ወዛአደሮች በጥቅማቸው ስር ለማቀፍና ለማታለል አቀፍ ወዛአደሮች በማለት መሪዎችን ከበሬው ወዛአደር በመነጠል በጉቦና በጉርሻ ገዝቶ ወዛአደሩን በመሪነት እንዲቆጣጠሩለትና ትግሉን እንዲያደናቅፉ ሆነ ተብሎ የሚሰራ ተንኮል



ነበር፡፡

<u>ማርክስና ኤንግልስ ከትሬድ ዩኒየኖም ጋር ያካሄዱትን ትግል አንዳንድ ነጥቦችን እናነሳለን</u>፡-

<u>የሠራተኛ ማኅበርን እንቅስቃሴ በሚመለከተው</u>፡- እነዚህ ትሬድ ዩኒየኒስቶች ወዛአደሩ ለደመወዝ ጭማሪ አይታሰብ የሥራ ማቆም አድማ ማድረግ የለበትም ይሉ ነበር፡፡ የደመወዝ ጭማሪ መጠየቅ በእቃዎች ላይ የዋጋ መጨመርን ያስከትላል በማለት ሲቃወሙ ወዛአደሩ እንዲ ያም በሙያ ማኅበር መደራጀት አያስፈልገውም ይሉ ነበር፡፡ ማርክስ ደመወዝ፣ ዋጋና ትርፍ /ዌጅ ፕራይስ ኤንድ ፕሮፊት/ በሚለው ጥናቱ እነዚህን አድርባዮች በማጋለጥ ከበርቴው በምርቱ የወዛአደሩን ደመወዝ በጣም ዝቅ ለማድረግ የሚጥር መሆኑን ካስረዳ በኋላ ወዛአደሩ ለደመወዝ ጭማሪ መታገል እንዳለበትና በደመወዝ ጭማሪው ብቻ ተደስቶና ተደልሎ ትግሉን ባይ ረቢ ማፋፋም እንዳለበት ገለጸ፡፡

<u>የወዛአደሩን የሥራ ሰዓት በሚመለከተው ጥያቄ</u>፡- እሱ የተቃወሙበትን፤ ትክክል ያልሆነውንና የእንግሊዝ አገር ዋና ጥያቄ የነበረውን የምርጫ ጉዳይ የሚመለከት ጥያቄ ነበር፤ የምርጫው ሕግ እንዲቀየር ወዛአደሩ ብዙ ጊዜ ታግሎ አካሂዶ ነበር፡፡ ማርክስና ኤንግልስም የምርጫው ሕግ እንዲቀየር ወዛአደሩ በየጊዜው ይቀሰቅሱ ነበር፡፡ ለዚህ የዲሞክራሲ መብት መሰጠት የእንግሊዝን ወዛአደር በየጊዜው ቀስቅሰው ነበር፡፡ በ1867 ወዛአደሩ ባደረገው ትግል የእንግሊዝ መንግሥት ይህን የምርጫ መብት እንዲሰጥ ተገደደ፡፡ ሆኖም ይህ የተሰጠው መብት ለበሬው ወዛአደር ሳይሆን ለሊበራል ከበርቴዎችና ለከፍተኛው የወዛአደር መሪዎች ብቻ ነበር፡፡ ይህንን ሪፎርም የትሬድ ዩኒየን መሪዎችና ሊበራል ከበርቴው በደስታ ተቀበሉት፡፡ የትሬድ ዩኒየኑ መሪዎች ይህ መብት ለወዛአደሩ አያስፈልገውም በማለት ገደቡት፡፡ በዚህም ምክንያት ለዚህ መብት የተደረገው ትግል በመሐል መንገዱ ተጨናገፈ ቀረ፡፡ የትሬድ ዩኒየኑ አመራር ወዛአደሩን በመክዳት ከመንግሥትና ከሊበራል ከበርቴው ጋር ባደረገው ስምምነት የወዛአደሩን ትግል በመክዳቱ ማርክስ ይህን ማኅበር አጥብቆ ታገለው፡፡ ወዛአደሩም ለዚህ የዲሞክራሲ መብት መሰጠት መታገል እንዳለበት ቅስቀሳ አደረገ፡፡

<u>የአየርላንድን የብሔራዊ ነፃ አውጪ እንቅስቃሴ በሚመለከተው</u>፡- እንግሊዝ በመጀመሪያ ቅኝ ገዢነት አድርጋ የያዘቻት አገር አየርላንድ ነበር፡፡ ከ1801 ጀምሮ የአየርላንድ ሕዝቦች ለብሔራዊ ነፃነታቸው ያካሄዱት የነበረው ትግል ወደ 1860 ገደማ ላይ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ደረሰ፡፡ የትሬድ ዩኒየኑ መሪዎች ግን ጥልቅ ባለ የትምክህተኝነት አቋማቸው የከበርቴውን መንገድ በመከተል የቅኝ ገዢዎች ቀጥ ጠባቂ ጠበቃዎች በመሆን የአየርላንድ ሕዝቦች የሚያካሂዱትን ትግል ይቃወሙ ጀመር፡፡

ማርክስና ኤንግልስ የነዚህን አድርባዮች አቋም በማጋለጥ ያለም አቀፍ ወዛአደሮችን አቋም በማስተጋባት "ሌላውን ሕዝብ የሚጨቁን ሕዝብ የራሱን ማሰሪያ ሰንሰለት ይሰራል" በማለት የእንግሊዝ ወዛአደር ራሱን ነፃ ለማውጣት መታገል እንዳለበትና ወዛአደሩ ራሱን ከከበርቴው በመለየት ለአየርላንድ ብሔራዊ እንቅስቃሴ ድጋፍ መስጠት እንዳለበት አስረዱ፡፡ የእንግሊዝን አረመኔነት በማጋለጥ የዓለም ወዛአደሮች ይህንን ድርጊት እንዲቃወሙና የታሰሩትም የአየርላንድ ታጋዮች እንዲፈቱ የተቃውሞ ሰልፍ አደረጉ፡፡

ከለንደን ጉባዔ በኋላ ማርክስ ባቀረበው ኃሳብ መሰረት የዓለም አቀፍ ፕሬዚዳንት የነበረው ኦዶገር የሚባለው ሰው ከቦታው እንዲነሳ ተደረገ፡፡ እነዚህ አድርባዮች የአውሮፓ መንግሥታት አንደኛውን ዓለም አቀፍ ለመደምሰስ ሲነሱ ከአንደኛው ዓለም አቀፍ ለመውጣት አጋጣሚ ምክንያት ስለፈጠረላቸው ከድርጅቱ በገዛ ፍቃዳቸው ወጡ፡፡ በመጨረሻም ወዝ አደሩን በመክዳት ወደ ከበርቴው ካምፕ ገቡ፡፡

<u>ከላሳሊያን ጋር የተደረገው ትግል</u>

ላሳል /1825–1864/ ከአንዱ የፕሩሲያ ቱጃር..ቤተሰብ ተወለደ፡፡ አባቱ የወርቃጨርቅ ነጋዴ ነበር፡፡

ይህ አድርባይ ሰው በ19ኛው መቶ አጋማሽ ላይ በጀርመን አገር አድርባይነትን የአስፋፋ ነው፡፡ በጀርመን አገር የካፒታሊዝም ማደግ የመደቦችን ቅራኔ አፋፋመ፡፡ ወዝ አደሩም ነፃ የሆነ ድርጅት ለማቋቋም አመቺ ሁኔታ በማግኘቱ በ1863 መላው የጀርመን ወዝ አደሮች ማህበር የሚባለውን አቋቋሙ፡፡ ላሳልም የፕሬዚዳንትነቱን ቦታ ያዘ፡፡

ላሳል በ1848 አብዮት ጊዜ በሬይን ጋዜጣ አማካይነት ማርክስን ሊተዋወቀው ቻለ፡፡ ከዚያም በኋላ ሶየኛ ሶሻሊስት በመቀበል የማርክስ ተማሪ ነኝ እያለ ወደ 1860 ላይ አገዛዙ ጽሑፎችን ማውጣት ጀመረ፡፡ ይህ ሰው ፀረ–አብዮተኛ፣ ወዝ አደሩን የከዳና በሁለት ቋንቋ የሚናገር ታክቲክም ፖለቲካዊ መልኩ ያለ አድርባይነትን የሚያራምድ ነበረ፡፡

ላሳል መንግሥት "እንደ መደብ ሌሎችን መደቦች የሚጨቁንበት መሣሪያ አይደለም፣ በአጠቃላይ ቀጥተኛና ነፃ ምርጫ የከበርቴው መንግሥት በሕዝባዊ መንግሥት ሊለውጥ ይችላል፡፡" "ወዝ አደሩ በምርጫ ብቻ ነፃ ሊወጣ ስለሚችል አብዮታዊ አመጽና የወዝ አደሩ አምባገነንነት አያስፈልገው" በማለት የማርክስንና የኤንግልስን አብዮታዊ መስመር ይቃወም ጀመር፡፡ የወዝ አደሩ አጋር የሆኑትን ጭሰኛውን ገበሬና እነዚህም ሌሎችን መደቦች "አድሃሪ ኃይሎች" ናቸው በማለት በወዝ አደሩና በገበሬው መሀከል መመስረት ያለበትን አንድነት ይቃወም ነበር፡፡ "የወዝ አደሩ ድህነት" የተፈጥሮ ሕግ ነውና ምንም ማድረግ አይቻልም በማለት ያወናብድ ጀመረ፡፡

በመጨረሻም የአድርባይ መስመሩን ለማስፋፋት ከፕሩሲያ መንግሥት ጋር በድብቅ መነጋገር ጀመረ፡፡ የፕሩሲያውን ቻንስለር ቢስማርክን እያደነቀ ከቆየ በኋላ በ1863 በድብቅ ይገናኝ ጀመር፡፡ ይህን ሁኔታ የደረሰበት ማርክስና ኤንግልስ ድርጅቱን ወርቦ እንደከዳ ይገነዘቡ፡፡ ላሳልም ከሞተ በኋላ ደቀመዛሙርቱ የጀርመኑን የወዝ አደር ድርጅት በቁጥጥራቸው ስር ለማድረግ በዓለም አቀፍ ውስጥ እንዳይገቡ እንቅፋት ሆኑ፡፡ እንዲያውም የፕሩሲያ መንግሥት የጀርመን ወዝ አደሮች ከሌሎች ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እንዳያደርጉ ተጽእኖ እንዲያደርግባቸው ሞከሩ፡፡ ማርክስና ኤንግልስ ከድርጅቱ ተራማጅ ክፍሎች ከዊልሄልም ሊብክነሽት እና ከኦገስት ቤበል ጋር ግንኙነት በማድረግ የላሳልን ተከታዮች ተዋጉ፡፡ ተራማጆቹ ቤበል እና ሊብክነሽት ከነሱም በ1867 ከድርጅቱ ወጡ፡፡

በ1869 በሊብክነሽትና በቤበል መሪነት በአይዘናክ ከተማ የወዝ አደር ወኪሎች



በተገኙበት የጀርመን ሶሻል ዲሞክራቲክ ፓርቲ ወይም የአይዘናከር ፓርቲ የሚባለው ተቋቋመ፡፡ የአይዘናከሩ ፓርቲ በአገሩ ውስጥ የዓለም አቀፍን የፓርቲ ፕሮግራም ተቀበለ፡፡ የላሳልን አስተሳሰብ ከወዝ አደሩ መደብ ለማጽዳት ማርክስና ኤንግልስ ትግላቸውን ቀጠሉ፡፡

<u>ከአናርኪስቱ ባኩኒን ጋር የተደረገው ትግል፡፡</u>

ከፕሩደን በኋላ በአንደኛው ዓለም አቀፍ ውስጥ ባኩኒንና ተከታዮቹ በቦታው ተተኩ፡፡ እነዚህ አድርባዮች — የድርጅቱን አንድነትና ሕልውና ለማናከም መከፋፈልና የዓለም ወዝ አደር እንቅስቃሴን ማዳከምን ተግባራቸው ሆነ፡፡ ሚካኤል ባኩኒን /1814–1876/ ከአገሩ የሩሲያ ደጃዝማቾች ቤተሰብ የተወለደ ሰው ነው፡፡ በ1848 በፕራግና በድሬስደን ተደርጎ በነበረው አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ተሳትፎ ስለነበረ በእስረኝነት ተይዞ ለዛሩ መንግሥት ተሰጠ፡፡ እስር ቤትም ሆኖ "ስህተቴን አምኛለሁ" በማለት ምህረት እንዲደረግለት ጠይቆ ምህረት ስላልተደረገለት ከታሰረበት የሳይቤሪያ እስር ቤት አምልጦ ወደ ጃፓን ከዚያም ወደ አሜሪካ ከሄደ በኋላ በመጨረሻም ወደ አውሮፓ ተመለሰ፡፡ በ1864 አንደኛው ዓለም አቀፍ ውስጥ ገባ፡፡ ከዚያም ወዲህ የዘመናዊው ሕብረተሰብ ዋና ጠላት ካፒታሊዝም ሳይሆን መንግሥት ነው በማለት ማንኛውንም መንግሥት በተለይም ደግሞ የወዝ አደሩን አምባገነን መንግሥት ይቃወም ጀመረ፡፡

"የመውረስን መብት በመከልከል፣ የህብረተሰብ ሥራ በማስተጓጎል፣ የጋራ ሃብት በመመስረት፣ ከአምባገነንነት ነፃ የሆነና ሕዝባዊ ማዕከላዊ አመራር የሌለበት ነፃ ሕብረተሰብ ለመመስረት ይቻላል፡፡" የሚሉትን ሃሳቦች ማስፋፋት ጀመረ፡፡ ይህን ሕብረተሰብ በኃይል ለመቀየር ዋናው ኃይል ወዝ አደሩ ሳይሆን የዱርዬው ክፍል ነው በማለት የወዝ አደሩን አብዮትና የወዝ አደሩን አምባገነንነት ይቃወም ጀመረ፡፡

ይህ ሰው ከሌሎቹ አድርባዮች የሚለየው በአቀራረቡ ብቻ ነው፡፡ የባኩኒን አናርኪስት አስተሳሰብ የሶሻል መሰረት አለው፡፡ ይህ ሰውም በ1840 ገደማ ላይ በፕሩደን አናርኪዝም ተመርዞ ነበር፡፡ በ1860 በኢጣሊያ አገር በሚኖርበትና በፖለቲካ ትግል ውስጥ ተሳትፎ በሚያደርግበት ጊዜ በዚህ አገር ካፒታሊዝም የገጠሩን ገበሬና የከተማውን ንዑስ ከበርቴ ወደ ሃብት የለሽነት ሲቀይራቸው ይመለከት ነበር፡፡ በዚህም የካፒታሊዝም እድገት ደሃ እየሆኑ የሚሄዱት ወጣት ንዑስ ከበርቴዎች ተስፋ በመቁረጥና በቁጣ ያገኙትን በኃይል ይደመስሱ ይዘርፉ ነበር፡፡ ባኩኒን ከዚህ ተነስቶ ሶሻል አብዮት ለማድረግ እነዚህን ኃይሎች ማሰለፍ ያሻል በማለት አይዲዮሎጂውን መሰረተ፡፡ ባኩኒን የወዝ አደሩን እንቅስቃሴ የጎዳው በአናርኪስትነቱ ብቻ ሳይሆን በተንኮሉና በከፋፋይነቱ ሥራውም ጭምር ነበር፡፡ ማርክስ ይህንን ሰው "በቲዎሪ ባዶ የሆነ አሻጥር አንጃሪው የሆነ ሰው ነው፡፡" በሉታል፡፡

በ1872 በአምስተኛው የዓለም አቀፍ ጉባኤ ላይ ባኩኒን በፈጸማቸው ተንኮሎች፣ በቡድን ማቀነባበርና በፀረ አብዮተኛነቱ ተከስ ከድርጅቱ ተባረረ፡፡ በ1873 የጄኔቭ ጆርናል በተባለው ጋዜጣ ላይ በገዛ ... እጅ ከትግል መውጣቱን እንደተሰናበተ ገለጸ፡፡ በ1876 ሞተ፡፡ ከፓሪስ ኮምዩን መውደቅ በኋላ በአድሃሪ የአውሮፓ መንግሥታት ክትትልና በባኩኒን የመከፋፈል ሥራ ምክንያት ዓለም አቀፍ በአውሮፓ ውስጥ ለመስራት ስላልቻለ መቀመጫውን ወደ አሜሪካ አገር ቀየረ፡፡

ማርክስ ባቀረበው ሃሳብ መሰረት በሐምሌ 15/1876 በፊላዴልፊያ የተሰበሰበው የመጨረሻው ስብሰባ የአንደኛው ዓለም አቀፍ እንዲፈርስ ወሰነ፡፡

## ማርክስና ኤንገልስ በወዛአደር ፓርቲ አመሰራረት ጉዳይ ላይ በአውሮፓና በአሜሪካ አድርባዮችን እንዴት እንደታገሉ፡፡

በአሥራዘጠነኛው ክፍለ ዘመን በ70ና 80 ዓመት ላይ ካፒታሊዝም ባደረገው ፈጣን እድገት ምክንያት በወዛአደሩና በከበርቴው መካከል ያለው ቅራኔ የቀዳሚውን ቅራኔ ቦታ ያዘ፡፡ በዚህም ዘመን ወዛአደሩ ራሱን የቻለና ነፃ የሆነ አብዮታዊ ፓርቲ መፍጠር ግዴታው ሆነበት፡፡

በማርክስና በኤንገልስ አርዓያ በአውሮፓና በአሜሪካ ተራ በተራ የሶሻሊስት ድርጅትና ፓርቲ ተመሰረቱ፡፡ ከ1869 የአይዘናከሩ የጀርመን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ በኋላ በ1870 በሆላንድ፣ በ1871 በዴንማርክ፣ በ1877 በአሜሪካ፣ በ1878 በቼኮዝሎቫኪያ፣ በ1882 በኢጣሊያ፣ በ1885 በቤልጂግ፣ በ1887 በኖርዌይ፣ በ1888 በኦስትሪያ፣ 1889 በስዊድና በስዊዙን የሶሻሊስት ወዛአደር ፓርቲዎች ተመሰረቱ፡፡ በፈረንሳይም በ1883 የመጀመሪያው የማርክሲስት ድርጅት በ1884 በእንግሊዝ የሶሻል ዴሞክራት ፌዴሬሽን የሚባሉት ተቋቋሙ፡፡

ምንም እንኳን እነዚህ ድርጅቶች ሶሻሊዝምን በማስፋፋት ትልቅ አስተዋጽኦ ቢያደርጉም በተለያዩ የእድገት ደረጃ ላይ ስለነበሩ በአድርባይ ኃይሎች በየጊዜው ተበክለው ነበር፡፡ ማርክስና ኤንገልስ እነዚህን ድርጅቶች በመገንባትና በማጠናከር ሲረዱ የድርጅቶቹን አድርባይ አዝማሚያዎች ታገለው ነበር፡፡

### በጀርመን አገር የወዛአደር ፓርቲ አመሰራረት ላይ የታየው የሁለት መስመር ትግል፡፡

በፈረንሣዩና በፕሩሲያ መካከል በተደረገው ጦርነት ተከፋፍሎ ይተዳደር የነበረው ጀርመን አንድ ሆነ፡፡ ከፈረንሣይ በካሳ መልክ የተገኘው አምስት ሚሊያርድ ፍራንክና ጀርመን በጦርነቱ ከገዛቸው ውስጥ በአጠቃላለው የማዕድን ሃብት የከበረው አልሳስ ሎሬንን ከነበረው የቴክኒክ ሙያ ቀ ጋር ለጀርመን ኢንዱስትሪ በአሩጫ ማደግ ጥሩ አጋጣሚ ፈጠረ፡፡ ይህ ሁኔታ ለወዛአደሩ መደብ በቁጥር መጨመር፣ ከከበርቴው ጋር ያለው ቅራኔ መስፋፋትና ለወዛአደሩ እንቅስቃሴ መጠናከር አመቺ ሆነ፡፡

በፈረንሣዩ የወዛአደሩ መደብ በፓሪስ ኮምዩን መሸነፍ ምክንያት ተዳክሞ ነበር፡፡ በአንጻሩም የወዛአደር መሳፍንት በመነገሡ የወዛአደሩ እንቅስቃሴ ተከሳሽቶ ነበር፡፡ የጀርመኑ ወዛአደር ግን ምንም እንኳን ለሁለት ቢከፈልም ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች በዓለም አቀፍ የወዛአደር እንቅስቃሴ ውስጥ ግንባር ቀደም ነበር፡፡

የአድርባዩ የላሳል ክንፍ በ1863 የተቋቋመው ጠቅላላ የጀርመን ወዛአደር ማሕበር ተብሎ የሚታወቀው ነው፡፡ ሌላኛው ክንፍ ደግሞ በ1869 የተቋቋመው የአይዘናከር የጀርመን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ነው፡፡ ይህኛው ፓርቲ ማርክስና ኤንገልስ ላሳሊያኖችን ታግለው ያቋቋሙት አብዮታዊ ድርጅት ነበር፡፡ የዚህም ድርጅት መሪዎች ኦገስት ቤበል እና ዊልሄልም ሊብክኔሽት ነበሩ፡፡ በነዚህ ሁለት ድርጅቶች መካከል ትልቅ ልዩነቶች ነበሩ፡፡

<u>የአይዘናከር የጀርመን ሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ፡-</u> ከመጀመሪያው ጀምሮ በአንደኛው ዓለም አቀፍ ውስጥ በአባልነት የተካተተ ድርጅት ነው፡፡ ይህ ድርጅት በወዛአደር ኢንተርናሽናሊዝም ላይ በተመሰረተው መስመሩ የፕሩሲያ መንግሥት ፈረንሣይን መውረሩን



የሚቃወም በሆነ ለፈረንሣይ ወዛአደር ወገኑን በመስጠት የፓሪስ ኮምዩን ደግፏል፡፡

<u>የላሳል ጠቅላላው የጀርመን ወዛአደር ማሕበር፡-</u> ዓለም አቀፉን የሚቃወም፣ በትምክህተኛነቱና በብሔረተኝነቱ የፕሩሲያን ወረራ የደገፈ፣ ለፈረንሣይ ወዛአደርና ለፓሪስ ኮምዩን ጥላቻን ያለበት ድርጅት ነው፡፡

ብዙዎቹ የላሳል ድርጅት ደጋፊዎች የነበሩት ወደ አብዮታዊው የአይዘናከር ፓርቲ ይጎርፉ ነበር፡፡ በላሳል የሙራዊም ድርጅት ጥቂት አባሎች ብቻ ቀሩ፡፡ የአይዘናከሩ ድርጅት ከላሳል ድርጅት ጋር የአንድነት ትግልና ህብረት በጋራ ጠላቶች ላይ ያስፈልጋል በማለት ብዙ ጊዜ ጥሪ አቅርቦ ነበር፡፡ ከዚህ በፊት ጥሪውን ያልተቀበለው የላሳል ድርጅት ደጋፊዎቹ በየቀኑ እየቀነሱ ስለሄዱ ካለበት ችግር ለመውጣት ሲል ጥሪውን ተቀበለ፡፡ ማርክስና ኤንገልስም ይህን ሁኔታ በደምብ ከመረመሩ በኋላ የአንድነቱን አስፈላጊነት ደገፉ፡፡ ነገርግን ለአንድነት ዋናው መሰረት የላሳል ወገኖች ከፋፋይነታቸውንና አቋማቸውን መተው እንዳለባቸው አመለከቱ፡፡ አንድነት ከመመስረቱ በፊት በጋራ ጠላት ላይ ህብረት መፍጠር የመጀመሪያው እርምጃ መሆን አለበት አሉ፡፡ የአይዘናከር ወኪሎች ግን የአንድነት አስፈላጊነት ብቻ በመመልከት የማርክስና የኤንገልስን ምክር ለመስማት ባለመቻላቸው የላሳል አድርባዮች የአንድነት ፕሮግራሙን አቋዲው በሁለቱም ድርጅቶች ልቦናች ላይ እንደወጡ በማድረግ በማርች 7/1875 ፕሮግራሙ አወጡ፡፡

ይህም ፕሮግራም የጎታ ፕሮግራም በመባል የሚታወቀው ነው፡፡ ማርክስና ኤንገልስ ይህ የጎታ ፕሮግራም ከኮሙኒስት ማኒፌስቶና ከፓሪስ ኮምዩን መሰረታዊ ሃሳቦች የሚቃረን በመሆኑ ኤንገልስ ለቤበል ረዥም የተቃውሞ ደብዳቤ ጻፈለት፡፡ ማርክስም በአፕሪልና በሜይ 1875 መካከል የጎታ ፕሮግራም ትችት የሚለውን ጽሑፍ በመጻፍ ለሊብክኔሽትና ለቤበል ላካላቸው፡፡ ቤበልና ሊብክኔሽት ስህተታቸውን ባያርሙ በሜይ 1875 የሁለቱ ድርጅቶች ወኪሎች በተገኙበት የአንድነት ጉባዔ ተካሄደ፡፡ በተደረገው የማዕከላዊ ኮሚቴ ምርጫ ሦስት የላሳልና ሁለት የአይዘናከር ሰዎች ተመረጡ፡፡ ማርክስና ኤንገልስም ከዚህ ከተፈጠረው ድርጅት ጋር ምንም አይነት ግንኙነት እንደሌላቸው ገለፁ፡፡

### ማርክስና ኤንገልስ ዱሪንግን እንዳጋለጡ፡፡

ከላሳሊያን ጋር በተደረገው ስምምነት የተመሰረተው የአንድነት ፓርቲ ውስጥ የከበርቴውና የንዑስ ከበርቴው አስተሳሰቦች ይፈልቁበት ጀመር፡፡ ፀረ-ማርክሲስት አስተሳሰብ ስር እየሰደደ መጣ፡፡ የዚህ ፀረ-ማርክሲስት አስተሳሰብ አራማጅ ከ1833-1921 ድረስ የኖረው* ሰው ሆነ፡፡ ይህ ሰው ከፕሩሲያ መሣፍንት ቤተሰብ የተወለደ ነው፡፡ ዱሪንግ በመጀመሪያ በጠበቃነት ይተዳደር ነበር፡፡ ከዚያም በኋላ ከ1863 ጀምሮ በበርሊን ዩኒቨርሲቲ ውስጥ የፍልስፍናና የኢኮኖሚ አስተማሪ በመሆን ይሰራ ጀመር፡፡

ዱሪንግ ወደ 1860 ገደማ ላይ የማርክስን ጽሑፎች በተለይም ዳስ ካፒታልን ለመተቸት ሞከረ፡፡ ወደ1870 ገደማ ላይ ማርክሲዝምን በኃይል መታገል ጀመረ፡፡ የዚህ ሰው አስተሳሰብ በፓርቲው ውስጥ ብዙውን ሰው በቲዎሪ ከማወናበዱም ሌላ ከበርንስታይንና ከሌሎች ጋር በማበር የወዛአደሩን ድርጅት አፍርሶ ሌላ ድርጅት ለመፍጠር ፀረ-ድርጅት ሥራ ማካሄድ ጀመረ፡፡

ማርክስና ኤንገልስ ማርክሲዝምን ከአድርባይነት ለማጽዳት በሶሻል ዴሞክራቲክ ልሳን

*ዱሪንግ፡የተባለው

ላይ ተከታታይ ጽሑፎችን በማውጣት ዱሪንግን አጋለጡ፡፡ እነዚህ ጽሑፎች ፀረ-ዱሪንግ በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡

ኤንገልስ በፀረ-ዱሪንግ ጽሑፉ የዱሪንግን የተዘበራረቀ ፍልስፍና፣ የቡርዧ ፖለቲካ ኢኮኖሚና የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም በሚገባ በማጋለጥ ማርክሲዝምን በበለጠ አዳበረ፡፡

<u>ኤንገልስ የዱሪንግን "ፍልስፍና" በሚመለከተው፡-</u> የዱሪንግ መገለጫ 'አፕሪዮሪዝም' በከንቱ ሜታ ፊዚክስ በሃሳብ አይዲያሊስት ቲዎሪ ላይ የተመሰረተ ነበር፡፡ ይኸውም ዱሪንግ ተፈጥሮና የሰው ልጅ ከመፈጠራቸው በፊት አንድ "መሰረተ ሃሳብ" ነበረ ይላል፡፡ኤንገልስም መሰረተ ሃሳብ የምርምር መነሻ ሳይሆን የምርምር ውጤት እንደሆነና ዱሪንግም ነገሮችን ገልብጦ በጭንቅ ላታቸው የሚያየው አይዲያሊስት እንደሆነ በመግለጽ አስተሳሰብ የዓለም ነፀብራቅ እንደሆነ አስረዳ፡፡

<u>ኤንገልስ የዱሪንግን ፖለቲካ ኢኮኖሚ በሚመለከተው፡-</u> ዱሪንግ የካፒታሊዝምን ስልተ ምርት ማጥፋት ባይሆን ካፒታሊዝም የተመሰረተበትን "አመጽ"በማጥፋት ሶሻሊዝምን መገንባት ይቻላል ይል ነበር፡፡ ኤንገልስ ወዝአደሩ ራሱን ነፃ የሚያወጣው፣ የወዝአደሩ አብዮትና የወዝአደሩ አምባገነንነት በአመጽ ብቻ እንደሚሆን ገለጸ፡፡

<u>ኤንገልስ የዱሪንግን የንዑስ ከበርቴ ሶሻሊዝም በሚመለከተው፡-</u> ዱሪንግ ወደፊት የሶሻ ሊስት ሕብረተሰብ ሊመሰረት የሚችለው "ከትክክለኛነትና በህብረት" ላይ የተመሰረተ ነው ይል ነበር፡፡ ኤንገልስ በታሪካዊ ቁስ አካል ላይ በመመስረት ዱሪንግ የሚለው ሕብረተሰብ ተመኝታዊ እንደሆነና እንዲያውም ሶሻሊዝምን የሚመስል ካፒታሊዝም እንደሆነ በመግለጽ የወዝአደሩ መንግሥት ብቻ ሶሻሊዝምን ለመገንባት እንደሚችል አስረዳ፡፡

በዚህ ሁኔታ በልዩ ልዩ የነበረው የዱሪንግ አስተሳሰብ ውድቅ ሆነ፡፡በዱሪንግ ላይ የተ ገኙት ድሎች ማርክሲዝም በ"ግራ"ና ቀኝ አድርባይነት ላይ ያለውን ኃይለኛነት በበለጠ ያሳ ያሉ፡፡

<u>ማርክስና ኤንገልስ የዙሪክን ትሪዮ አጋለጡ፡፡</u>

በማርክስና ኤንገልስ ትግል በአድሃሪው ዱሪንግ ላይ የተገኘው ድል የወዝአደሩን ድር ጅት ሲያጠናክር በአይዲዮሎጂ ተራም ወዝአደሩን ትልቅ የንቃት ደረጃ ላይ አደረሰ፡፡ ድር ጅቱም ከነበረበት 23 ሺህ ወደ 41 ከፍ ለማለት ችሏል፡፡ ለምክር ቤት በተደረገው ምርጫም በ1877 500ሺህ ድምፅ አገኘ ነበር፡፡ የወዝአደሩን እንቅስቃሴና ፓርቲ እየጠነከረ መምጣት የተመለከተው አድሃሪው የቢስማርክ መንግሥት እንቅስቃሴውንና ፓርቲውን ለመደምሰስ ምክንያቶች ይፈልግ ነበር፡፡ ስለዚህም ቢስ ማርክ በራሱ አነሳሽነት ሁለት ጊዜ በአደባባይ የንጉሡ መኪና እንዲደረገበት በማድረግ ሕዝቡን ካታለለ በኋላ የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ አደገኛ ድርጅት ነው በማለት በህግ አስከለከለ፡፡ ይህ አስቸኳይ አዋጅ የመሰብሰብ፣ የማተም፣የመጻፍ፣የመናገር ...ወዘተ መብቶችን የሚከለክል ነበር፡፡ ከሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ጋር ግንኙነት የነበረው ሰው ይባረር፣ይታሰርና ይሰደድ ነበር፡፡ በወቅቱ ጀርመን የነጭ ሽብር ዘመቻ ይካሄድ ነበር፡፡ ይህ ሁኔታ በህጋዊ መንገድ ይሠራ ለነበረው ለሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ትልቅ ፈተና ሆነበት፡፡ የት ግል ስልቱን ለመቀየር አልቻለም ነበር፡፡ የድርጅቱና የሕዝቡ ግንኙነት በመቋረጡ ወቅቱ ሕብልቅልቅ ወጣ፡፡ የሳባ አስተሳሰቦች በድርጅቱ ውስጥ እንደገና በመነሳት የድርጅቱን መፍረስ



ያደረጉ ውስጥ አስገቡት፡፡ በዙሪክ አባሎችም ይወላወሉ ነበር፡፡ በተለይም በስዊዝ ውስጥ በስደት የሚገኙት ሆችበርግ፣ ስክራም፣ በርንስታይንና ሌሎችም በሶሻል ዴሞክራቲክ ጋዜጣ ላይ የዙሪክ ትሪዮ በሚለው መግለጫቸው ላይ ቢስማርክን ይቅርታ ጠየቁ፡፡ ይህ መግለጫ ወዝአደሩን ከአንገቱ ወደ በከበርቴው ላይ የመደብ ቅርነት ማካሄዱ የለበትም፣ የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ የወዝአደሩ ብቻ ባይሆን የሁሉም ሕዝብ ፓርቲ ነው፣ ስለዚህም ደም የሚያፈስሰውን አብዮት አንፈልገም፣ በሕጉ መሰረት በቀጥታ ለውጥ እናመጣለን፣... ወዘተ የሚሉ ሐሳቦች አዘሉ ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ደግሞ በሞስት፣ ሀሰል ማንና በሌሎች የሚመራ "ግራ" አድርባዮች ተነስተው ነበር፡፡ እነዚህ "ግራ" አድርባዮች ደግሞ የቢስ ማርክን አድሃሪ መንግሥት በተደራጀ መልክ ባይሆን ግለሰቦችን በመግደል በአጭር ጊዜ በሽብርተኝነት ይህን መንግሥት ለመጣል የሚፈልጉ ነበሩ፡፡

ከዚህ በመወላወልና በቀውስ ውስጥ ከሚገኘው የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲ ማርክስና ኤንገልስ ትክክለኛውን የትግል ታክቲክ ቀየሱ፡፡ ማርክስና ኤንገልስ ሕጋዊና ሕገወጥ የትግል ዘዴዎችን በማዋሃድ በሕገወጥ መንገድ ጽሑፎችን በማተም አባሎችንና ሕዝቡን ማዘጋጀት አለበት አሉ፡፡

የዙሪክ ትሪዮ ማለትም የቀኝ አድርባዮች አደገኛ መሆናቸውን በመገንዘብ በ1879 ማርክስና ኤንገልስ እነዚህን ኃይሎች መታገል ጀመሩ፡፡ የወዝ አደሩ መደብ ነፃ መውጣት የወዝ አደሩ ሥራ እንደሆነ ገለጹ፡፡ ማርክስና ኤንገልስ የቀኝ አድርባዮችን ቢቃወሙ የ "ግራ" አድርባዮችንም ተቃውመው ነበር፡፡ ሞስት የተባለው የ "ግራ" አድርባይ በ1879 ላይ አዲስ ፓርቲ እንዲቋቋም ጥሪ አደረገ፡፡በ1880 በድብቅ የተሰበሰበው የሶሻል ዴሞ ክራቲክ ፓርቲ በጉባኤ ፕሮግራም ላይ የሰፈረውን የፓርቲውን አላማ ከግቡ ለማድረስ "በሁ ሉም ሕጋዊ መንገድ" የሚለውን አድርባይ አቋም "በሁሉም መንገድ" በሚለው ቀየረ፡፡ ሞስት በ "ግራ" አድርባይነቱ ከፓርቲው ተባረረ፡፡ እነ በርንስታይንም ተወገዙ፡፡

<u>ማርክስና ኤንገልስ በፈረንሳይ በእንግሊዝና በሌሎችም የወዝአደር ፓርቲዎች የአድርባዮችን መስመር እንዴት እንደታገሉ፡፡</u>

<u>የፈረንሳይ የወዝአደር ፓርቲ</u> ፡- የፓሪስ ኮምዩን በወደቀ በአምስተኛው ዓመት የፈረንሳይ ሶሻሊስቶች ለትግል መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡ በ1875 ገደማ ላይ እነ ላፋርግ እና ጁሊየስ ጉየስድ የንዑስ ከበርቴ ደጋፊዎችንና አናርኪስቶችን መታገል ጀመሩ፡፡ በ1879 ላይ የመጀመሪያው የፈረንሳይ የወዝአደር ፓርቲ በማርሴል ተመሰረተ፡፡ ማርክስና ኤንገልስ በ1880 ላይ በፓርቲው ረቂቅ ፕሮግራም ላይ በቀጥታ ተሳተፉ፡፡ ፓርቲው በተቋ ቋመ በአጭር ጊዜ ውስጥ በማሎንና በብሩሲ የሚመራው የቀኝ አድርባይ መስመር ብቅ አለ፡፡ ይህ ክንፍ በፕሮግራሙ ላይ የተቀበለውን የኮሙኒዝምን ሕብረተሰብ መመስረት መቃወም ጀመረ፡፡ የወዝአደሩን አምባገነንነት በመቃወም ወዝአደሩ በቡርዧዊ ሕብረተሰብ ውስጥ ሊያገኝ የሚችለውን መሻሻል አለበት እንጂ ለሥልጣን መንግሥት መታገል የለበትም የሚል አቋም ነበራ ቸው፡፡ እነዚህ አድርባዮች በዚህ አቋማቸው 'ፖሲቢሊስት' በመባል የሚታወቁት ናቸው፡፡

በተለያየ አካባቢ የሚገኙትን የወዛአደሩን ድርጅቶች በሚመለከተው የፓርቲው ፕሮግራም የሚለውን መከተል ባይሆን ለየአካባቢያቸው ተስማሚ ደንብ ያውጡ በማለት የድርጅቱን መፈረካከስ ይደግፉ ነበር።

በሁለቱ መስመሮች መካከል ይካሄድ በነበረው ትግል ምክንያት በ1882 በቅዱስ ኢትየን በተደረገው ስብሰባ ድርጅቱ በጉዌሲስቶችና በፖሲቢሊስት ተከፈለ። ፖሲቢሊስቶች ባደረጉት አሻጥር በቁጥር ይበዙ ነበር። ስለዚህ ጉዌሲስቶች ጉባዔያቸውን በሩዋን አካሄደው የፓርቲውን ስምና ፕሮግራም ይዘው ቀሩ። በማሉንና በብሩስ የሚመራው የቀኝ አድርባዩ ክንፍ የፓርቲውን ስም "አብዮታዊ የሶሻሊስት ወዛአደር ፓርቲ" በማለት ሲቀይር የወዛአደሩን አብዮታዊ ፕሪንስፕሎች አርገፍ አድርገው ጥለውት ነበር።

የ<u>እንግሊዝ የሪፎርም ማሕበር ፌቢየር</u>:— ይህ ማሕበር በ1884 በለንደን በከበርቴ ጋበ በተመረዙ ቡድኖች የተቋቋመ የከበርቴዎች "ሶሻሊስት" ድርጅት ነበር። ፌቢየር የሚለው ቃል የመጣው ፌቢየር ከሚባል ከክርስቶስ በፊት በሦስተኛው ዓመተ ዓለም የሮም የጦር ፊታውራሪ ከነበረ ሰው ስም ነው። ይህ ሰው በጦርነት ጊዜ የመጨረሻውን ፍልሚያ የሚሸሽና ቢቻለው ለማስተረት የሚቀጥር የጦር አለቃ ነበር። ይህ ድርጅት ስሙ እንደሚያመለክተው በወዛአደሩና በበርቴው መካከል የሚደረገውን የመጨረሻውን ትግል የሚፈራ ድርጅት ነበር። ለአነስተኛ ቅናሾች የሚተጋ ድርጅት ነበር። በሶሻሊዝምም ቀስ በቀስ በተመረጡ የአካባቢ ተወካዮች በስራ ላይ ይውላል ብሎ ተስፋ የሚያደርግ ድርጅት ነበር።

ኢንገልስ በዚህ ድርጅት ላይ በጻፈው ብዙ ትችቶች የተነሳ የድርጅቱ ተከታዮች በቁጥር እያነሱ ለመሄድ ችለዋል። በዚህም ጊዜ የእንግሊዙን የሶሻል ዴሞክራቲክ ፌዴሬሽንና የአሜሪካን ሶሻሊስቶች ጭምር አቀርበውቸው ነበር። ማርክስና ኢንገልስም አድርባዮችን በመታገል ማርክሲዝምን በሰፊው ለማስፋፋት ቻሉ።

በማርች 14/1883 ታላቁ የወዛአደር አብዮታዊ መሪና የሳይንሳዊ ሶሻሊዝም መስራች ካርል ማርክስ በተወለደ በ65 ዓመቱ በሚሰራበት ወንበሩ ላይ እንዳለ አረፈ። በማርች 17 1883 የብዙ አገር ወዛአደር መሪዎች በተገኙበት በትልቅ ስነስርአት በለንደን ከተማ ተቀበረ።

የዓለም ዓቀፍ ወዛአደሮችን የመምራት ኃላፊነት በኢንገልስ ጫንቃ ላይ ይወድቃል። ወደ 1880 መጨረሻ ላይ የጀርመኑ ሶሻል ዴሞክራትና የፈረንሳይ ጉዌሲስቶች የዓለም ዓቀፍ ሶሻሊስቶች ጉባዔ እንዲጠራ ኃይል ያቀርባሉ። የፈረንሳይ ፖሲቢሊስቶች፣ የእንግሊዙ ትሬድ ዩኒየኖችና አናርኪስቶች የዓለም ዓቀፉን አመራር ለመተካት አንድነት ይፈጥራሉ።

ዓለም ዓቀፍን በሚመለከተው ሁለት መስመሮች ይነሳሉ። አንደኛው የሪፎርም መንገድ የሚከተሉ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በማርክሲዝም ላይ የተመሰረተው ነበር። ኢንገልስ በዚህ ትግል አንደገለማባ ይሳተፍበታል። ሆኖም ሊብክነሽት፣ ቤበል፣ ላፋርግ፣ ክላራ ዜትኪንና እንደነዚህ ሌሎች በተገኙበት በጀርመን አገር በሃሌ ከተማ ማኅበራት ጉባዔ ያካሂዳል። በ1889 ሁለቱም በፓሪስ ከተማ በተለያየ ቦታ ጉባዔ ያካሂዳሉ። በቀኞቹ ጉባዔ ላይ ከዘጠኝ አገር የመጡ የሰባ የሙያ ማሕበራት ወኪሎች ብቻ ሲገኙ በአብዮተኞቹ የሶሻሊስት ጉባዔ ላይ ግን ከ22 የአውሮፓ አገሮች የመጡ 393 የወዛአደር ወኪሎች ተገኝተው ነበር። ይህ ጉባዔ ቢሆንም ሊብክነሽ



ትን በሊቀመንበርነት መረጠ። ቤበል፣ ቫይላንትና ላፋርግና የቀኞቹ በስራ አስኪያጅ ኮሚቴ ውስጥ ተመረጡ። የሁለተኛ ዓለም አቀፍ መመስረቱን ጉባዔው አስታወቀ። እዚሁ ላይ ለማስታወስ ያህል በጉባዔው መጀመሪያ ላይ አንዳንድ ተካፋዮች ዓለም ዓቀፍ ድርጅት እንዲኖር ከአድርባዮቹ ፖሲቢሊስቶች ጋር አንድነት መፍጠር አለብን በማለት አስቸግረው ነበር። በጉባዔው ላይ በተደረገው የሁለት መስመር ትግል አንድነት ብቻ ይፈልጋል በማለት የተለያዩ አይነት ሃሳቦችን በበሰበ ዓለም ዓቀፍ ድርጅት መመስረት ስህተት እንደሆነ በማስረዳት የነውሌ ያም ሊብክነሽት ወገኖች ይህን ጥያቄ ያነሱትን ረቱ።

የፓሪሱ ሁለተኛው ዓለም ዓቀፍ ጉባዔ . በሜይ አንድ 1886 የቺካጎ ወዛአደሮች ለስምንት ሰዓት የሥራ ቀን ሳደረጉት ተጋድሎ ማስታወሻ ይሆን ዘንድ የዓለም ወዛአደሮች ከዚያን ዓመት ጀምሮ ሜይ አንድን በሰላማዊ ሰልፍ እንዲያከብሩ ወሰነ። ለመጀመሪያም ጊዜ በ1890 ሜይ አንድ በእንግሊዝ፣ በጀርመን፣ በኦስትሪያ፣ በቤልጅግ፣ በስዊዲን፣ በኖርዌይና በአሜሪካ በደመቀ ትልቅ ሰላማዊ ሰልፍ ተከበረ። ኢንገልስም በ70 ዓመት እድሜው በእንግሊዝ አገር በለንደን ከተማ ከወዛአደሮች ጋር አብሮ ተሰለፈ።

<u>ኢንገልስ በሁለተኛው ዓለም ዓቀፍ ውስጥ የ"ግራ" እና የቀኝ አድርባዮችን እንዴት እንደተዋጋ</u>

በብራሰልስ 1891 ና በዙሪክ በ1893 በተደረጉት ሁለት የዓለም ዓቀፍ ጉባዔዎች ላይ ዋናው አጀንዳና አነጋጋሪ ጥያቄ የአናርኪስቶች ጥያቄ ነበር። የፈረንሳዩ የወዛአደር ማሕበር፣ "ወጣት" በመባል የታወቀው የጀርመኑ ድርጅትና በሆላንድ፣ በኦስትሪያ፣ በስፔንና በስም የሚገኙት አናርኪስቶች ይገኙበት ነበር። እነዚህ የአናርኪስት ድርጅቶች "ነፃነት ለሁሉም፣ ወዛአደሩ ፓርቲ አያስፈልገውም፣ የወዛአደሩ አምባገነን መንግሥት አያስፈልገውም፣" በማለት ማርክሲዝምን ሲቃወሙ ነበር። በሕጋዊ የትግል መድረክ አንሳተፍም፣ በፓርላማ ትግል ውስጥ አንካፈልም፣ የኢኮኖሚ ትግል ማድረግ አያስፈልግም፣ አብዮት አሁኑኑ...ወዘተ በማለት ዓለም ዓቀፍ ድርጅቱን ለማናጋት ተነሱ። በ1896 በለንደን ከተማ የተደረገው የዓለም አቀፍ ጉባዔ ላይ* ዱሬ ተመታ ሆኖም ግን ዓለም ዓቀፍ የ"ግራ" አድርባይነትን በሚታገልበት ወቅት የቀኝ አድርባይነት በዓለም ዓቀፍ ውስጥ በቀ እያሰና እየተጠናከረ ይመጣል። ቀኝ አድርባዮች በሕጋዊ ሥራ ላይ በመሳተፋቸው ይህ የትግል ዘዴ በጣም አድርጎ ማረካቸው። በፓርላማ ትግል ውስጥም በመሳተፋቸው ፍላጎታቸው ብዙ ድምጽ ለማግኘት ብቻ ሆነ። ሕገወጥ ትግል አደገኛ ነውና አያዋጣም በማለት ከቀን ወደ ቀን እየተገሸራተቱ ከዱሃሬው በፊር መደገፍ ጀመሩ። ኢንገልስ የወዛአደሩን አብዮት ለማካሄድና የወዛአደሩን አምባገነንነት ለመመስረት ወዛአደሩ መበረተ ኃይሎች መሸር የለባቸውም በማለት እነዚህን የቀኝ አድርባዮች መታገል ጀመረ። በዚህም ትግሉ ሁለተኛ ዓለም ዓቀፍን ከቀኝ አድርባዮች ለማዳን ተችሏል።

በ1890 ቢስማርክ በገዛ እጁ ከስልጣን እንደወረደ "የሶሻሊስት ሕግ" በመባል የሚታወቀው አዋጅ በወዛአደሩ ትግል ሊነሳ ቻለ። የጀርመን መደብም አንዳንድ የቀጥና ሰዎችን አደረገ። ለምሳሌ እሁድ የእረፍት ቀን ሆነ፣ ሕፃናት ስራ እንዳይሰሩና የወሊድ የእረፍት ጊዜ

*———
ኣናርኪዝም

በሕግ ተወሰነ፡፡ የጀርመኑ የወዝአደር ፓርቲ በዚህን ጊዜ የትግል ስልቱን ቀየረ፡፡ በዚያውም ወቅት ይህ ሁኔታ ለቀኝና ለ"ግራ" አድርባዮች በፓርቲው ውስጥ መፈልፈል ምክንያት ሆነ፡፡

የ"ግራ" አድርባዮች፡- በጀርመኑ የሶሻል ዴሞክራት ፓርቲ ውስጥ የ"ግራ" አድርባይ ክንፍ "ወጣት" በመባል የሚታወቁት ነበሩ፡፡ እነ ዚሁ "ወጣት" የሚባሉት ተማሪዎችና አንዳንድ ትምህርታቸውን ጨርሰው አናውቃለን በማለት አፈጣቸውን የወዝአደሩ መሪ ያደረጉ ቡድኖች ናቸው፡፡ እነዚሁም አድርባዮች በማርክስና በኤንግልስ ስም በመማልና በመገዘት ሕጋዊ ስራን ያጣጣሉና ትግላቸውን በሕገወጥ ስራ ላይ ብቻ ያተኩሩ ነበሩ፡፡ ኤንግልስ እነዚህን "ወጣቶች" ካጋለጠ በኋላ አንዳንዶቹን ወደ ትክክለኛው የፖለቲካ መስመር ሲመልስ የተቀሩት በ"ግራ" አድርባይነት አቋማቸው በመቀረታቸው ከፓርቲው እንዲባረሩ ተደረገ፡፡

የቀኝ አድርባዮች፡- በጀርመን ሶሻል ዴሞክራት ፓርቲ ውስጥ የቀኝ አድርባይ የፖለቲካ መስመር አራማጁ በቮልመር የሚመራው ክንፍ ነበር፡፡ ቮልመር ከገጠሩ ሕዝብ በተገኙት አንዳንድ የቀኝ ሰዎች በመማረክ "የገጠሩ ሕዝብ ከዛሬ ጀምሮ የወዝአደሩ ወዳጅ ነው፡፡" "የገጠሩ ሕዝብ የሰራውን ሐብት ተቀም ከአንገቱ ይወስዳል፡፡" ስለዚህም የወዝአደሩ ፓርቲ ይህን የገጠሩን ሕዝብ መሬት ፈቃዱ አንድ አዛዡን መቀበል አለበት በማለት ጭልጥ ያለ የአድርባይ መስመሩን ማስተጋባት ጀመረ፡፡ ወዝአደሩ አብዮት ማድረግ የለበትም፤ ሁሉንም ነገር በሰላማዊ የፓርላማ ትግል ብቻ እናገኛለን በማለት ፀረ-ወዝአደር አቋም ያዘ፡፡

ኤንግልስም በጀርመን የወዝአደር ፓርቲ ውስጥ የተነሱትን አድርባዮች ለመዋጋት በመጀመሪያ የጎታ ፕሮግራም ትችት በይፋ እንዲወጣ ያደርጋል፡፡ ሁለተኛም በ1891 ላይ የ20ኛውን ዓመት የፓሪስ ኮሙን ምክንያት በማድረግ "የእርስ በርስ ጦርነት በፈረንሳይ አገር" የሚለውን ጽሑፍ መግቢያውን በመጻፍ እንዲታተም ያደርጋል፡፡ እነዚህ ጽሑፎች ለአድርባዮች ትልቅ ጥንቃቄን ፈጠሩ፡፡ በመጨረሻም ኤንግልስ የወዝአደሩን አምባገነንነትና አብዮታዊ አመራር መሰረት በማድረግ "የሶሻል ዴሞክራት ንድፍ ፕሮግራም ላይ የቀረበ ትችት" የሚል ጽሑፍና "የገበሬ ጥያቄ በፈረንሳይና በጀርመን" በሚል መጽሐፍ ላይ አድርባዮችን ይመታል፡፡ ኤንግልስም በዚህ አይነት ትግል ሁለተኛው ዓለም አቀፍን አድርባዮች በተቆጣጠሩት ሥር እንዳያደርጉትና ወዝአደሩንም እንዳያባስቱ ነቅቶ በመታገል ላይ እንዳለ በኦገስት 5/1895 በጉሮሮ ነቀርሳ ታሞ ይሞታል፡፡ አስከሬኑም በኑዛዜው መሰረት ብዙ የወዝአደር መሪዎች በተገኙበት ተቃጥሎ አመዱ በሕይወቱ በነበረበት ጊዜ ያርፍበት በነበረው ኢስት ቦርን በሚባል እንግሊዝ አገር በሚገኝ አነስተኛ መንደር አካባቢ በሚገኘው ባሕር ላይ ተበተነ፡፡



በማርክሲዝምና በከሳቦችና በአድርባዮች መካከል ከተደረገው ትግል አንዱ ትልቁን ስፍራ የያዘው በሌኒን የተካሄደው ነበር፡፡ ሌኒን የከሳቦችና የአድርባዮች በወዝአደሩ ንቅናቄ ውስጥ መገባት ድንገተኛ እንዳልሆነ ከማብራራትም በላይ ከሳብና አድርባይነት የካፒታሊስት ስርአት ፍሬዎች የከበርቴው ፖሊሲ መሆናቸውን አረጋገጠ፡፡ የከሳቦችንና የአድርባዮችን መደባዊ መሰረትና በሕብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ስፍራ ለማብራራትና እነዚህን ኃይሎች ለማጋለጥ ብዙ ጽሑፎችን ጽፏል፤

ከፓሪስ ኮሙን 1871 መውደቅ በኋላ ካፒታሊዝም በ"ሠላማዊ" እድገት እየዳበረ ብዙ ዘመናትን ካሳለፈ በኋላ በ20ኛው ክፍለ ዘመን የካፒታሊዝም እድገት ወደ ኢምፔሪያሊዝምነት ተቀየረ፡ ከበርቴው ከሚያገኘው የናጠጠ ትርፍ የወዝአደሮችን መሪዎች በስጦታና በጉቦ በመያዝ የሌበር አሪስቶክራሲውን መሠረተ፡፡ ከዚህም በመነሳት አድርባዮች በህብረተሰብ ውስጥ መሠረታቸውን ጣሉ፡፡

በዚህም ጊዜ የካፒታሊዝም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ፍጥነት ማደግ ወዝአደሩ በንዑስ-ከበርቴው ርዕዮተዓለም እንዲበከል ከማድረጉም በላይ ብዙዎችን ገበሬዎችን የእጅ ጥበብ ሠራተኞች እንደሁም በዚ ያሉ ሰዎች የንዑስ-ከበርቴ ክፍሎች በዚህ ርዕዮተዓለም እንዲበከሉ ሁኔታው አስገደዷቸዋል፡፡

እንደሚገነዘቡት የበዝባዥ መደብ ከበርቴው ስልጣኑን ለማጠናከርና እድሜውን ለማራዘም ሲል በማጣመር ወይም በተናጠል ከተበዝባዥ መደቦች ጋር ሙሉ የሚያደርግበትን ሁለት ታክቲኮች ተጠቀመ፡ ይኸውም አንደኛው ካለአንዳች ስምምነት ወዝአደሩን መጨፍጨፍ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ አንዳንድ ስምምነቶችን በማድረግ ወዝአደሩን መደለል ነው፡፡ ካፒታሊዝም በመጠኑ ማደግ በጀመረበት ወቅትም ቢሆን ከበርቴው እንደ ጦር ሥራው አድርጎ የያዘው የወዝአደሩን አብዮታዊ ፍላጎት አንዳንድ አነስተኛ ተገናታችን አበቃፊ በሆኑ ስምምነቶች በማድረግ ንቅናቄያቸውን ማጨናገፍ ነበር፡፡ ይህ ድርጊት "የከበርቴ ፓርላማንታሪና" "የከበርቴ ጠጋኝነት" የሚባለውን በብዙ የሠራተኛው ንቅናቄው መሪዎች ውስጥ እንዲፈጠር ምክንያት ሆኖ ተስፋፋ፡፡ በዚህም ጊዜ የወዝአደሩን አብዮታዊ ስሜት ለመግደብ ብዙ ታች የንዑስ-ከበርቴ ምሁራን መንገዳቸውን ወደ ወዝአደሩ ንቅናቄ አመሩ፡፡

ከሳቦችና አድርባዮች ጠቃሳሳውንና አብዮታዊውን የማርክስን ትምህርቶች ጊዜ በመበረዝ ለከበርቴው ጥቅም እንዲውል ለከበርቴው አስተሳሰብ በር ይከፍትላታል፡፡ የካፒታሊስት ስርዓቱ ተውስ ቢኖርም ቀሉ ይህ ተውሶ ሊወሩ ይችላል በሚል አስተሳሰባቸው የካፒታሊዝምን መውደቅ በተቀታ ይቃወማሉ፡፡ የወዝአደሩንም የመደብ ትግል በመካድ ከከበርቴው ጋር ወዝአደሩ እርቅ እንዲፈጥር ይታገላሉ፡፡ ከዚያም አልፈው በሰላማዊ መንገድ የመደብ ትግል ባይካሄድ ከካፒታሊዝም ወደሶሻሊዝም መሸጋገር ይቻላል በማለት ጠቃሳሳውን የወዝአደሩን አምባገነንነት በጥብቅ ይቃወማሉ፡፡

በአጭሩ እነዚህ የከበርቴውን ርዕዮተዓለም ተሸክመው በወዝአደሩ ንቅናቄ ውስጥ የሚገቡ መኪናዎች ከመሆናቸውም በላይ በወዝአደሩ ንቅናቄ ውስጥ የከበርቴው ወኪሎች ናቸው፡፡ እንደነዚህ ዓይነቶቹ ከወዝአደሩ አብዮትና ጥቅም ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የሌላቸው ናቸው፡፡ ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በፊት ከሳቦችና አድርባዮች በሠራተኛው መደብ ንቅናቄ ውስጥና በወዝአደሩ ፓርቲ ውስጥ ሆነው በፊትን ሕዝብ ከአብዮታዊው መንገድ በማስለስ ከወገኑ ከአብዮታዊው ጦርነት መከላከል ጀመሩ፡፡ በጦርነቱም ጊዜ ሶሻል ሾቪኒስት / የተፈጠረ ካባ የለበሱ የብሔር ትምክህተኞች/በመሆን

ካፒታሊስቶች ለዘረፋና ዓለምን ለመከፋፈል የተነሡበትን ወርነት ደገፉ። ከታላቁ የኦክቶበር አብዮት በኋላ ቦልሼቪክን ከመቃወም በበለጠ ከመደብ ጠላቶቻቸው ጋራ በሶቪየት መንግሥት ላይ ትልቅ አሻጥር በማድረግ፣ በጀርመኒ፣ በሀንጋሪና በሌሎችም አገሮች የነበሩትን አብዮቶች በመክዳት የተ ተኛ የከበርቴው ገልጽ ወዳጆች በመሆን በይፋ የፀረ አብዮትና አድኃሪነት ወሳኞች ሆኑ።

በከሓዲዎችና በአድርባዮች ፖሊሲ በሠራተኛው መደብ ንቅናቄ ውስጥ የገባው አቋም በተ ሳሉ የሚታዩ አይደሉም። እነዚያም ተያይዞ /ለማርክሲዝም ለአብዮትና ለቦልሼቪዝም መቆም ወይም በተፃራሪው ለከበርቴው ርእዮተ አለም መንበርከክ/ በአንደኛ ደረጃ የሚቀርብ ነው።

ወዝአደሩን አዘጋጅቶ ለድል ለማብቃት በጣም አስፈላጊ ከሆኑት ሁኔታዎች ውስጥ በጣም ፈረጅምና በለማወላወል ያለርህራሄ አድርባዮችን፣ ወጋኞችን፣ ቦሹ ሾቪኒስቶችን፣ ከሓዲዎችንና የመ ባበሉትን የከበርቴውን ተጽእኖዎችንና ዝንባሌዎች መዋጋት ነው።

ሌኒን የዲያሌክቲካል የታሪካዊ ቁስ አካልነትን ትክክለኛነት በማሳየትና በማረጋገጥ የተለያዩ ገጽ ያላቸውን ጠቅላላውን የአይዲያሊስትና የሜታፊዚክስን ዝንባሌዎች ስህተተኛነት አሳ ይቷል። የማርክሲስትን የፖለቲካል ኢኮኖሚን መሰረት በማድረግ ታሪካዊ ሁኔታ በፈቀደለት በኢ ምፔሪያሊዝም ዘመን የኢምፔሪያሊዝምን ቲዮሪ ከመመስረቱም በላይ ጭምር ለኢኮኖሚ ዕድገቱ ሊያወላ ዳው በማይችለው ሁኔታ እውነተኛውን የወዝአደሩን አብዮትና የወዝአደሩን አምባገነንነት በማያወላ ዳ ሁኔታ አስፈረ። ኢምፔሪያሊዝም ጥገኛ፣ የበሰበሰና የሞተ ካፒታሊዝም መሆኑን፣ ኢም ፔሪያሊዝም ዋዜማ የወዝአደሩ አብዮት ዘመን እንደሆነና በኢምፔሪያሊዝም ዘመን ኢምፔሪያሊስቶች አለምን ለመከፋፈል በሚያደርጉት እሽቅድድም /ለገበያ፣ ለጥሬ እቃና ለርካሽ ጉልበት ...ወዘተ በሚያደርጉት ፉክክር/ በመሀከላቸው ወርነት እንደሚቀሰቅሱ፣ ቦልሼቪዝም በኢምፔሪያሊዝም መሀከል ያለ ውን ደካማ ሰንሰለት በመበጠስ ሊፈነዳ እንደሚችል በማሳየት በወዝአደሩ አብዮት ውስጥ መሰረታዊ ጥያቄ የሆነውን የከበርቴውን የመንግሥት መኪናዎች /ስቴት ማሽነሪ/ መሰባበርና የወዝአደሩን አም ባገነንነት መገንባት፣ አብዮት ድልን እንዲቀዳጅ ወዝአደሩ የወዝአደሩንና የገበሬውን አንድነት መመስረት እንዳለበት፣ ይህም አንድነት በተለያዩ ጊዜያት የተለያዩ ቅርፅ እንደሚኖረውና በዚህም አኳያ በቅኝ ገዢዎችና በጥገኛ አገሮች ውስጥ ለብሔራዊ ነፃነት ትግል ከሚያደርጉ ኃይሎች ጋር ሳጋራ ትግል ማለትም ኢምፔሪያሊዝምን ለመዋጋት አንድነት መፍጠር፣ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በሚደረገው የሽግግር ጊዜ ውስጥ የወዝ አደሩ አምባገነንነት እንደበረታ መጠንከር፣ ኢንዱስትሪ ያላይዜሽንና ኮሌክቲቪዜሽን በሥራ ላይ መዋል በጣም አስፈላጊ እንደሆኑና በዚሁም ባሳነበ ሁኔታ የካፒታሊስት ርዝራዦችንና የከበርቴውን ተጽእኖ ካለማወላወል በረጅም ትግል መታገል እንደሚያስ ፈልግ አስረዳ። እነዚህ ከላይ የተጠቀሱት በሥራ ላይ ከዋሉ ሶሻሊዝምን ገንብቶ ወደ ኮሚኒዝም መሸጋገር እንደሚቻል አሳየ። ለዚህም በመጀመሪያ ደረጃ ወዝአደሩ ከአድርባዮች ነፃ የሆነ የራሱን እውነተኛ ማርክሲስት—ሌኒኒስት አብዮታዊ ፓርቲና የወዝአደሩን አምባገነንነት መመስረት አለበት።

ሌኒንም አዲስ የሆነና ከሌሎች የተለየ አድርባዮችን የጸዳ ፓርቲ የቦልሼቪክ ፓርቲን መሰረተ። የቦልሼቪክ ፓርቲ በሌኒን በመሪነት በሩሲያ አብዮት ውስጥ ያደገና የጎለመሰ ካወሰ



ዋና ከውድ ከሓዲዎችና አድርባዮች ጋር የታገለ፣ በመጨረሻም በኦክቶበር አብዮት ትልቅ ድልን የተጎናፀፈና በዓለም ውስጥ የመጀመሪያውን የሶሻሊስት አገር የገነባ ነው። ታሪኩ እንዲህ ባጭሩ ሲቀርብ የወዝአደር ፓርቲ የመፍጠርና ይህም ፓርቲ ድልን ተጎናጽፎ አዲሲቱን ሕብረተሰብ የመገን ባት ጉዳይ ቀላል ይመስል ይሆናል። ነገር ግን አይደለም።

ሌኒን በአብዮት መሪነት ሲሰማራ የሩሲያ ሰፊ ሕዝብ በዛሩ መንግሥት በጣም አስከፊ ጭቆ ናና በዝበዛ ላይ ከመገኘቱም ሌላ ሰፊው ሕዝብ ወርቦ የፖለቲካ መብቶች አልነበሩትም የካፒታሊዝም መጎልበት ወዝአደሩን በተደራጀ ሁኔታ ሰፊ የስራ ማቆም አድማዎችን እንዲያካሂድ ረዳው። ከዚህም አልፎ የማርክሲስት የጥናት ክበቦች ተመስርተው ማርክሲዝም መስፋፋት ጀመረ። ምንም እንኳን እነዚህ የማሌ ድርጅቶች የፕሮፓጋንዳና የአጅቴሽን ስራዎች ቢያካሂዱም ቅሉ ከሰፊው ሕዝብ ውስጥ የመግባት አቅማቸው በጣም የመነመነ ነበር። ይህንን በመገንዘብ የሩሲያ ማሌዎች አንደኛና አጣዳፊ ተግባራቸው አድርገው የወሰዱት የተበታተኑትን የማሌ ድርጅቶች አንድ ላይ መሰ ብሰብና አንድ የወዝአደር ፓርቲ መመስረት ሲሆን ከዚህ በፊት ግን ሶሻሊዝምን ከወዝአደሩ ጋር ማዋሃዱን ነበር። በሌላ አነጋገር ወዝአደሩን ማንቃት ነበር ማለት ነው። የሚተጣለው አርዕስት ወዝአደሩን መርተው የዛሩን አፍርሶ ከደመሰሱ በኋላ የሶሻሊስት አብዮትን ማካሄድ ሶሻሊዝ ምን መመስረት ነበር።

በዚያን ጊዜ ከነበሩት የሩሲያ ማርክሲስቶች ውስጥ ይህ ታሪካዊ ተግባር በገልጽ የገባውና አስከመጨረሻው የታገለው ሌኒን ነበር። በ1894 '' What the"friends of the pepole"are and how they fight the social-democrats '' የሚለውን ጽሑፉን ሲጽፍ እንዲህ ብሎ ነበር—

'' When its advanced representatives have mastered the ideas of scientific socialism, the idea of the historical role of the Russian worker, when these ideas become widespread, and when stable organizations are formed among the workers to transform the workers' present sporadic economic wa into conscious class struggle-then the Russian **WORKER**,rising at the head of all the democratic elements, will overthrow absolutism and lead the **RUSSIAN PROLETARIAT** (side by side with the proletariat of **ALL COUNTRIES**) along the straight road of open political struggle to **THE VICTORIOUS COMMUNIST REVOLUTION.** ''

(Lenin CW Moscow Vol. 1, P. 300)

እንግዲህ ሌኒን ለሩሲያ ወዝአደሮችና ማሌዎች ትክክልና ገልጽ በሆነ መንገድ ይህን ከዚህ በላይ ያቀረብነውን ስትራቴጂ አብዮታዊ ተግባር አቀረበ። ይሄንንም በተግባር ለመተርጎምና ከፀረ— ማርክሲስት ኃይሎች ጋር የመረረ ትግል በሚያካሂዱበት ጊዜ ይህ አብዮታዊ ስትራቴጂ ተግባር በስራ እንዳይተረጎም የቆየ የሽርክ ትግሎችን ከአኪኖች ፀረ—ማርክሲስት ኃይሎች ውስጥ አንዱ ናሮ ድኒዝም የሚባለው ድርጅት ነበር። ይህም ድርጅት በተለይ የወዝአደሩ ፓርቲ እንዳይመሰረት አስከመጨረሻ ው የሚታገል ነበር። ናሮድኒዝም ፀረ—ማርክሲስት መሆኑን በሩሲያ ውስጥ ካፒታሊዝም ሊያድግ አይችልም ይል ነበር። ናሮድኒዞች የሩሲያን ገበሬ የተደራጀ ትግል ችላ በማለት እየገለፀ የሰፊውን ሕዝብ አደራ አብዮታዊ ወደ ቡርዣ አይችልም በማለት አብዮታዊ ንቅናቄን በማስጠንቀቅ ይቀበሉ ነበር። ለት በአንዳንድ በተናጠል በሽብርተኝነትና በአጋፋጭ በተግባር ትግል አንዲሁም ይበላሉ ነበር። ምንም እንኳን ማሌዎችና ጀማሪዎች ቢኖሩ ለበር ገሬዎች በለማድረግ ናሮድኒዝምን በርእዮተ አለም ደረጃ በመቃወም ገና ወርቦ አልተደመሰሰም ነበር። የዚህ ተግባር የወደቀው በሌኒን ላይ ነበር።

የተቀረው የሶሻሊዝም ኢኮኖሚ መገንባት በስታሊንና የሊኒን ፖለቲካ በሚከተሉ ማርክሲስቶች ትከሻ ላይ ወደቀ:: ትሮትስኪና ሌሎች ኦፖዚሽን ነሩፖች የኢኮኖሚ ቀውሱን ሁኔታና የሌኒን ህመም አመቺ ጊዜ በመጠቀም የ46 ኦፖዚሽንስት ፕላት ፎርም ይዘው ቀረቡ:: ይህ ፕላት ፎርም በሶቭየት ህብረት ትልቅ የኢኮኖሚ ቀውስ እንዳለና ከዚህም የተነሳ የሶቭየት መንግሥት ተንኮታኩቶ እንደሚወድቅ አመለከተ:: ከዚህም ሁኔታ ለመውጣት ለከፋፋዮችና ለነሩፖች እንዲደረጅ ነፃነት ይሰጥ የሚል ፀረ—ወዝአደርና ፀረ—ማርክሲስት ሃሳብ ይዘው ቀረቡ:: በ1924 ዓ.ም በፓርቲው 13ኛ ጉባኤ ላይ የ46 ኦፖዚሽኖች ፕላት ፎርም ፀረ—ማርክሲስትና የንዑስ ከበርቴው ከማርክሲዝም መሠረታዊ ሃሳቦች የመንሸራተት አዝማሚያ መሆኑን በማሳየት በርእዮተአለም ደረጃ ከለርሁሬ መዋጋት እንደሚያስፈልግ ጉባኤው ወሰነ:: ይህንን የ13ኛውን የሶቭየት ዩኒየን ኮሙኒስት ፓርቲ ውሳኔ 5ኛው የኮሙኒስት ኢንተርናሽናል ጉባኤ ሙሉ በሙሉ በመደገፍ ትሮትስኪይዝም በርእዮተ ዓለም መመታት ያለበት መሆኑን አረጋገጠ:: ነገር ግን ትሮትስኪና ሌሎች አድርባዮች ፀረ—አብዮት ሥራቸውን በመቀጠል የወዝአደሩን ፓርቲ ለማዳከም በየጊዜው ይጣጣሩ ነበር:: ትሮትስኪ መሪ በመሆን ''ዘ ሌሰን ኦፍ ዘ ኦክቶበር'' የሚል ሌኒን ለሶቭየት ዩኒየን ያደረጋቸውን ረጅም አብዮታዊ ተጋድሎዎች ይቀይስ የነበራቸውን ታክቲክና ስትራተጂ የሚጻረር በአንጻሩም የሌኒን ቲዎሪ በትሮትስኪይዝም የሚተካና የቦልሸቪክን ታሪክ የሚያንኳስስ ጻፈ::

ስታሊን ይህንን ፀረ—ቦልሸቪክ ቲዎሪና የሌኒን ቲዎሪ ሥራዎች በትሮትስኪይዝም ለመተካት የተደረገውን ፀረ—ማርክሲስት አቋም የሚያንፀባርቅ ጽሑፍ ሌኒንዝምን በመከላከል ስራና ሳይንሳዊ የቲዎሪ ጽሑፍ ''የሌኒን መሠረተ ሃሳቦች'' የሚል በ1924 ዓ.ም አወጣ:: ይህ ጽሑፍ በአለም አቀፍ ደረጃ የማርክሲዝም ሌኒንዝም የወዝአደሩ የትግል መሣሪያ ነው፤ ማርክሲዝም ሌኒንዝም ለዘለዓለም ይኑር ብለው በዚህ ሰንደቅ ሥር የሚታገሉ ለወዝአደር ፓርቲዎች ትልቅ የቲዎሪ አስተዋጽኦ ሆነ:: ማርክሲዝም ሌኒንዝምን በትሮትስኪይዝም ለመተካት ባንዱ በኩል፤ ትሮትስኪይዝም ፀረ—ማርክሲስትና ፀረ—ቦልሼቪክ የሆነ የንዑስ ከበርቴው ዥንጉርጉር ርእዮተዓለም በሌላ በኩልና ይህን ርእዮዓለም ከወዝአደሩ እንቅስቃሴ ውስጥ ደብዛውን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ወቅት በጃኑዋሪ 24 1924 ዓ.ም ታላቁ ሌኒን ከዚህ ዓለም በሞት ተለየ:: ከዚህ ጊዜያት ጀምሮ ማርክሲዝም ሌኒንዝም በንዑስ ከበርቴው ርእዮተዓለም እንዳይበረዝና ሶሻሊዝምን በወዝአደሩና በገበሬው አንድነት በጠነከረ መሠረት ላይ በወዝአደሩ ፓርቲ መሪነት የመገንባቱ ጉዳይ በስታሊን ትከሻ ላይ ወደቀ::



ከ4 ዓመታት የአዲስ ኢኮኖሚ ፕላን ውጤት በኋላ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሠረት ተጣለ:: የኢንዱስትሪና የእርሻ ምርት በእጥፍ ጨመረ:: በፖለቲካ የወዝአደሩ አምባገነንነት፤ የወዝአደሩ አርሶአደሩ አንድነት መሠረት ያዘ:: ነገር ግን በተፋጠነ ሶቭየት ህብረትን በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ የተመሠረተ ኢንዱስትሪ መስፋፋት እንዳለበት ፓርቲው አሁንም ያቀን ተቀን ትግል እንደሚያስፈልግ ለዚህም ፕራክቲካል እቅዱ ማስፈለጉን አመለከተ:: ትሮትስኪና ሌሎች ኦፖዚሽን ክፍሎች ይህንን የፓርቲውን ፕላን በመቃወም የሶሻሊስት ኢኮኖሚን በሶቭየት ህብረት መገንባት የማይቻል ነው በማለት የወዝአደሩን ፓርቲ ሚና በመዘንጋት ከፓርቲው ጋር በተጻራሪ ተሰለፉ:: ትሮትስኪ ''ዘ ቲዎሪ ኦፍ ፐርመናንት ሪቮልሽን'' ከሚለው ከቀደመው ቲዎሪ በመነሳት ሶሻሊዝምን በሶቭየት ለመገንባት የሚቻለው በሌሎች አውሮፓ አገሮችም በአጠቃላይ ወይንም በአንድነት የሶሻሊስት አብዮት ከተደረገና እነዚህ ለእርዳታ ከመጡ ብቻ ነው በማለት ሰብጀክቲቭ አስተሳሰብ አቀረበ:: በዚህ የትሮትስኪ ቲዎሪ መሠረት የአብዮት ሃይል ወሳኞች (አብዮት ማድረግና የሶሻሊስት ኢኮኖሚን መገንባት) የውስጥ አብጀክቲቭና ሰብጀክቲቭ ሁኔታዎች መሟላት ሳይሆን ወሳኙ ሃይል፤ የውስጥ ሳይሆን የውጭ ሃይል ነው የሚል ፀረ—ማርክሲስት ፀረ—ወዝአደር ግምገማ ነው::

ቡካሪን ግን ከዚህ ለየት ባለ አቀራረብ ፓርቲውን ሙሉ በሙሉ እንደትሮትስኪና እንደሌሎቹ ኦፖዚሽኖች ባይቃወምም ቡርዣው በሰላም ከሶሻሊዝም ጋር በመሳመድ ያድጋል፤ ይህም ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ መገንባት ወሳኝ ነው በማለት በወዝአደሩና በቡርዣው መሀከል ያለውን የማይታረቅ ቅራኔ ጠበይ የሚሽር ቲዎሪ አቀረበ:: በቡካሪን አስተሳሰብ ቡርዣው የፖለቲካ ሥልጣኑንና ሀብቱን ከተነጠቀ በኋላ ከወዝአደሩ እጅ ሥልጣኑን ለመቀማት እንደገና የሚፈልግ ሳይሆን ከሱ ጋር በመሳመድ ያድጋል የሚል በሶሻሊዝም ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የመደብ ትግል የሚያዘነጋ ፀረ—ማርክሲስት ቲዎሪ ነው:: ይህም ሌላ ሳይሆን የወዝአደሩ አምባገነንነትን በቡርዣው ላይ ማስፈን የለበትም የሚል ለቡርዣው እንደገና መንሠራራት አመቺ ሁኔታን የሚፈጥር ስህተኛ ቲዎሪ ነው::

ዚኖቪየቭና ካሜኔቭ ሶቭየት ህብረት በቴክኒክ ወደኋላ የቀረች በኢኮኖሚ የቆረቆዘች ስለሆነች ሶሻሊዝምን ለመገንባት አይቻልም የሚል የወዝአደሩን ተልእኮና ሃላፊነት የሚጻረር ፀረ—ወዝአደር ቲዎሪ ሰነዘሩ:: ነገር ግን ስታሊንና ሌሎች ማርክሲስቶች ይህንን ፀረ—ወዝአደርና ፀረ—ማርክሲስት አቋም በማውገዝ ሶሻሊዝምን ለመገንባት አመቺ ሁኔታዎች እንዳሉ፤ የወዝአደሩ፤ አርሶአደሩ አንድነት በጠነከረ መሠረት ላይ እንዳለ፤ በሳይንሳዊ መንገድ በመተንተን ሌኒን ከዚህ በፊት ሶሻሊዝምን በአንድ አገርም መጀመሪያ

ለመገንባት ይቻላል ያለውን ቲዎሪ አረጋገጡ::

በ1925 ዓ.ም 14ኛው የፓርቲው ኮንግረስ ተካሄደ:: ከዚህ ፓርቲ ኮንግረስ ላይ ትሮትስኪይቶችና ቡካሪን የሚያስተጋቡትን ፀረ—ሶቪየት ፕሮፓጋንዳ፣ ሶሻሊዝምን ለመገንባት አይቻልም ብለው ያቀረቡትን ስህተተኛ ግምገማ አወገዘ:: በዚህም ኮንግረስ ሶሻሊዝም በአሸናፊነት ይወጣ ይችል ዘንድ ሶቪየት ህብረትን በፕላን ኢኮኖሚ መሠረት ኢንዱስትሪላይዝ (በኢንዱስትሪ መገንባት) ማድረግ መሀከለኛ ነጥብ መሆኑን ወሰነ::

ሆኖም ግን ዚኖቪቭና ተከታዮች ይህንን የፓርቲውን አጠቃላይ ፕላን በመቃወም በምትኩ የወዛአደሩን አርሶአደሩን መንግሥት የሚያዳክም፣ ሶቪየት ህብረትን በሌሎች አገሮች የኢኮኖሚ ጥገኛ የሚያደርጋት ሃሳብ አቀረቡ:: በዚህ ፕላን መሠረት ሶቪየት ህብረት በእርሻ ላይ ብቻ በማተኮር የእርሻ ምርቷንና የጥሬጥሬ ሀብቷን ወደውጭ በመላክ በአንፃሩም የካፒታሊስት አገሮች የሸቀጥ ማራገፊያ እንድትሆንና ነፃ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንዳትገነባ የሚያደርጋት ፀረ—ሶሻሊስት፣ ፀረ—ወዛአደር ኢኮኖሚ ፕላን አቀረቡ:: ፓርቲውም ይህንን ፀረ—ሶቪየት የሆነ አቋም፣ ሶቪየት ህብረትን የካፒታሊስት አገሮች ተቀጥያና የብሔራዊ ኢኮኖሚዋ እንዳይዳብር ወደኋላ የሚጎትታት ፕላን መቀጋት እንደሚያስፈልግ ወሰነ::

እንደዚሁም ሌሎች ተቃራኒ ኃይሎች የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት የመሀከለኛውን አርሶ አደር የወዛአደሩ አጋር ለመሆን አይችልም በማለት መሀከለኛ ገበሬውን ወደ ፀረ—አብዮት ካምፕ ሊያሸጋግረው የሚያስችል ስህተተኛ ፖለቲካ አቀረቡ:: ስታሊን ይህን የመሀከለኛ ገበሬውን ሚና በዝቅተኛ መመልከትና የወዛአደሩ አጋር አይሆንም ማለት አደገኛ አስተሳሰብ መሆኑን በማመልከት መሀከለኛው ገበሬ ወደወዛአደሩ መሳብ እንዳለበት የወዛአደሩ አርሶ አደሩ አንድነት መጠንከር እንዳለበት አሳየ:: በሌላ በኩልም ይህ አቀራረብ ሌኒኒዝምን መውጋትና ወዛአደሩ አርሶአደሩን ወደሱ ለመሳብ የሚያደርገውን ትግል ያለውን ችሎታ መናቅ መሆኑን አመለከተ::

በጦርነት ኮሙኒዝም ምትክ አዲሱ የኢኮኖሚክ ፕላን በሥራ ላይ እንዲውል ከተደረገ ወዲህ ትሮትስኪና ሌሎች ፀረ—ቦልሼቪክ ክፍሎች ይህ ፕላን በሥራ ላይ የማይውልበትን መንገድ በማውጠንጠን ፀረ—ሶሻሊስትና ፀረ—ወዛአደር ፖለቲካ በማስተጋባት የቦልሸቪክን ፓርቲ ተፈታትነውታል:: በሌላ በኩልም ከዱሮ የተወረሰውን ቢሮክራቲክ አፓራተስ በጣጥሶ ህዝባዊ አስተዳደር ለመገንባትና የኢኮኖሚው እድገት በተፋጠነ ሂደት እንዲጓዝ ለማድረግ ፓርቲው እነዚህና ሌሎች ችግሮች ገጥመውታል:: በተለይም ከዚህ በፊት



ሂነት ኢኮኖሚ ደሚናንት ሚና በሚጫወትበት ህብረተሰብ ከዚህ ወደኋላ ቀር ኢኮኖሚ ተላቀቆ አዲስና ዳይናሚክ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ መገንባት አስቸጋሪ መሆኑን መረዳት አይከብድም:: ሆኖም ግን ከዚህ ወደኋላ ቀር ኢኮኖሚ ተላቆ የወዛአደሩ መንግሥት አርገጠኛ ሊሆን የሚችልበትን በቴክኒክ የተራመደ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ለመገንባት ስታሊንና ፓርቲው ከብዙ ችግሮች ፊት ቢደቀኑም ቀሎና፣ ትሮትስኪና ቡካሪን እንደዚሁም ሌሎች አደርባዮች የፓርቲውን ፖሊሲ በየጊዜው ለማክሸፍ ያልሞከሩት ፀረ—ሶቪየትና ፀረ—ሶሻሊስት ሴራ ባይኖርም፣ ይህ ፖሊሲ በሥራ ላይ መዋል ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ አይነተኛ ለውጦች ተደርገዋል:: ስታሊንና ፓርቲው የሶሻሊስት ኢኮኖሚን በሚገባ ለመገንባትና ከካፒታሊስት አገሮች ጥገኝነት በፍጹም ለማላቀቅ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ከፍተኛ በሆነ የቴክኒክ መዋቅር ላይ መጣል እንዳለበት ወደኋላ የቀሩ የኢንዱስትሪ ዘርፎች መሻሻል (ሬሽናላይዝድ) እንዳለባቸው፣ በየቦታው ለኢንዱስትሪላይዜሽን ብቁ የሚያደርጉት የማሽን ቢልዲንግ ፕላንቶች (መሽን ቢልዲንግ ፕላንስ) መስፋፋት እንደሚያስፈልግ ወሰኑ:: ይህንንም የኢኮኖሚ አቅዱ ለማስፋፋት ምንጩና ሃይሉ እዚያው ሶቪየት ህብረት ውስጥ እንዳለ አመለከቱ:: ይህ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ኢንዱስትሪላይዜሽን እቅዱ ለብሔራዊ ኢኮኖሚ በራስ ሃይል በመተማመን መገንባት የሶሻሊዝም ኢኮኖሚ ከፍተኛ በሆነ ቴክኒክ እንዲገነባ ይችል ዘንድ ሰፋ ያለ በር ከፈተለት:: የንግድ ልውውጥ የገበረው የመግዛት ሃይል መጠመር፣ በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉት ኢንዱስትሪዎች የሚያመርቱት ምርት ከሚገኘው ትርፍ ካፒታል ለማከማቸትና ኢንቬስት ለማድረግ ተቻለ:: በአጭር ጊዜ ውስጥ የሶሻሊስት ኢንዱስትሪላይዜሽን ከፍተኛ ውጤት አሳየ:: ነገር ግን በእርሻ በኩል ያለው ውጤት ደካማ ስለነበረና በግል እርሻ ላይ ያተኮረ ስለሆነና በከፍተኛ ቴክኒክ ያልተመሠረተ ስለነበር ተፈላጊውን ውጤት ሊሰጥ አልቻለም:: ኢንዱስትሪና እርሻ ተመጣጣኝ በሆነ መንገድ እንዲራመድ ካልተደረገ፣ በተለይም ለቀላል ኢንዱስትሪ የሚሆን የጥሬጥሬ ሀብቶች በብዛት የሚመረቱበትን መንገድ በሰፊው ካልተተለመ፣ በገጠርና በከተማ መሀከል ያለው ልዩነት ቀስ በቀስ ሊወገድ የሚችልበትን ዘዴ መፍትሄ ካልተደረገ ብቁ የሆነ የሶሻሊስት ኢኮኖሚን በተፋጠነ መንገድ ለመገንባት ፓርቲው የማይቻል መሆኑን በመረዳት በዘመናዊ ዘዴ መስፋፋት የሚያስችሉትን አቅዶች አወጣ:: ይህ ዘመናዊ የእርሻ አቅድ በኮሌክቲቭ እርሻ ላይ የተመሠረተ እንዲሆንና መካናይዝድ የሆነ እርሻ እንዲስፋፋና ለካፒታሊዝም መገበሪያ በሆኑ ለሀብታም (ኩላኮች) ላይ የእፈንቢሽ ትግል መጀመር እንደሚያስፈልግ ፓርቲው ወሰነ:: ፓርቲው የድሃ ገበሬውንና መሀከለኛ ገበሬውን በመሳብ በኩላኮች ላይ እንዲነሱ አደረገ:: ነገር ግን ትሮትስኪና ተከታዮች እንዲሁም ቡካሪን የፓርቲውን ኮሌክቲቭይዜሽን ፕሮግራም በመቃወም በኩላኮች ላይ የእፈንቢሽ ትግል መካሄዱ የለበትም በማለት ከኩላኮች ጎን ተሰልፈው ፀረ—ሶሻሊስት ትግላቸውን ቀጠሉ:: ቡካሪንና ተከታዮቹ ኩላኮች በሶሻሊዝም ውስጥ

በመሳመድ ያድጋሉ ከዚህም የተነሳ የነቡ ሀብት ማከበት ለሶሺሊዝም አደጋ አያመጣም በማሰት ከፒታሊዝም እንደገና እነበረር ተ የወዝአደሩ መንግሥት በቡርዧው የሚተከበትን መንገድ አመለከቱ:: ኩላኮች ይህን ትሮትስኪይቶችና ቡካሪን የተበሉሩ ክንፎች ከነሱ ጋር መሆናቸውን በመረዳት በወዝአደሩ መንግሥት ላይ በማመጽ የህብረት እርሻዎችን የፓርቲው አባላት በሆኑ ኮሚኒስቶች ላይ የገዳይ ዘመቻ በማካሄድ ለኩሌክቲቭይዜሽን እንቅፋት ፈጠሩ:: ፓርቲው ግን በዚህ ፀረ—ሶሺሊስት ትግል ሳይፈታ በደሃ ገበሬው ላይ መተማመን ከመካከለኛ ገበሬው ጋር አንድነት በማጠንከር በሚል መፈክር ስር በመሰለፍ ኩላክሽን ከሰርሀራዊ ለመቀጋት በቆራጥነት ተነሳ:: እነ ቡካሪን በዚህ በሬት ያቀረቡትን የተሸሩፈን ቲዎሪ በይፉ በማውጣትና በኩላኮች ላይ የሚደረገውን የአፈገናብ ትግል በመቃወም የኩሌክቲቭይዜሽን መስፋፋት በአንጻሩም የኩላኮች መዳከም የእርሻ ውጤት እንዲቀነስ ይሆናል የሚል ስህተተኛ አቀራረብ ሰነዘሩ:: ከዚህ በመነሳት ይህ የአፈገናብ ትግል መቀረት እንዳለበት በማሰየት በሶሺሊዝም ውስጥ የሚፋፋመው የመደብ ትግል እንዲዘነጋ የሚያደርግና የወዝአደሩን የምባገነንነት የሚያናጋ ፀረ—ማርክሲስት ቲዎሪ አቀረቡ:: በሶሺሊዝም ውስጥ የመደብ ትግሉ የሚቀዘቅዝ ሳይሆን በተለየ መልክ የሚፋፋም መሆኑን ለመጠረቨውም የሞት የሽረት ትግል ቡርዧው የወዝአደሩን አምባገነንነት ለመታገል በየረዶፈ አሸቀሮችን በመሸረብ ከወዝአደሩ መንግሥት ሥልጣኑን ለመንጠቅ መንገዱን የሚያመቻች መሆኑን ቡካሪንና ተከታዮቹ ይህን በለመመልከት ስህተት ላይ ወደቁ:: ማርክስ በሶሺሊዝም ውስጥ ሊኖር የሚችለውን የመደብ ቅገልና መሠረታዊ አብዮታዊ ለውጥ በመመርኮዝ በካፒታሊዝምና በኮሙኒዝም መሀከል ያለውና የሚደረገው ለውጥ ሌላ ሳይሆን የወዝአደሩ አምባገነንነት መሆኑን ያበያል:: ስለዚህም ወዝአደሩ የመደብ ትግሉን አቀዝቅዞ ከቡርዧው ጋራ አንድነት የሚፈጥር ሳይሆን ወደ መደብ የለሹ ህብረትሰብ ለማምራት የገዒታ ቡርዧውን እንዳይንሰራራ በአምባገነንነት መዛሪያው ቆልፎ ይይዛል::

ፓርቲው በአንዱ በኩል ከአድርባዮች የሚሰነዘርበትን ፀረ—ሶሺሊስትና ቡርዧውን ሥልጣን ላይ የሚያወጣ ቀልበሽ ርእዮተዓለም በሌላ በኩል ኩላኮችና ሌሎች ፀረ—ሶቭየት ሃይሎች የኩሌክቲቭ እርሻውን ፕሮግራም በመቃወም. በየቦታው አሸቀሮችን በመሸረብ እንቅፋት ሆኑ:: ትሮትስኪና ተከታዮቹ እንዲሁም ቡካሪን የኩላኮች አፈ ቀላጤ በመሆን ሰልፋቸውን ከፀረ—ሶሺሊስት ሃይሎች ጋር አጣመሩ:: አድርባዮችና ኩላኮች በሚሸርቡት ሴራ የተነሳ የህብረት እርሻው ወዲያውኑ ተፈላጊውን ውጤት ሊያሳይ አልቻለም:: ፓርቲው እነዚህ ለሶሺሊዝም አደገኛ የሆኑ ሃይሎች የኩላኮችን የመደብ ጋንጭ ማጥፋትና የህብረት እርሻዎች ዋገጠሚዎቻቸውን ችግሮች ለመወጣት አስፈላጊ እርምጃዎች መወሰድ እንደሚያስፈልግ ወሰነ:: ፕሮግራሙ በሥራ ላይ ይውል ዘንድ የህብረት እርሻዎች የተበገበትን ፀረ—አብዮት ሃይሎች ማስወገድና በመነሱ ምትክ ለሶሺሊዝም ታማኝ የሆኑ ባለሞያዎች



በማሰልጠን መላክ እንደሚያስፈልግ በማመን 17000 የፓርቲ አባላት የሆኑትን እንዲሰማሩ ተደረገ:: በሁለት ዓመት ውስጥ የህብረት እርሻዎች በዴሞክራት በአስተዳደር ያሳችውን ችግሮች ከሞላ ጎደል በመወጣት የህብረት እርሻዎች አባላት የፖለቲካ ንቃት ከፍ በማድረግ፣ ኩላኮችና ሌሎች አድሃሪዎችን በመገጠር ጥሩ ውጤት ታየ:: በ1934 ዓ ም መጠረሽ ላይ የህብረት እርሻዎች 3\4 ኛውን የሀገሪቱን እርሻ በማጠቃለል የብሔራዊ ኢኮኖሚ ከኢንዱስትሪው ጎን ጥሩ መሠረት ተጣለ:: በቴክኒክ ረገድ ህብረት እርሻዎች አይነተኛ ለውጥ ተደረገባቸው:: ስታሊንና ፓርቲው የሶቭየትን ኢኮኖሚ በእርሻ ላይ ብቻ እንዲያተኩርና የካፒታሊስት አገሮች ተቀጥያ እንድትሆን አድርባዮች ያስተጋቡትን ፀረ—ወዝአደር አቀድ ከሰርሀራዊ በመቀጋታቸውና የብሔራዊ ኢኮኖሚው ነፃ በሆነ መንገድ እንዲያድግ ኢንዱስትሪላይዜሽን ፕሮግራም በሥራ ላይ እንዲውል ከፍተኛ ትግል በማካሄዳቸው ሶቭየት ህብረትን ከእርሻ ወደ ኢንዱስትሪ ሀገር በአጭር ጊዜ ውስጥ ለመለወጥ ተቻለ:: የቦልሸቪክ ፓርቲ በስታሊን መሪነት የፖለቲካ መስመር ትክክለኛነቱን በማረጋገጥ በማርክሲዝም ሌኒንዝም ርእዮተዓለም በመመራት አድርባዮች የፖለቲካ ከስረት እንዲደርስባቸውና የእነሱን መስመር ፀረ—አብዮትን የሚያገዙ የወዝአደሩን መንግሥት የሚያዳክሙና በቡርዧው የሚያስተክው መሆኑን በቲዎሪ ብቻ ሳይሆን በተግባር ጭምር አሳዩ::

ትሮትስኪ፣ ዚኖቭየቭ፣ ካሜኔቭ፣ ቡካሪንና ሌሎች የነሱ የቀኝ አድርባይ ፖለቲካ አራማጆች የሚያራምዱት ስህተተኛ የፖለቲካ መስመር በአሸናፊነት የማያዋጣቸው መሆኑን በመረዳት ከዚህ ፀረ—ሶቭየት ፖለቲካቸው አልፈው የወዝአደሩን መንግሥት በሃይል ለመቋቋም ወደ ቴሮሪዝም ተግባር ተሰማሩ:: ይህንን የቴሮሪዝም ሥራቸውን ለማቀነባበር ገዳይ ቡድን በማቋቋም የፓርቲውን ከፍተኛ ሃላፊነት ያላቸውን አባላት አንድ በአንድ ለመጠረስ አቀዱ:: ለመጀመሪያ ጊዜ ኪሮቭ የተባለውን ኮሚኒስት ገደሉ:: ይህ የቴሮሪዝም ተግባር በምርመራ የትሮትስኪይቶችና የዚኖቭየቭ አቀድ መሆኑ ተደረሰበት:: ከዚህ ተግባራቸው አልፈው ተርፈው የውጭ ሰላዮች በመሆን ፀረ—ሶቭየት ፖለቲካ ያራምዱ ጀመር:: ፓርቲው ይህን አደገኛ አዝማሚያ በመመልከት በዚያን ጊዜ የጀርመን ኢምፔሪያሊዝም ለሁለተኛ ጊዜ ጦርነት ለማንሳት ያንዣብብ ስለነበር ይህን ጦርነት ለመቋቋም የውስጥ ፀረ—አብዮት ሃይሎችን በቅድሚያ ማጽዳት እንደሚያስፈልግ በመረዳት ከሰርሀራዊ ታገላቸው::

## የአድርባዮች አቋቋምና የቻይና ጥያቄ

አድርባዮች የሶሺሊዝምን ኢኮኖሚ መገንባትና የወዝአደሩ መንግሥት የሚጠናከርበትን ብቻ የተቃወሙት ሳይሆን በአለም አቀፍ ደረጃ ፀረ—ማርክሲስትና ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይጣጣም የፖለቲካ መስመር ማስተጋባት ጀመሩ:: የተጨባጭ ሁኔታዎችንና የሃይልን

አስሳለፍ ካለመመርመራቸው የተነሳ በአወያሳይ ሁኔታዎችና በልዩ(አብኖርሜል) ሁኔታዎች መሃከል የተምታታ ሃሳብ ያቀርቡ ጀመር:: ከዚህም የተነሳ የአብዮት ሃይሎችን የሚያዳከምና የሚያስመታ በአንፃሩም ፀረ—አብዮት ሃይሎችን የሚያጠናክር ግምገማ ሰነዘሩ:: የቻይናን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሁኔታ በሚመለከት ረገድ ልክ እንደ ኦክቶበር አብዮት በተፈጠነ መንገድ መጓዝ አለበት በማለት በኦክቶበር ጊዜ የነበረው ተጨባጭ ሁኔታና በቻይና በ1925 ዓ/ም በሜይ በወዝአደሩ የኢንግሊዝና የጃፓንን ኢምፔሪያሊዝም በመቃወም የተደረገውን ሰላማዊ ሰልፍ በማመሳሰል የዚህን ንብታዊ እንቅስቃሴ ምንነት በይረቅ ወዝአደሩ ወሳኝ የሆነ ትግል ማካሄድ አለበት በማለት ወዝአደሩን ከሚንታግ ውስጥ በተሰገበሰገቡ አድሃሪዎችና በኢምፔሪያሊስቶች የሚያስመታውን መንገድ አመለከቱ:: ከዚህ ሰላማዊ ሰልፍ ጋር በማስታከክ አድርባዮች(ኦፖዚሽን ግሩፕ) የቻይና ወዝአደርና አርሶ አደር ልክ እንደ ሶቭየት ሀብረት ሶቭየትስ(የወዝአደሮችና የአርሶ አደሩ ኮረጋን) ማቋቋም አለባቸው የሚል ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር የማይገናኝ ስህተተኛ ፖሊቲካ አቀረቡ:: በዚያን ጊዜ የነበረው አብዮታዊ ሁኔታ በድርጅታዊ ሆነ በአመራሩ እንዲሁም የአብዮቱ እንቅስቃሴ ከፍተኛውን ደረጃ በለመያዙ በእንደዚህ ዓይነቱን ያልበሰለ ሁኔታ የወዝአደሩ መጋፈጥ የአብዮቱን ሃይል የሚያስመታውና የሚበታትነው መሆኑን ባለመረዳት በሰብጀክቲቭ አስተሳሰቡ የተሳሰተ ፖለቲካዊ አረማመድ አቀረቡ:: በቻይና ውስጥ ሊደረግ የሚችለውን አብዮትና የመደብ አሰላለፍ በሚመለከት በኩል እንዲሁም የነበረውን የበሸል ፍርሜሽን ስህተተኛ ግምገማዎችን አቀረቡ:: ቻይና በመሠረቱ በዚያን ጊዜ ግማሽ—ፊውዳል ግማሽ—ካፒታሊስትና ግማሽ—ኮሎኒ አገር እንደመሆኑ መጠንና ቀናው የህብረተሰቡ ደሚናንት ከፍሎች ገበሬውና ጉልተኛው ነበሩ:: ይህም ማለት የምርት ግኑኝነቶች መሬት በሳቸውና በሌሳቸው ላይ የተመሠረተ ነበር:: በሌላ በኩልም በካፒታሊዝም መስፋፋት የተነሳ በአሮጌው የምርት ግኑኝነትና በአዲሱ መካከል ቅራኔ እየበረ ሰለመጣ የፊውዳሉ ክፍል ይህንን አዲስ የምርት ግኑኝነት ለመግታት ትግል ያካሄድ ነበር:: የሚርቻንት ካፒታሊዝም ሥርጉ መግባት የኢንዱስትሪዎች በትሳልቅ ከተሞች መስፋፋት የወዝአደሩን ቁጥር እንዲያድግ ሆኖዋል::

ራዴክ የተባለው አድርባይ የነዚህን ሁለቱን የኢኮኖሚ ግኑኝነቶች ቅራኔ ውስጥ መግባትና በዚያን ወቅት የትኛው ደሚናንት ሚና እንደሚጫወት ባያስይ የመደቦችን አሰላለፍ ባያመለክት ደረገ የሚችለው አብዮት የአገራሪያን ረቮሉሽን ነው በማለት በቲዎሪ አቀራረቡ ቀንጽል የሆነ ሃሳብ አቀረበ:: በዚህ ቲዎሪ ውስጥ ገበሬው ከባላባቱ ይልቅ በከበርቴው ላይ ነው ትግሉን ያተኮረው በማለት ከተጨባጭ ሁኔታ ጋር ያልተያያዘ የፊውዳሉን መደብ መኖር በዝቅተኛ ደረጃ የሚመለከት ወይንም እንደሌለ የሚቆጥር የተሳሳተ ግምገማ አቀረበ:: በዚህ ጽሑፍ ውስጥ በመቀጠል ኮሚንታንግ አንድ የሆነ የተለያዩ



መደቦችን ያቀፈ አንድ ፓርቲ ነው በማለት ከኮሚንታንግ ይዘት ጋር የማይመሳሰል ሐሳቦችን ሰነዘረ:: በዚያን ጊዜ ኮሚንታንግ የተወከሉ መደቦችንም ጥቅም የሚያስጠብቁ ፓርቲዎች የነበሩበት የፓርቲ ብሎክ የሆነና፣ ይህ የፓርቲ ብሎክ ያቀፋቸው ፓርቲዎች የራሳቸው ድርጅታዊ መዋቅር ያላቸው ነበሩ:: የዚህን የፓርቲ ብሎክ ዲሞክራሲያዊነት ባይመረምር ማርክሲስቶች እንደ ኮሚንታንግ ባሉ የፓርቲ ብሎኮች ውስጥ መሳተፍን አይቀበሉም በማለት የሃቀኛ ማሌዎችን ሃሳፊነት አመቺ ሁኔታዎች ቢፈጠሩ የአብዮቱን ሂደት ለማፋጠን መሳተፍ የአብዮቱን ግስጋሴ የሚያፋጥን መሆኑን ባለመረዳቱ ስህተት ውስጥ ወደቀ:: የኮሚኒታንግን የመደብ ይዘት ባይመረምርና በዚያን ጊዜ የተሰለፉትን ማሌዎች አቋም ባያጤን ኮሚንታንግ የንዑስ ከበርቴ ፓርቲ ነው በማለት ስህተተኛ ግምገማ ሰነዘረ:: በዚያን ጊዜ ኮሚንታንግ በከፊል ፊውዳል በከፊል ካፒታሊስት ቻይና ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያካሂድ በብሔራዊ ከበርቴው እስከ ማሌዎች ድረስ ያቀፈ የፓርቲዎች ብሎክ የሆነ እንደነበር አልተረዳም:: (የኮሚንታንግ አንዱ ክፍል በሸንጋይሼክ የሚመራው በኋላ አድሃሪ ሆኖዋል)

ማርትኖቭ የተባለው አድርባይ የሁዋን መንግሥት(የኮሚንታንግ ግራ ክንፍ በሁዋን አውራጃ) ሁለተኛ አብዮት ባያደርግ በሰላም ወደ ወዝአደሩ አምባገነንነት ሊሻገር ይችላል በማለት በሁዋን መንግሥት የመደብ ይዘት ባለመመርመር ሰብጀክቲቭ አስተሳሰብ አቀረበ:: በዚያን ጊዜ የሁዋን መንግሥት ከኮሙኒስቶች እስከ ብሔራዊ ከበርቴው ድረስ ያቀፈ ድርጅትና በፀረ—ኢምፔሪያሊስት መድረክ ላይ የተሰለፈ ቢሆንም የዲሞክራቲክ አብዮቱን ጠርሶ ወደ ሶሻሊስት አብዮት ለመሸጋገር የሚያስችሉትን ጠባዮች ሙሉ በሙሉ ያላቀፈ ብሎክ ነበር:: የዚህን የቡርዧዋ አብዮት ከፍጻሜ ሊያደርሰው የሚችለው ሃይል የኮሙኒስት ፓርቲ እንደሆነና ይህም ፓርቲ ወዝአደሩንና ገበሬውን እንዲሁም የግራ ክንፍ ንዑስ ከበርቴውን የመምራት ሃሳፊነት እንዳለበት በዚህም አብዮታዊ ጉዞው ከቡርዧዋው ሥልጣኑን ለመንጠቅ አመጽ ወሳኝ ሚና እንዳለው አልተረዳም:: ትሮትስኪና ዚኖቪየቭ የቻይናን የመደብ ፎርሜሽን የነበረውን ቅራኔ ባይመረምሩ በወቅቱ የነበረውን አብዮታዊ እንቅስቃሴ ሲገመግሙ የቅራኔ መፋፋም ዋና ምንጩ የቻይና ከኢምፔሪያሊስት ሃይሎች ጋር መንግሥታዊ የንግድ ግኑኝነት ስላላትና ከዚህም የተነሳ ጥገኛ ስለሆነች ነው በማለት የፊውዳሉንና የቢሮ ከበርቴው በሰፊው ገበሬ ላይ የሚያደርጉትን ጭቆና በዝቅተኛ ደረጃ የሚያስመለከት ስህተትኛ ግምገማ አቀረቡ:: ከዚህም የቲዎሪው አቀራረብ ትሮትስኪ የኢምፔሪያሊስት ሃይሎችን ለመዋጋት በመጀመሪያ በፊውዳሉና በቢሮክራሲው ላይ መነሳት እንደሚያስፈልግ ኢምፔሪያሊዝምን ለመደምሰስ ፊውዳሊዝምን መዋጋት እንደሚያስፈልግ ባለመረዳቱ የቲዎሪ ስህተት ላይ ወደቀ:: የዚህ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ጠባይ የገጠር አብዮት እንደሆነና ይህም ሌላ ባይሆን የቡርዧው አብዮት አንደኛው ጉን

መሆኑን ባለመገንዘቡ የቻይና ካፒታሊስቶችን ጥቅም የሚያንፀባርቅ የከበርቴ ነፃነት መኖር አለበት አለ:: ትሮትስኪ የቻይናን አብዮት አረማመድና የመደቦችን አሰላለፍ ካለመረዳቱ የተነሳ የሁዋን መንግሥት (የኰሚንታንግ ገራ ክንፍ) ልብ ወለድ (ፊክሽን) ነው በማለት ሶሚክን ያልተከተለና የኮሚኒስቶችን ሚና የሁዋንን ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል የሚያንቋሽሽ የቲዎሪ ስህተት ብቻ ሳይሆን ኮንፊዩዥን ውስጥ ወደቀ:: ዚኖቭየቭ የሁዋን መንግሥት ኪማሊስት ነው በማለት ፍጹም የኰሚንታንግን ገራ ክንፍ የመደብም ይዘቱን የማይመለከት ግምገማ ሰነዘረ:: ኪማሊስት(በቱርክ አገር የተነሳ ሃይል) በመደብ ይዘቱ ፀረ—ወዝአደርና ፀረ—ገበሬ የሆነ ከኮሚኒስቶች ጋር በፍጹም ለመሥራት የማይፈልግ ፀረ—አብዮት ሃይል ሲሆን የሁዋን መንግሥት ግን ከኮሚኒስቶች ጋር ይሠራ የነበረ፣ የገጠር አብዮት እንዲካሄድ አመቺ ሁኔታዎች የፈጠረ ከኮሚኒስቶች እስከ ብሔራዊ ከበርቴው ያቀፈ ድርጅት ነበር:: ከዚህም ስህተቱ ሌላ አራቱ ኪማሊስት ብሎ የሚጠራውን ፀረ—አብዮት ሃይል በሙሉ ሃይል መርዳት ያስፈልጋል የሚል አርስ በራሱ የሚጋጭ ሃሳብ አቀረበ::

ትሮትስኪና ዚኖቭየቭ ይህንን የኰሚንታንግ ገራ ክንፍ ድርጅት በዝቅተኛ ደረጃ በመመልከት በቻይና የወዝአደሩና የገበሬው ዲፒዮቲ እንዲቋቋም ሃሳብ አቀረቡ:: ይህንንም ሃሳብ ሲያቀርቡ ከሶቭየት ህብረት አብዮታዊ እንቅስቃሴ ጋር በማመሳሰል በሁለቱ አገሮች የነበረውን የተለያየ ሁኔታና አብዮታዊ እንቅስቃሴ ፈለግ ባለመመርመር ነበር:: በዚያን ጊዜ በሁዋን የሚገኘው የኰሚንታንግ ገራ ክንፍ ለቡርዧዋ ዲሞክራቲክ አብዮት መገፋት ይረዳ ስለነበር ከንኑ ''ሶቭየትስ'' ማቋቋም ብሔራዊ ከበርቴውን በፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል ውስጥ እንዳይሰለፍና በኮሙኒስቶች ላይ ጥርጣሬ እንዲያድርበት ወደ ቀኙ የኰሚንታንግ ክንፍ አሰልፎ አብዮቱን የሚያኮላሽው መሆኑን ባለመገንዘብ ስህተተኛ መስመር ላይ ወደቁ:: ሌላው ይህ የቡርዧ አብዮትን ገና በአንጭጩ ስለነበር እንደዚህ አይነት ገራ ቀደም ፖለቲካ ማስተጋባት አብዮቱ እንዲቀጭ ማድረግና ፀረ—አብዮት እንዲነገስ ትሮትስኪና ዚኖቭየቭ አልተረዱም:: እንዲያውም የገጠር አብዮቱ ከዳር እስከ ዳር ጥልቀት እንዲኖረው ኮሙኒስቶች ይህንን መድረክ መጠቀምና ገበሬውን በንቃት፣ በድርጅቱ ኩፍ እንዲል የማገዝ ሃላፊነትን በእነሱ ላይ እንደወደቀ ትሮትስኪና ዚኖቭየቭ አልተገነዘቡም:: ከዚህም አያይዞ ቻይና በተለያዩ የኢምፔሪያሊስት ሃይሎች በተደጋጋሚ የተያዘች ስለነበር የዚህ አብዮት አንደኛው ጠባይ ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግል እንደመሆኑም መጠን የብሔራዊ ከበርቴውንና አገር ወዳድ የሆነው ነገር ግን በአብዮቱ ላይ ጥርጣሬ የሚያድርበትን እስከተወሰነ ደረጃ ከኮሙኒስቶች ጋር ተሰልፎ የውጭ ወረራን እንደሚከላከሉ በአጭሩ በአንድ አብዮታዊ እንቅስቃሴ ውስጥ የሃይልን አሰላለፍ፣



የቅራኔዎችን አጠቃቀም ባለመገንዘብ የአብዮቱን ጠባይና አረማመድ ካለመመርመር ኮሙኒስቶችን የሚያስመታና የሚጠታትን አደገኛ መፈክሮች አመለከቱ:: ትሮትስኪና ሌሎች አድርባዮች የዚህን አብዮት ምንነትና ጠባይ ካለመገንዘባቸው የተነሳ አርስ በራሳቸው የሚጋጩና የተዛባ አቋሞችን ያሰሙ ነበር:: በአንድ የተወሰነ ወቅት ፊውዳሊዝም በቻይና ውስጥ ስለሌለ የገጠር አብዮት ማካሄድ አይቻልም የሚል የቻይና ህብረተሰብ ያረፈበትን ስልተምርት(የኢኮኖሚ ስርአት) የዚህ የስልቱ ምርት አቀናጆዎች የሆኑትን የምርት ግኑኝነቶችና የምርት ሃይሎች በምን የእድገት ደረጃ ላይ እንዳሉና የህብረተሰቡን የሶስዮ ኢኮኖሚክ ጠባይ ባለመመርመራቸው የስህተት ስህተት ላይ ወደቁ:: በሌላ ጊዜ ይኸው ክንፍ የፊውዳሉን ስልተ ምርት መኖር በመካድ አገጠር አብዮት ሊካሄድ ይችላል የሚል የትኛው የህብረተሰብ ክፍል በየትኛው ላይ መነሳት እንዳለበት ወይንም በህብረተሰቡ ውስጥ በአንድ የተወሰነ ታሪካዊ ወቅት ዶሚናንት ሚና የሚጫወተትን የህብረተሰብ ክፍሎች የሚያሳይና በየትኞቹ መደቦች ላይ ቅራኔው ጉልቶ የሚታየው ብለው ባይመረምሩ የገጠርን አብዮት መደረግ መቻሉን አመለከቱ:: በሌላ ወገን ደግሞ የቻይና አብዮት ዋና ምክንያት የገጠር አብዮት ሳይሆን የከበርቴ አብዮት ነው የሚል የአገር ውስጥ ካፒታሊስቶች በአለም አቀፍ ካፒታሊዝም እንደተበተቡ የሚያሳይ የካፒታሊስቶችን ጥቅም ብቻ የሚያንፀባርቅ የቻይናን አብዮት ጠባይና አረማመድ ያሳቀፈ ግምገማ አቀረቡ::

ስታሊን ይህንን የአድርባዮችን የፖለቲካ ቅዠት በማሳየት የቻይናን የህብረተሰብ እድገት ደረጃ የኢኮኖሚው ስርአት ያረፈበትን ስልተ ምርት በትክክል በማመልከት የአብዮቱን እንቅስቃሴ ምንጭና የቅራኔዎች አሰላለፍ እንዴት እንደነበሩ በሳይንሱ አመዘዘነ:: የህብረተሰብ የኢኮኖሚ ስርአት የሚያይለው ክፍል የፊውዳሉ ስለሆነ ጥቂት ጉልተኞች ብዙሃኑን ገበሬ በመበዝበዝ ከሰብ በመቶ የሆነው መሬት በቁጥጥሩ ሥር ነበር:: የዚህ አብዮት የቡርዧ አብዮት ሲሆን በነበረው አመቺ ሁኔታ የገጠር አብዮት ከዳር እስከ ዳር እንዲሰፋ ለኮሙኒስቶች ከሰፊው ገበሬ ጋር እንዲቀሳቀሱ ጥሩ ሁኔታ ፈጥሮላቸው ነበር:: በሌላ በኩልም የፊውዳሉና የቢሮክራሲው ክፍል ከውጭ ኢምፔሪያሊስቶች ጋር በሺህ ድር ተሳስሮ የውጭ ተጽእኖ በብሔራዊ ከበርቴው ላይ እንዳያድግ ቆልፎ ይዟል:: ከዚህም የተነሳ የዚህ አብዮት ፀረ—ፊውዳል ብቻ ሳይሆን ፀረ—ኢምፔሪያሊስት ትግልም ነው በማለት የአብዮቱን ይዘትና አረማመድ በትክክል አስቀመጠው:: ስለሆነም በነበረው የሃይል አሰላለፍና አመቺ ሁኔታ ኮሙኒስቶች ከብሔራዊ ከበርቴው ጋር ጊዜያዊ ትብብርን በመፍጠር ይህንን የቡርዧዋ አብዮት በመጠቀም የገጠሩን አብዮት ጥልቀት እንዲኖረው በሁዋን መንግሥት (የኰሚንታንግ ገራ ክንፍ) ውስጥ መሳተፍ

ይችላሉ በማለት የአድርባዮችን ስህተት አሳዩ:: የዚህን የቡርዥዋ አብዮት ወቅሳኝነት በመረዳትና የብሔራዊ ከበርቴውን ፀረ-ፊውዳልና ፀረ-ኢምፔሪያሊስት ትግል በማጤን አብዮቱ በወቅሳኝነቱ እንዲቀጥልና የገሬ ኮሚንታንግ ወደ ቀኙ እንዳይደበላለቅ ባለጊዜው ሶቪየት ዲፕቲስ መድረክ ወይንም ኮሙኒስቶች ለዚህ በችኮላ ቅስቀሳ ማካሄድ የለባቸውም በማለት የዚህን ችኩል ፖለቲካ ስህተተኛነት አመለከተ:: ነገር ግን ብሔራዊ ከበርቴው ወላዋይነት ጠባይ እያሳየ ከሄደና የገጠር አብዮቱን እንዳይራመድ እንቅፋት ከመሆን ኮሙኒስቶች ይህንን አዝማሚያ መቃጋት እንዳለባቸው አሳዩ::

## ስታሊን ቀኝ አድርባዮች በኢኮኖሚ ጥያቄዎች ላይ ያላቸውን ስህተት እንዴት እንዳመለከተ::

የወዝአደሩ መደብ በፓርቲው አመራርነት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ የሶሺሊስት ኢኮኖሚን ለመገንባትና የወዝአደር አርሶአደሩን አንድነት ለማጠንከር ከፆን ችግሮች ፊት እንደተደቀነ፣ እነዚህን ችግሮች ተወጥቶ በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ የተመሠረተ ኢኮኖሚ ለመገንባት በአንድ በኩል ምን ያህል ውጣ ውረድ የበዛባቸው ትግሎች እንዳካሄደና በሌላ በኩል በእነዚህ ችግሮች ሽፋን ስር መሽገው የፖለቲካ ከሥረታቸውን ለመደበቅና የወዝአደሩን መንግሥት አዳክመው ሥልጣን የቡርዥዋው እጅ ለማስገባት አድርባዮች ያልጠነሰሱት ሴራ፣ ያልገለበጡት ድንጋይ እንደሌለ አይተናል:: ነገር ግን ስታሊንና ፓርቲው እነዚህን አድርባዮች በርእዮተዓለም አሸንፈው የፖለቲካ ከስረታቸውን አሳይተው የሶሺሊስት ኢንዱስትሪላይዜሽን በተፋጠነ መንገድ አካሄደው፣ የተናጠል እርሻዎችን ወደ ህብረት እርሻ በመለወጥ ከቀላል የእርሻ መሣሪያዎች ወደ ከፍተኛ የምርት መሣሪያዎች በመሸጋገር የብሔራዊ ኢኮኖሚው መሠረት የሆነውን ዘርፍ በከፍተኛ ደረጃ እንዳደራጁና ነፃ የሆነ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እንደገነቡ አይተናል:: ነገር ግን በሶሺሊዝም በካፒታሊዝምና በኮሙኒዝም መሀከል የሚደረገ ረጅምና አስቸጋሪ የህብረተሰብ ለውጥ እንደመሆኑ ሁሉ ከዚህ አዲስና ታላቅ የህብረተሰብ መኪና ጋር ለመጓዝ ያቃታቸው እስከ ተወሰነ ደረጃ በማርክሲዝም ቀሚስ ተሸፍነው የሚጓዙ ግን ቀናት ሲያልፍ ይህንን የጋሪውን ገበናቸውን እየከፈቱት እንደገና በማርክሲዝም ላይ ጥያቄዎች ማስቀመጣቸው የማይቀረው ሃቅ ነው:: የሶሺሊስትን ህብረተሰብ መስርቶ ወደ መደብ የለሽ ህብረተሰብ ለመጓዝ በየቦታው እንቅፋቶች ይደቀናሉ:: እነዚህን እንቅፋቶች እንደየሁኔታውና እንደየአመጣጡ መታገል ማርክሲዝምን እንዳበርዙ አቀብዮ መከላከል ስህተቶች ብቅ ሲሉ በሳይንሱ ጉሉ መቅጠት የሃቀኛ ማርክሲስቶች ተግባር ይሆናል::



## የኢኮኖሚ ጥያቄና የአድርባዮች ስህተት

የመጀመሪያው የአድርባዮች ስህተት ወዝአደሩ በፓርቲው አማካይነት ሥልጣን ከጨበጠ በኋላ ከዚህ በፊት አሮጌው ስርአት የሚገለገልበትን የፖለቲካ የኢኮኖሚ ህጎች በማጥፋት በእሱ ምትክ አዲስ ህጎችን ይፈጥራል በማለት የፖለቲካና የኢኮኖሚ ህግ በዘፈቀደ በሰው የሚጠፋና የሚፈጠር ወይንም የሚንቀሳቀስ መስሏቸው:: ይህንን ፖለቲካዊ ኢኮኖሚ ህግ የስነፍጥረትንም ህግ ጠምሮ ስቶች በህብረተሰብ እድገት ውስጥ አንደኛው መደብ ሌላኛውን መደብ ለመተብተብ እንደሚያወጣው ፍርዳዊ ባህሪ ያላቸው፣ አንደኛው መደብ በሌላኛው መደብ ሲተካ እንደሚሽረው ህግ ጋር አንድ አደረጉት:: ማርክሲዝም ግን እነዚህን የተፈጥሮም ሆነ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚ ህጎች የተጠበቁ ነገሮች አረማመድ ሂደት ነፀብራቆች እንደሆኑ የሚጠሩ የሚደመሰሱ ሳይሆኑ አሮጌው ስርአት በአዲስ ሲተካ አሮጌ ህጎች ጥቅሞታቸውን(ቫሊዲቲ) የሚያጡ ለአዲሱ ህግ ቦታቸውን የሚለቁ መሆናቸውን ነው:: በጥሩ አሮጌው ህግ ከአዲስ የህብረተሰብ እድገት ህጎች ጋር ስለማይጣጣም በአዲስ የህብረተሰብ አውታሮች ውስጥ ሚናው አያከትም አዲሱ ቦታውን እየተካው የሚሄደ ነው:: ይህ የአሮጌው ተፈጥሮ ቀዋሚ ሆነ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ በአዲሱ ሲተካ ከሰው አእምሮ ቁጥጥር ውጭ እንደሆነና የህጎችንም ድርጊት ሰው ለራሱ የሚጠቀምባቸው መሆኑን ነው::

ሁለተኛው ስህተታቸው የኢኮኖሚ ህጎች በጠባያቸው ነጥራዊ ነገሮች(ኤሌሜንትስ) የሆኑ ድርጊታቸው ሊለወጥ የማይችልና ህብረተሰብ እነዚህን ከነሱ አንፃር ቢታይ ሃይለቢስ ነው በማለት ህብረተሰብ በአለፋቸው የእድገት ደረጃዎች የእነዚህን ህጎች ድርጊት ውስን በማድረግ ለራሱ እንዳልተጠቀመባቸው አድርገው ካዱ:: ነገር ግን ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ህጎችን ድርጊት ልክ እንደተፈጥሮ ህጎች ድርጊት በመለወጥ ነርውን ለማሸሸል እንደተጠቀመባቸው ደረጃ በደረጃ ያለፋቸው የህብረተሰብ እድገቶች ከነዚህ የእድገት ለውጦችም ጋር የኢኮኖሚ ህጎችን ድርጊት በመለወጥ እንደተጠቀመባቸው ታሪካዊ ቁስአካላዊነት ያስተምረናል:: በሌላ በኩልም የኢኮኖሚ ህጎች ነጥራዊ ጠባይ(ኤለመንታል) ያዘሉ ባይሆኑ በአንዱ ህብረተሰብ እድገት ደረጃ ላይ ያለው የስልተ ምርት ነፀብራቅ ማለት የምርት ሃይሎችና የምርት ግንኙነቶች ድምራዊ ነፀብራቅ ናቸው:: ስለዚህም እነዚህ የስልተምርት ነፀብራቆች በአዲስ ስልተምርት ሲተኩ(ለምሳሌ ካፒታሊዝም በሶሺሊዝም)ቦታቸውን ለአዲሱ የሚለቁ ናቸው::

ስድስተኛው ስህተታቸው የወዝአደሩ ፓርቲ የተስተካከለ የብሔራዊ ኢኮኖሚ እድገት በመጠቀም የድሮውን ህግ ደምስስ በአዲስ ተክቸው በማለት ይህ የተስተካከለ የኢኮኖሚ እድገት(ባላንስድ ኢኮኖሚክ ዲቨሎፕመንት) ህግ አናርኪና የሸቀጥ ውድድር ከሚካሄድበት ከካፒታሊስት ኢኮኖሚ ጋር በተቃራኒው የቆመ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ህግ መሆኑን አልተረዱም:: በመሆኑም በኅብረተሰብ እጅ የነበረው የምርት መሣሪያ በወዝአደሩና ከዚህ በፊት በተጨቆነው ህብረተሰብ ቁጥጥር ሥር በመዋሉ የምርት የህብረተሰብን የማቴሪያል ፍላጎት በተስተካከለ የብሔራዊ ኢኮኖሚ ህግ እድገት ብቻ ለማሟላት ስለሚቻልና የሶሻሊዝም ኢኮኖሚ መንቀሳቀስ የሚችለው በዚህ ህግ ብቻ ስለሆነ ይህን ህግ መጠቀም አስገደደ:: ነገር ግን የወዝአደሩ ፓርቲ በመጠቀም የድሮውን ህግ አሳጠፋውም:: አሮጌው ህግ በአዲሱ በመቀጡ በታውን ለቀቀ::

ሰባተኛው ስህተታቸው አንዱ ህብረተሰብ ከካፒታሊዝም ወደ ሶሻሊዝም በመሸጋገሩ በአቀዳዊ ኢኮኖሚ መሠረት የኢኮኖሚ ህጎችም ይለወጣሉ( ትራንስፎርሙ) (ትራንስፎርም የውጭውን ቅርጽ መለወጥና የውስጡን ባህርይ መቀየር) አንዱ ነገር ከተለወጠ(ትራንስፎርሙ) ለማጥፋት እንደሚቻልና በምትኩ አዲስ ህግን መፍጠር እንደሚቻል ሊገነዘቡ አልቻሉም:: ነገር ግን ሰው እነዚህን የኢኮኖሚ ህጎች አደገኛ ከሆኑ ድርጊታቸውን ሊወስን ወይንም የድርጊቱን አቅጣጫ ሊቀይረው ይችላል::

ስምንተኛው ስህተታቸው ወዝአደሩ ስልጣን ከጨበጠ በኋላና የምርት መሣሪያዎችን ከወረሰ ወዲህ የእቃ ምርትን(ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን) በህብረተሰብ ውስጥ ቦታ (ተሳትፎ) እንዲኖረው አደረገው በማለትና ባተለያዩ የኢኮኖሚ የእድገት ደረጃዎችና የአንዱ ህብረተሰብ እድገት መመጠኛ የሆነው የኢኮኖሚው ሥርአት በከፍተኛ ደረጃ መገኘትና አለመገኘትን ሁኔታዎች ሳያጤኑ የወዝአደሩ ፓርቲ እነዚህን ሁኔታዎች ባይመረምር በዘፈቀደ ማንኛውም እርምጃዎች የሚወስድ በማስመሰል የወዝአደሩን ፓርቲ ሃሳፊነት ዝቅ የሚያደርግ ስብጀክቲቭ አስተሳሰብ ላይ ወደቁ:: የወዝአደሩ ፓርቲ ሥልጣን ከመውሰዱም በፊት ህብረተሰብ የሚገኝበትን የኢኮኖሚ ሥርአት የዚህን የኢኮኖሚ ስርአት በከፍተኛ ደረጃ መገኘትና አለመገኘት ይመረምራል:: ከዚህ በመነሳት ሊወሰዱና ሊጠበቁ የሚችሉ እርምጃዎችን ያጠናል:: በመሆኑም የካፒታሊዝም እድገት ከፍተኛ ደረጃ በደረሰባቸው አገሮችና እርሻ በከፍተኛ ቴክኒክ በሚታረስባቸው ሀገሮች የወዝአደሩ ፓርቲ ሥልጣን ጨብጦ የኢንዱስትሪንም ሆነ የእርሻ ምርት መሳሪያዎችን በመውረስ የህዝቡ ሃብት ያደርጋቸዋል:: ይህ ማለት 1ኛ የምርት መሣሪያዎች ጠቅላላውን መሸጣቸውና መለወጣቸው ያከትማል:: ለጠቅላላው የህብረተሰብ ጥቅም እንዲውሉ ይደረጋሉ:: 2ኛ የምርት መሣሪያዎች በግል እጅ እስከሌሉ ድረስ ደግሞ የምርት ባለቤትም ስለማይኖር የወዝአደሩ መንግሥት በአቀዳ



ዊ ኢኮኖሚ መሠረት ምርት ለህብረተሰቡ የሚቀረስበትን መንገድ ያዘጋጃል:: (ምርት አይታደልም) እንደዚሁ የሚመረተውም ትርፍን ለማካበት ሳይሆን ከህብረተሰቡ የእድገት ደረጃና የማቴሪያል ፍላጎት ጋር እየተመዛዘነ ከብዛት ወደ ጥራት የሚያመራ ነው:: ነገር ግን ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ደረጃ ባላደገባቸው ሀገሮች ገና በየቦታው ተበታትነው የሚገኙ አናነሽ የእርሻም ሆነ እንደኮቴጅ ያሉ እንዱስትሪዎች በሚገኙባቸው ሀገሮች የወዝአደሩ ፓርቲ እነዚህን ሁሉ በአንድ ጊዜ ሊወርሳቸው አይችልም:: በእርግጥ በካፒታሊስቶች እጅ የሚገኙ የምርት መሣሪያዎች ትላልቅ መካናይዝድ እርሻዎች የህዝቡ ያደርጋቸዋል:: ሌሎች ትናንሽ ተናጠል አምራቾች ግን በጋራ እንዲያመርቱና መንግሥትም ዘመናዊ የሆነ የእርሻ መሳሪያ በመስጠት ይረዳቸዋል:: ይህ ግን ቢደረግ ለእነዚህ የጋርዮሽ(ኮሌክቲቭ) እርሻ የሚሰጠው የምርት መሣሪያ አይሸጥም:: አይለወጥም:: ምርትን ግን መንግሥት በተመነው ዋጋ መሠረት(አምራች በይጎዳ) ሊሸጠውና ሊለውጠው ይችላል:: በዚህም የኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን(የሸቀጣሸቀጥ ንግድ) ንግዱ በከፍተኛ ደረጃ እንዲካሄድ መንገድ ይከፍታል:: ይህ የሚደረገው ግን ካፒታሊዝም ተስፋፍቶ የሶሻሊስት ህብረተሰብን ለመተካት ሳይሆን ለእዚህ በአይነት አያደገ ለሚሄደው ህብረተሰብ የማቴሪያል ዝግጅት ለማድረግና ከፍተኛ የኢንዱስትሪ መስኮችን ለመክፈት እንዲያስችል ነው:: ምክንያቱም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ በከባድ ኢንዱስትሪና በከፍተኛ ቴክኒክ መዋቅር ላይ ብቻ ስለሚመሠረት ነው::

ዘጠነኛው ስህተታቸው የሸቀጣሸቀጥ ምርት(ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን) በማንኛውም ጊዜና በማንኛውም ሁኔታ ወደ ካፒታሊዝም ያመራል የሚል ነው:: የካፒታሊስት ምርት በከፍተኛ ደረጃ የሚገኘው የሸቀጣሸቀጥ ምርት ነው:: ስለሆነም የምርት መሣሪያዎች ግላዊ ባለቤትነት እስካላቸው ድረስ የሸቀጣሸቀጥ ምርት ወደ ካፒታሊዝም ያመራል:: የካፒታሊስት ምርት የሚጀምረውም የምርት መሣሪያዎች በግል ሀብት እጅ እየወደቁ ሲሄዱ ነው:: የምርት መሣሪያዎች በግል እጅ እስከሆኑ ድረስ ደግሞ የሰው ጉልበት የሚሸጥና በምርት ሂደቶችም ውስጥ የሚበዘበዝ ይሆናል:: ካለነዚህ ሁኔታዎች የካፒታሊስት ምርት አይኖርም:: ለምሳሌ በባሪያ ሥርአት ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ነበር:: ነገር ግን ይህ ወደ ካፒታሊዝም እንዲያመራው አላደረገም:: እንደዚሁም በፊውዳሉ ህብረተሰብ ውስጥ የሸቀጣሸቀጥ ምርት(በከፍተኛ ደረጃ አይደለም) ነበር:: ግንም ለካፒታሊዝም የማቴሪያል ሁኔታዎችን ቢያዘጋጅም ቀሉ በቀጥታ ወደ ካፒታሊዝም እንዲመራ አላደረገም:: በሶሻሊስት የኢኮኖሚ ሥርአት ሁለት የኢኮኖሚ አውታሮች ማለትና የህዝብና የጋርዮሽ በሚገኙበት ሁኔታው ስለሚያስገድድ እስከተወሰነ ደረጃ ድረስ የሸቀጣሸቀጥ ምርት ይካሄዳል:: ይህም ማለት በጋርዮሽ እርሻዎች በኩቴጅ ኢንዱስትሪ የሚመረቱት ምርቶች አምራቾች ሊሸጧቸውና ሊለውጧቸው ይችላሉ:: በዚህም በአንድ በኩል አምራቾች ያመረቱትን

በመሸጥ የኢንዱስትሪን ምርትን እንደየምርጫቸው ሊገዙ ይችላሉ:: በሌላ በኩል ገንዱ ይሰፋፋል:: ግን ይህ ማለት የገዱታ የዚህ የምርት መሸጥና መለወጥ የወዝአደሩ ፖርቲ ሥልጣኑን እስከጠበጠ ድረስና የግል ሀብት በምርት መሣሪያዎች ላይ ቁጥጥር እስከሌለው ድረስ ወደ ከፒታሊስት ምርት(ከፒታሊስት ፕሮዳክሽን) ያመራል ማለት አይደለም:: ሊሆንም አይችልም:: ከዚህ ስህተታቸው ጋር በማያያዝ የወዝአደሩ ፖርቲ የእቃ ምርት እንዲቀጥል ስለአደረገ የከፒታሊስት ህብረተሰብ ጠባይ የሆኑት የሰው ኃልበት እንደእቃ መሸጥ ሰርፕላስ ቫልዩ የከፒታሊስት ትርፍ የመባሰሉት አንደገና ብቅ እንዲሉ የሚያስችላቸውን መንገዱ ከፍተቀል የሚል በከፒታሊስት ምርትና በኮሞዲቲ ምርት መሀከል ያለውን ልዩነት ለመገንዘብ አልቻሉም:: የወዝአደሩ መደብ በሥልጣን ላይ ባለበት ወቅት ሊካሄድ የሚችለው የኮሞዲቲ ምርት ልውውጥና በከፒታሊስት ህብረተሰብ የሚመሳሰለውን ልውውጥ ጋር አንድ አደረጉት::

ሰባተኛው ስህተታቸው የዋጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫልዩ)ከማንኛውም የህብረተሰብ ታሪክ እድገት ጋር የተያያዙ፣ የማያቋርጥ ህግ የሆነና በኮሙኒስት ህብረተሰብ ውስጥ የልውውጥ ግኑኝነቶችን(ኤክስቸንጅ ሪለሽንሽፕ)የመቆጣጠር ተግባሩን ቢያጣ እንኳ በተለያዩ የምርት ዘርፎችና ሥራን በነሱ መሀከል እንዲከፋፈል የማድረጉን ተግባር ይቆጣጠራል በማለት የዋጋ ህግ(ሎፍ ኦፍ ቫሊዩ) ከኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ጋር የተያያዘ ታሪካዊ የእድገት ደረጃ እንዳለው አልተገነዘቡም:: በተወሰነ የታሪክ እድገት ደረጃ ላይ ዋጋና እንዲሁም የዋጋ ህግ ከኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ጋር የሚጠፉ ናቸው:: በዚያን ጊዜም ምርትን ለማምረት የሚፈሰው የሰው ኃልበትም በዋጋ ሳይሆን የሚለካው በቀጥታና ምርትን ለማምረት በተጠቀመባቸው ሰዓቶች ናቸው:: የሥራ ክፍፍል በምርት ዘርፎች ውስጥ የሚካሄደው እንደዚሁ በዋጋ ህግ ላይ በመመሥረት ሳይሆን የህብረተሰቡ የማቴሪያል ፍላጎት ማደግ ምርትን ለማምረት በሚፈሰው ኃልበት ላይ ቁጥጥር ይኖረዋል:: እንደዚሁም የህብረተሰቡ የማቴሪያል ፍላጎት ማደግ የምርትን እድገት ይቆጣጠረዋል:: ስለዚህም የዋጋ ህግ በምርት ውጤቶች ላይ መለኪያ ወይም ቁጥጥር ሊኖረው የሚችለው በከፒታሊስት ምርት ላይ ብቻ ነው:: በሶሻሊስት ህብረተሰብ የምርት መሣሪያዎች በህዝብ ቁጥጥር ሥር በሚውሉበት ጊዜ የዋጋ ህግ ያለው ሚና በጣም ውስን ነው:: ነገር ግን ከኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን መጥፋት ጋር የዋጋ ህግም ወሰን ሚናው እያከተመ ይሄዳል:: ይህ ማለት የዋጋ ህግ ቁጥጥር የሚኖረው(ሪጉሌት) የምርት መሣሪያዎች ግሳዊ እስከሆኑ ድረስ ብቻ ነው:: ከዚህ ስህተታቸው በመነሳት ብሔራዊ ኢኮኖሚ የተስተካከለ እድገት ህግ በእቅዱ መመሪያ የምርትን ትርፍ ማጣት ይሰርዘዋል የሚል መደምደሚያ ላይ ደረሱ በሶሻሊስት ኢኮኖሚ የምርት ትርፍ የሚለካው ከተናጠል የኢንዱስትሪ ዘርፎች



እንጻር ሳይሆን በጠቅላላው የብሔራዊ ኢኮኖሚ እድገት አንጻር ነው:: የምርት ትርፍ መገኘት ደግሞ ለጠቅላላ ኢኮኖሚው ማበደጊያ የሚውል፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎች ቴክኒካዊ መዋቅር በከፍተኛ ደረጃ ላይ እንዲያድግ ለማድረግና የህዝቡን የማቴሪያል ፍላጎት ለማሟላት እንዲሁም በየጊዜው በአንዳንድ ሁኔታዎች የተነሳ ብቅ ሊሉ ከሚችሉት የኢኮኖሚ ክሪዝ ለመዳን ያስችል ዘንድ ነው:: በጥሩ የምርት መሣሪያዎች ግሳዊ ስለሆኑ በአንድ ዘርፍ ያሉት የምርት መሣሪያዎች የሚያመጡት ትርፍ ምንም ትርፍ ሊያመጡ የማይችሉትን የምርት መሣሪያዎች ሊደጉሙና የቀረቀዘው ኢንዱስትሪ ክፍሎች ጉን በተስተካከለ የእድገት ደረጃ ላይ በመመስረት እንዲራመዱ ለማድረግ ነው::

ስምንተኛው ስህተታቸው የሶሻሊስት ኢኮኖሚን(ህብረተሰብ) ለመመሥረት በሚደረገው ጉዞ በገጠርና በከተማ፣ በኢንዱስትሪና በእርሻ፣ በጭንቅላት ሥራና በጉልበት ሥራ ያሉት ዋና የሆኑት ልዩነቶች ብቻ ሳይሆኑ ልዩነቶች ሙሉ በሙሉ ይወገዳሉ የሚል ስብጀክቲቭ ሃሳብ ስነዙ:: ለምሳሌ በሶሻሊስት ኢኮኖሚ አንድ በህዝብ ቁጥጥር ያሉ ሌላ በጋርዮሽ ያሉ የእርሻ መስኮች አሉ:: በእነዚህ መሀከል ያለው ልዩነት ዋና ሳይሆን በሁለተኛ ደረጃ የሚቀመጥ ነው:: በኢንዱስትሪና በእርሻ መሀከል ያለው ዋና ልዩነት እንዲወገድ፣ የጋርዮሽ እርሻዎች በዘመናዊ የምርት መሣሪያ ይጠቀሙ ዘንድ ኢንዱስትሪዎች ዘመናዊ የእርሻ መሣሪያዎች በመላክ እንዲሁም ለቤት የሚያገለግሉ ቁሳቁሶች በገበያ ላይ በማቅረብ በወዝአደሩና በገበሬው መሀከል ያለው ዋና ልዩነት እንዲወገድ ይደረጋል:: አንድነቱ ይጠነክራል:: ይህ ማለት ግን ጥቃቅን ልዩነቶች በሙሉ ይወገዳሉ ማለት አይደለም:: በኢንዱስትሪና በእርሻ መሐከል ተግባርቶ መሥራት አንድ አይደለም:: ሌላው እንኳ በኢንዱስትሪ ዘርፎች መሀከልም እንደዚሁ ጥቃቅን ልዩነቶች ይኖራሉ:: በከሰል ፋብሪካ ውስጥ በሚሰሩ ወዝአደሮችና በማሽን እየተረዱ በሚሠሩ ወዝአደሮች መሀከልም እንደዚሁ ልዩነቶች ይኖራሉ:: ግን እነዚህ ልዩነቶች እንደ ዋና ልዩነቶች የሚቆጠሩ ሳይሆን የወዝአደሩን አርሶአደሩን አንድነት የሚያሸከሩት ሳይሆን የሚያጠናክሩት በመሆናቸውና አላማቸውም ሙሉ በሙሉ የሶሻሊስትን ህብረተሰብ መሥርቶ ወደ መደብ የለሹ ህብረተሰብ ለመሸጋገር ስለሆነ ነው:: የሶሻሊስት ህብረተሰብ መሥርቶ ወደ መደብ የለሹ ህብረተሰብ ለመሸጋገር በሚደረገው ረጅም ጉዞ በገጠር ውስጥ የገጠሩን ህዝብ የባህልና የማቴሪያል ፍላጎት ሊያሟሉ የሚችሉ ከተማዎች ይቆረቆራሉ:: እንደዚሁም በጭንቅላት ሥራና በጉልበት ሥራ መሀከል ያለው የባህልና የቴክኒክል ዋና ልዩነት ይወገዳል:: ይህ ማለት ግን ጥቃቅን ልዩነቶች በሙሉ ይወገዳሉ ማለት አይደለም:: በአስተዳዳሪዎችና በወዝአደሩ መሀከል ያሉት የሥራ ሁኔታዎች ሊወገዱ አይችሉም:: በወዝአደሩና በአስተዳዳሪዎች መሀከል ያለው ግኑኝነት እንደ ከፒታሊስት ህብረተሰብ ሳይሆን

በጓደኛነት ላይ የተመሠረተ፣ የወዝአደሩ በማኔጀሮች በነቀት የሚታይ ባይሆን ሁለቱም
የሶሻሊስትን ህብረተሰብ መሥርተው ወደ መደብ የለሹ ህብረተሰብ ለመጓዝ ግንኙነታቸው
ም በቀል ያዘለ ባይሆን በወንድማማችነት፣ በጓደኛነት ላይ የተመሠረተ ይሆናል::

ዘጠነኛው ስህተታቸው ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የዓለም ሁኔታ ስለተለ
ወጠ በካፒታሊስት ሀገሮች መሀከል ጦርነት አይነሳም:: ከዚህም የተነሳ ጦርነት የማ
ይቀር መሆኑን አቀሏል በማለት ጦርነት ከግል ሀብት ጋር የተያያዘ፣ የካፒታሊስት አገ
ሮች ርካሽ ጉልበት፣ ርካሽ የጥሬጥሬ ሀብትና ለሸቀጣቸው ማራገፊያ ለመፈለግ በሚያደር
ጉት መራኮት የሚነሳ መሆኑን ዘነጉ:: አንደኛውና ሁለተኛው የዓለም ጦርነት የተነሱ
ት በራሳቸው በኢምፔሪያሊስት አገሮች በነበረው የጥቅም ግጭት፣ በመሀከላቸው በተደረገ
ው አሽቅድምድም ነበር:: በእርግጥ በአሁኑ ጊዜ ይህ አኪሔት የሆነ መልክ ባይዝም፣
የቀዝቃዛ በመስልም በካፒታሊስት አገሮች ያለው ኢኮኖሚክ ክራይሲስ በርሻውን እያጧደፈው
ሲሄድ ገበያው በአንጉ እንተያዘበት(ሞኖፖላይዝድ) ሲሄድ መፈናፈኛ ቢያጣ ጦርነት የማ
ይቀረው ህግ ነው:: በሌላ በኩልም በአንደኛው ዓለም ጦርነት ወቅትና ከዚህ ጦርነት
ወዲህ የሶሻሊስት ካምፕ ብቅ ባልም ከዚህ ሁኔታ የካፒታሊስት ካምፕና በሶሻሊስት ካም
ፕ ቀና(ዋጀር) ቅራኔ ብቅ ብሎ ቢወጣ የሁለተኛው ዓለም ጦርነት ዋናው ምክንያት በሁ
ለቱ ተፃራሪ ካምፖች መሀከል ያለው ባይሆን እራሱ በኢምፔሪያሊስት አገሮች የነበረው
የጥቅም ግጭት ነበር:: በተግባርም እንደታየው አሜሪካን፣ እንግሊዝና ፈረንሳይ ከሶ
ቭየት ህብረት ጋር ጊዜያዊ አሊያንስ ፈጥረው የጀርመንን ኢምፔሪያሊዝምን ተዋግተዋል::
ግን በቲዎሪ ደረጃ ቢታይ በሶሻሊስትና በካፒታሊስት አገር ያለው ቅራኔ በመጀመሪያ ደ
ረጃ የሚቀመጥ ይሆናል:: ነገር ግን ከሁለተኛው ዓለም ጦርነት ወዲህ የዓለም ሁኔታ
ቢለወጥም፣ የሃይል አሰላለፍ ቢቀያየር፣ የሶሻሊስት ሰፈር መጠናከርና እንዲሁም ለሰላ
ም የሚታገሉ ሃይሎች ቁጥር በጠቅላም ይህ ማለት ግን ወደፊት የሚመጡን የኢምፔሪያሊ
ስቶች ጦርነት ያስቀረዋል ማለት አይደለም:: ወይንም ደግሞ ይህን የማይቀረውን ጦር
ነት ወደህዝባዊ ጦርነትም ለመለወጥ የሚደረግ ትግልም ካፒታሊዝምን ደምስሶ ሶሻሊዝምን
ይተካል ማለት አይደለም:: (ዋና አላማው) ለዚህ ለሰላም የሚደረገው ትግል ዋናው
አላማ ሰላም እንዳይደፈርስና ይህን የማይቀር ጦርነት ለማዘግየት የሚደረግ እንቅስቃሴ
ነው:: ግን ደግሞ ይህ ማለት ለወደፊት የኢምፔሪያሊስት ጦርነት አይገኝ እየሆነ ቢ
መጣ(አኩዮት) ለሰላም የሚደረገው ትግልም ይህን ጦርነት ወደህዝባዊ ጦርነት ለመለወ
ጥና ካፒታሊዝምን ለመደምሰስ የሚደረግ እንቅስቃሴም አይሆንም ማለት አይደለም:: ለ
ሰላምና ለዲሞክራሲ የሚታገሉ ሃይሎች የኢምፔሪያሊዝምን አደገኛነት እየተረዱት ቢመጡ፣
ኢምፔሪያሊዝም ሰላም አደፍራሽ መሆኑን በይበልጥ እየተገነዘቡት ቢመጡና ጦርነትም



እየገፋ ቢመጣ ይህንን ጦርነት ወደህዝባዊ ጦርነት የመለወጥ ሁኔታ ይፈጠራል:: ለዚ
ህ ደግሞ ትልቅና ሰፊ ፕሮፓጋንዳ ማካሄድ ያስፈልጋል:: ለማንኛውም ሌላ ጦርነት እ
ንዳይነሳ ከተፈለገ የግዲታ ኢምፔሪያሊዝምን መደምሰስ ያስፈልጋል:: ኢምፔሪያሊዝም
እስካለ ድረስ ጦርነት የማይቀር ነው:: ሌኒን ጦርነት ከግል ሀብት ጋር የተያያዘና
የሱ ውጤት መሆኑንና ኢምፔሪያሊዝም እስካለ ድረስ የማይቀረው ህግ መሆኑን ሲያሳይ:-

> "War is a law of capitalism as economic crises and uneven economic and political development are laws of Capitalism. War is not standing in contradication with private ownership, but its inevitable aftermath."

**መሠረታዊ የካፒታሊዝምና የሶሻሊዝም የኢኮኖሚ ህጎችና የአድርባዮች ስህተት**

የካፒታሊስት መሠረታዊ የኢኮኖሚ ህግ የካፒታሊዝምን የተወሰነ ጠባዩን ወይንም
ክፍሉን የሚወስነው ብቻ ባይሆን ጠቅላላና ዋና ጠባዩን፣ እንዲሁም በምርት ሂደት ውስ
ጥ የሚያልፍባቸውን የእድገት ደረጃዎችንም ጭምር ነው:: የዋጋ ህግ (ሎው ኦፍ ቫሊዩ)
የካፒታሊዝምን ጠቅላላ አረማመዱና ጠባይ ስለማይወስን የካፒታሊስት ምርት መሠረታዊ
ህግ ሊሆን አይችልም:: የዋጋ ህግ በመጀመሪያ ደረጃ ከእቃ ምርት ጋር የተያያዘ
(ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን) ከካፒታሊስት ምርት በፊት የነበረ የኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ዋና ህግ
ነው:: በሌላ በኩል በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ (የኮሌክቲቭና የህዝብ ሀብት በሚገኝበ
ት ኢኮኖሚ) ወይንም ደግሞ የወዝአደሩ መደብ ሥልጣን ጨብጦ ለሶሻሊስት ኢኮኖሚ የማቴ
ሪያል ሁኔታዎችን በማጥቀር ካፒታሊዝም ቢያልፍ የእቃ ምርት ስለሚኖር ከዚህም አያይዞ
የዋጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫሊዩ) ወሰን ግን አለው:: ነገር ግን ይህ ማለት በካፒታሊስ
ት ምርት ውስጥ በሩ ያለ ተግባር የለውም ማለት አይደለም:: የተመረቱትን እቃዎች
ዋጋ ለመተመን፣ የወዝአደሩን ጉልበት ዋጋ፣ የሚመረተ ጥሬጥሬ(ሮው ማቴሪያል) ዋጋ
ለመወሰን ካፒታሊስቶ በስራው ይጠቀምበታል:: ይህም ሆኖ የካፒታሊስት መሠረታዊ ህግ
እድሉን ሊወስነው የሚችል አይደለም::

እንደዚሁም የውድድር ህግና(ሎው ኦፍ ኮምፒትሽን) የምርት አናርኪ(አናርኪ ኦፍ
ፕሮዳክሽን) የካፒታሊስት ስልተምርት ጠባይ ቢሆንም ቅሉ በጠቅላላው የካፒታሊስትን
ስልተምርት ወደ ሞኖፖሊካፒታሊዝም መለወጥ አይወስንም:: የካፒታሊስት ምርት አጠቃላ
ይ ባህሪይና አረማመድ አይወስኑም:: ስለዚህም መሠረታዊ ህግ ሊሆኑ አይችሉም::
መሀከለኛ ፕሮፊትም(አቨረጅ ሬት ኦፍ ፕሮፊት) የካፒታሊስት ምርት መሠረታዊ ህግ
አይደለም:: ይህ መሀከለኛ ትርፍ ከኦርጋኒክ ካፒታል ማለት የምርት መሣሪያዎችና

ለሥራ የወጣው ካፒታል ቀንጅት(ኮንስታንት ቶ ቨሪአብል) ጋር ሲነፃፀር ይህ ኦርጋኒክ
ካፒታል እያደገ ሲሄድ መሀከለኛ ትርፍ እያሽቆለቆለ ይወርዳል:: መሀከለኛ ትርፍ
የአንድ የምርት ዘርፍ ውጤት ሳይሆን ከሁለት በላይ የሆኑ የምርት ዘርፎች ውጤት የሆ
ነ የነዚህ ድምር ክፍያ ነው:: ስለዚህም የካፒታሊስትን ምርት ጠቅላላ አረማመድ የ
ማይወስን በመሆኑ መሠረታዊ ህግ ሊሆን አይችልም::

ቡርዣው ከፍተኛ ትርፍ ለማካበትና የስልተምርት ቅንብሮሽ ወይንም በአጠቃላይ አ
ነጋገር ምርት ስያደርጥ እንዲመረትለትና በገበያ አውጥቶ ትርፍ ለማካበት ይችል ዘንድ
ከፍተኛ ትርፍ(ማክሲማም ፕሮፊት) ይጠይቃል:: ቡርዣው በመሠረቱ የሌላውን በላተኛ
ህዝብ ፍላጎት ለማርካት የሚያመርት ሳይሆን ምርቱን በከፍተኛ ዋጋ በመሸጥ ትርፍ ለማ
ግኘት ነው::ምርቱ ከፍተኛ ትርፍ እስካላገኘለት ድረስ የኢንዱስትሪው ስያደርጥ መንቀ
ሳቀስ ህይወት ውስን ይሆናል::ወይንም ከፍተኛ ትርፍ ለማግኘት የሚችልበትን ዘዴ ይ
ተምናልቁ:ማለትም ኢንዱስትሪውን በከፍተኛ ቴክኒካዊ መዋቅር ላይ እንዲንቀሳቀስ ያደር
ጋል::ይህ የፈለገውን ከፍተኛ ትርፍ ካላመጣለት ደግሞ በጉልበት ስራ ላይ ያተኩራል::
ያም ሆነ ይህ ካፒታሊዝም ወደ ሞኖፖሊ ካፒታሊዝም ሊሸጋገር የቻለው ይህን ከፍተኛ ት
ርፍ በማካበት ነው::የጠቅላላውንም የካፒታሊዝምን ዕድገት አረማመድ ጠባይ የሚወስነው
ይኸው ክፍል ነው::ስለሆነም የካፒታሊስት መሰረታዊ ህግ ነው::

የሶሻሊስት ኢኮኖሚ መሰረታዊ ህጎችስ ምንድነው? የሶሻ ሊስት ኢኮኖሚ መሠረታዊ
ህግ የማያቋርጥ የማቴሪያልና የባሕል ፍላጎትን ለሟሟላት ምርትን በማስፋፋትና ይህንን
ም ምርት ከሕብረተ ሰቡ ፍላጎት ጋር ለማባደግ በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ የተመሰረተ ነው::
በመሆኑም የሶሻ ሊስት ኢኮኖሚ የህብረተሰቡን ትብቅብቂ ፍላጎት ማቀበብ ሳይሆን ፍላጎ
ቱን ከኢኮኖሚው እድገት ጋር ለማሟላት የማያቋርጥ የምርት እድገት እንዲኖር ማድረግና
የማያቋርጥ የቴክኒክል እድገት በዓይነትና በጥራት ጥሩ የሆነ ምርት ማምረት ነው::
የተስተካከለ ብሔራዊ ኢኮኖሚ እቅድ አስፈላጊውን ውጤት ሊሰጥ የሚችለው የዚህ እቅድ
መወጠን በመጀመሪያ ደረጃ ለምን ዓላማ እንደሆነ ሲታወቅ ብቻ ነው:: ማለትም የተስ
ተካከለ የኢኮኖሚ እቅድ ውጤት የሚታወቀው በመሠረታዊ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ህግ ላይ ተ
መሥርቶ ሲከናወን ብቻ ነው:: ይህም ሌላ ሳይሆን የህብረተሰቡን የማቴሪያል ፍላጎት
ከብዛት ወደ አይነት ለመለወጥ ከፍተኛ ትግል ሲደረግ ነው:: ይህንንም ለማድረግ ከ
ፍተኛ የቴክኒክ መዋቅር መጣል ሲቻል ብቻ ነው::

## ሌሎች ስህተቶች

ሰው የኢኮኖሚ ህጎችን በማወቅ ለህብረተሰብ ጥቅም በማዋል ድርጊታቸውን በመለ
ወጥ ሊጠቀምባቸው ችሏል:: ነገር ግን ይህ የኢኮኖሚ ህጎችን ማወቅ ህብረተሰብ ለሶ
ሻሊዝምና ለኮሙኒዝም የኢኮኖሚ ሥርአቶች ብቻ ሊጠቀምባቸው ይችላል በማለት ስህተተኛ
ግምገማ አቀረቡ::

ለምሳሌ የቡርዣውን አብዮት የተመለከትን እንደሆነ ቡርዣው ፊውዳሊዝምን በመወ
ርወር አዲስ የምርት ግኙኝነቶችን በመፍጠር ከዚህ ወደ ኋላ ቀር ስልተምርት የምርት
ሃይሎች ተላቀው ከአዲሱ የምርት ግኙኝነቶች ጋር እንዲቀናጁ አድርጓል:: በእርግጥ
ይህንን ሲያደርግ ከሌላው የህብረተሰብ ጥቅም አንፃር በመመልከት ሳይሆን ከራሱ የመደ
ብ ጥቅም አንፃር በማጤን ነው:: ስለሆነም ቡርዣው ህብረተሰብ ባለፋት የህብረተሰብ
እድገት ደረጃዎች ከፍተኛ አብዮታዊ ሚና በመጫወት አሮጌው የምርት ግኙኝነትን በበርቦ
በጣም ፈጣንና መሠረታዊ የቴክኒክ ለውጥ በማድረግ አዲስ የኢኮኖሚ ግኙኝነቶች የአሮጌ
ውን ቦታ እንዲወስዱ በማድረግ ነው:: ይህንን ሲያደርግ አዲስ የኢኮኖሚ ህጎችን በ
ማግኘት(ዲስከቨር) የነዚህን ኢኮኖሚ ህጎች ድርጊት በመለወጥና በሥራ ላይ በማዋሉ ነው::
እንደዚሁም የወዝአደሩ የወዝአደሩ መደብ ሥልጣን ሲጨብጥ አዲስ የምርት ግኙኝነቶችን
ሲፈጥር እነዚህ አዲስ የምርት ግኙኝነቶች ፈጣን ከሆነው የምርት ሃይሎች ጋር እንዲቀ
ናጁ በማድረግ ነው:: ስለዚህም በመደብ በተከፋፈለ ህብረተሰብ የኢኮኖሚ ህጎች በሥ
ራ ላይ መዋል መደባዊ ይዘት አለው:: አሮጌው የምርት ግኙኝነት አዲሱን የምርት ግ
ኙኝነት ወደኋላ ለመጎተት ትንቅንቅ ሲይዝ ከአሮጌው መደብ በእርዩ አስተዋይነት ወደፊ
ት የሚመለከተው ተራማጅ መደብ የኢኮኖሚ ህጎችን ለህብረተሰብ ጥቅም እንዲውሉ ያደርጋ
ቸዋል:: ነገ ከነዚህ መደቦች ሁሉ የወዝአደሩ መደብ እውነተኛ አብዮታዊ ሃይል ነው::
አሮጌውን የምርት ግኙኝነት በአዲስ የሚተካው የድሮውን ብዝበዛ ሥርአት በአዲስ የብዝ
በዛ ስርአት ለመተካት ሳይሆን ይህንን ወርሶ ለማጥፋትና ከዚህ በፊት የተበዘበዙ ሌሎ
ች የህብረተሰብ ክፍሎችንም ጥቅም ለመጠበቅ ሰው በሰው የማይበዘበዝበት የምርት ግኙኝ
ነት ለመፍጠር ነው:: ከዚህም ወደ መደብ የለሽ ህብረተሰብ ለመሸጋገር ነው:: ህ
ብረተሰብ በቀደሙ በሸሊዝም በፊት በነበሩት ኢኮኖሚያዊ ሥርአቶች የኢኮኖሚ ህጎችን ድ
ርጊት በጥቅም ላይ ባያውሉ፣ ድርጊታቸውን ባይቆጣጠር ኖሮ ከአንደኛው የኢኮኖሚ ሥርአ
ት ወደ ሌላኛው የኢኮኖሚ ሥርአት ለመሸጋገር ባልተቻለ ነበር:: ምክንያቱም ከአሮጌ
ው ወደ አዲሱ ለመሸጋገር መጀመሪያውኑ ከአዲሱ የኢኮኖሚ ሥነሥርአት ጋር የሚቀናጅ

የማቴሪያል ሁኔታዎች በአሮጌው ውስጥ መረገዝ አለባቸው:: ህብረተሰብ እነዚህን በአሮ
ጌው ሥርአት ውስጥ የተረገዙትን ሁኔታዎች ከቡርዥ አብዮት በኋላ ወደ አዲስ የምርት
ግኙኝነት በመለወጥ ከአዲሱ ሁኔታ ጋር እንዲቀነባበሩ ያደርጋቸዋል:: እንግዲህ ህብ
ረተሰብ በመደብ ከተከፋፈለ ወዲህ(ከባሪያ እስከ ቡርዥዋዚ) ከባሪያ ወደ ፊውዳሉ፣ ከ
ፊውዳሉ ወደ ቡርዣው ወደ ሶሻሊስት አብዮት የተካሄዱት አብዮታዊ ለውጦች ህብረተሰብ
በአያንዳንዱ የእድገት ደረጃ የኢኮኖሚ ህጎችን ድርጊት በመለወጥና በተግባር ላይ በማ
ዋል ከህሊናው ቁጥጥር ውጭ ሳያውቀው ለሚቀጥለው አዲስ ህብረተሰብ የማቴሪያል ሁኔታ
ዎችን በማዘጋጀት ነው::

በሶሻሊስት ህብረተሰብ ውስጥ የምርት መሣሪያዎች እንደኮሞዲቲ ይቆጠራሉ? ኮሞ
ዲቲ ማለት ምን ማለት ነው? ኮሞዲቲ የሚሸጥና የሚለወጥ ባለቤቱ በሚሸጥበት ጊዜ በ
እቃው ላይ ያለውን ሞኖፖልም ወይም ህጋዊ መብቱን የሚያጣበት ነው:: እንደዚሁም እ
ቃውን የገዛው ሰው ለሌላ ሰው ሊሸጠውና ሊለውጠው ባለቤትነቱን ያገኛል:: በሶሻሊስት
የኢኮኖሚ ሥርአት፣ ወዛደሩና የምርት መሣሪያዎች፣ ምርቶችም ጭምር እንደአንገባ በማ
ይተያዩበት ህብረተሰብ ውስጥ፣ ወዛደሩና ሌላው ጭቁን የነበረው የህብረተሰብ ክፍል
የምርት መሣሪያዎች በእውነትም የራሳቸው መሆኑን በሚረጋበት ህብረተሰብ ውስጥ የምርት
መሣሪያዎች የህዝብ ስለሆነ አይሸጡም አይለወጡም:: አገልግሎታቸውም ለህዝቡ ጥቅም
ስለሆነ መንግሥት በእቅድ በተግባር ላይ የሚሠማሩበትን መንገድ ይተልማል ማለት ነው::
ግን ይህ ማለት የሶሻሊስት መንግሥት ከውጭ የንግድ ግኙኝነት ጋር ባለው መሠረት የም
ርት መሣሪያዎችን በሚሸጥበት ጊዜ እንደ ኮሞዲቲ አይቆጠሩም ማለት አይደለም:: ወደ
ውጭ የሚሸጡት የምርት መሣሪያዎች የመሸጥና የመለወጥ ጠባይ ስለአላቸው ኮሞዲቲ ናቸ
ው:: ይህም ማለት መንግሥት በሚሸጥበት ጊዜ ባለቤታዊ ይዞታን ያጣል ማለት ነው::

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የዋጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫሊዩ) በጥሬጥሬ ሀብት ላይ
(ረው ማቴሪያልስ) የመቆጣጠር ተግባር (ሬጉሌቲንግ ፋንክሽን) አለው? የዋጋ ህግ በጥሬጥ
ሬ ሀብት ላይ(አግሪካልቸር ረው ማቴሪያልስ) የመቆጣጠር ተግባር ያለው በኢኮኖሚ ሥር
አት ውስጥ ልቅ ነፃ ንግድ እስከለ ድረስ፣ ኢኮኖሚው በእቅድ የሚተለም መሆኑ ቀርቶ
የገበያ ውድድርና የምርት አናርኪ የሞላበት ሥርአት ከሆነ የዋጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫሊ
ዩ) በነዚሁ የጥሬጥሬ ሀብት ላይ የመቆጣጠር ተግባር (ሬጉሌቲንግ ፋንክሽን) አለው::
በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ግን በህዝብና በኮሌክቲቭ ሥር የሚተዳደር የኢኮኖሚ መዋቅር ባለበት
ከጋርዮሽ እርሻ የሚመረተው የጥሬጥሬ ሀብት(አግሪካልቸር ረው ማቴሪያልስ) በእቅድ በተተ
መነ ዋጋ መሠረት በገበያ ላይ ይቀርባል:: ይህ ማለት ምንም እንኳ በጋርዮሽ እርሻ



የሚመረቱት የጥሬጥሬ ሀብት ባለቤትነት ቢኖራቸውም አርሶአደሩ ገቢውን ያፈሰበታል፣
መጀመሪያዎ ጥሬጥሬዎችን የሚገዛው በገንዘብ ስለሆነ በዘፈቀደ ዋጋ ሊተመንባቸው የሚ
ሸጡ አይደሉም:: ሁለተኛ የሚመረተው ምርት እንዲሁ ልቅ ባይሆን ከህዝቡ የማቴሪያል
ፍላጎት ጋር እየተነፃፀረ ነው:: ሶስተኛ እነዚህን የጥሬጥሬ ሀብት ለማምረት የጋርዮ
ሽ እርሻዎች የሚጠቀሙባቸው መሣሪያዎች በነሱ ቁጥጥር ስር (ገሳዊ ይዞት) ባይሆኑ በመንግ
ሥት ቁጥጥር ሥር የሆኑ የህዝብ ሀብት ናቸው:: በመሆኑም የዋጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫሊዩ)
የመቆጣጠር ተግባር ባይሆን ያለው ከላይ የተጠቀሱት ፋክተሮች እሱን ይቆጣጠሩታል::
ይህ ማለት ግን የጥሬጥሬ ሀብት(አግሪካልቸራል ፕሮዳክትስ) ገሳዊ ይዞት እስከለው ድረ
ስ የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥ የዋጋ ህግ ምንም ተግባር የለውም ማለት አይደለም:: ልቅ
ያልሆነ ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ስለአለ በነዚህ ምርት ላይ የተወሰነ ሚና ይጫወታል:: ም
ርቱ ስለሚሸጥ ስለሚለወጥ በገበያ ሂደት ውስጥ የምርቱን ዋጋ እንፍሉየንስ ያደርጋል::

በሶሻሊስት ሥርአት ውስጥ የምርት ግኙኝነቶች የምርት ሃይል ተቀፃ(ኮምፐንነት
ፖርትስ) ናቸው የሚል የምርት ግኙኝነቶችን ዝቅ የሚያደርግ የምርት ሃይሎችን በከፍተኛ
የሚመለከት ስህተተኛ ሃሳብ ስነዛሩ:: በመቀጠልም በሶሻሊስት ሥርአት ውስጥ ''በተጻ
ራሪ የቆመ መደቦች'' ስለሌሉና የምርት ግኙኝነቶች የምርት ሃይሎችን እየተጻረሩ ስለሚ
ያድጉ የምርት ግኙኝነቶች ማገናኛውም እራሳቸውን የቻሉ ሚና ያጣሉ ከዚህም የተነሳ ለእድ
ገት ወሳኝ ፋክተር መሆናቸውን በማቆም በምርት ሃይሎች በመጥ ተቀፃ ይሆናሉ የሚል
ነው::

ይህን ስህተት እናብይ:—

ማርክሲስቶች ስለምርት ግኙኝነቶች በሚያወሱበት ወቅት ስለማንኛውም የምርት ግኙ
ኙነት ሳይሆን፣ ስለአሮጌው የምርት ግኙኝነትና ይህ ያረጀው የምርት ግኙኝነት በፍጥነት
ከሚያድገው የምርት ሃይል ጋር አለመጣጣሙን በአሮጌው የምርት ግኙኝነት ላይም አዲስ የ
ምርት ግኙኝነት በመፈጠር ቦታውን ይወስዳል:: ይህ አዲስ የምርት ግኙኝነት ቀባይል
ከሆነው የምርት ሃይል ጋር በመቀናጀት ለምርት ሃይሎች እድገት ወሳኝ ሚና ይጫወታሉ::
ከለበለዚያ ግን በአሮጌው የምርት ግኙኝነት አዲስ የምርት ግኙኝነት ካልተተካ የምርት
ሃይሎችን ወደኋላ በመጎተት ለወደፊት እድገት እንቅፋት ይሆናሉ:: ለምሳሌ በአንድ
የተወሰነ የህብረተሰብ እድገት ደረጃ ላይ አሮጌው የምርት ግኙኝነትና ከሱ ጋን እያደገ
የሚሄደው አዲሱ የምርት ግኙኝነት መሀከል ያለው ቅራኔ በስሱ ሲፈነዳ የሶሻል አብዮት

ይከሄዳል። ከዚህ የሶሸል አብዮት በኋላ በአሮጌው የምርት ግኑኝነት ላይ አዲስ የምርት ግኑኝነት በመፍጠር ለምርት ሃይሎች ወዳበር፣ ወደፊት ማደግና ከሱም ጋር ለመጣጣም ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። ነገር ግን ካሰዚህ የሶሸል አብዮትና አዲሱን የምርት ግኑኝነት ከአሮጌው አስከል ተሳቀቀት ጹረስ የምርት ሃይሎች በመዳበር ፈንታ አዚያው ይቆረዛሉ። ወደፊት በመገስገስ ፈንታ አዚያው በሉበት አንዲረገሙ ይገደዳሉ። ነገር ግን እነዚህ የተፈጠሩት አዲስ የምርት ግኑኝነቶች አዲስ እንደሆኑ ይቀራሉ ማለት አይደለም። ከወጣት ወደ ጉልማስ፣ ከጉልማስ ወደ ሽማግሌ አያረጁ ሲሄዱ የምርት ሃይሎችን እድገት ወደኋላ በመጉተት ለእድገት እንቅፋት ይሆናሉ። (ከሶሸሊስት ህብረተሰብ ሌላኛ ከዚያም ለአዲሱ ቦታቸውን በመልቀቅ ጊናቸው ያከትማል። ስለሆነም በማንኛውም ህብረተሰብ ውስጥ ሆነ በሶሸሊስት የምርት ግኑኝነቶች አራቢቸው ችለው ለብቻቸው የቆሙ ሳይሆኑ አንደኛው ከአንደኛው ጋር የተያያዘ ነው። ሁለቱም የአንድ ህብረተሰብን ኢኮኖሚ ስርአት የሚፈጥሩ ስለሆኑ አንደኛው ከአንደኛው ሊነጣጠል አይችሉም። በሰዚህም አንደኛው በአንደኛው ተፅዕ ዘተኛ ጊናውን በማጣት ደንደኛው ተቀቀያ ይሆናል ማለት ማርክሲዝምን መጻረር ይሆናል። ምክንያቱም የህብረተሰብ ኢኮኖሚ ሥርአት ሉኖር የሚችለው በሁለቱ ዱምሬዊ ማለት በምርት ግኑኝነቶች(የሰው ተሰው በምርት ሂደቶች ውስጥ የሚፈጥረው ግኑኝነት)ና ሰው ከተፈጥሮ ጋር ባለው ግኑኝነት ላይ በመመርከዝ ነው። በሌላ በኩል የሁለቱ ቅንብር የህብረተሰብ ሥርአት መሠረት ስለሆነ ከዚህ መሠረት የፖለቲካ መዋቅሩ ይፈልቃል። አንደኛው በአንደኛው ቢቆም፣ ምንም አይነት ጊና በይኖረው መሠረቱም በሉም ሳእሳይ መዋቅሩም አይኖርም ማለት ነው። ስለሆነም በማርክስ አባባል፦

> "In the social production of their life men enter into definite relations that are indispensable and independent of their will, relation of production which correspond to a definite stages of development of their life of their material productive forces. The sum total of these relations of production constitutes the economic structure of society".

ይህም ማለት ማንኛውም ህብረተሰብ ሶሸሊስት ህብረተሰብንም ጨምሮ የራሱ የሆነ የኢኮኖሚ መሠረት አለው። ይህም የኢኮኖሚ መሠረት ሌላ በይሆን የምርት ግኑኝነቶችና የምርት ሃይሎች ዱምር ነው።

ሌላው ስህተት ከሶሸሊዝም ወደ ኮሙኒዝም ለመሸጋገር የምርት ሃይሎችን ራሽናል በሆነ መንገድ መጠቀም ያስፈልጋል የሚል ነው።

ከሶሸሊዝም ወደ ኮሙኒዝም ለመሸጋገር የምርት ሃይሎችን ''ራሽናል'' በሆነ ጠበጥ መልስ በማይሰጥ መንገድ ሳይሆን የምርት መሣሪያዎች በተሩጠነና በከፍተኛ ቴክኒክ በተመሠረተ ላይ በማስፋፋት፣ የብሔራዊ ኢኮኖሚውን በማያቋርጥ እንዲያድግ ማድረግ ከዚህም በማያያዝ የህብረተሰቡን የማቴሪያል ፍላጎት ለማሟላት በመቻል ነው። በሶሸሊስት ህብረተሰብ ውስጥ የሚገኙትን የጋርዮሽ አርሸያች(ኮሌክቲቭ) ቀስ በቀስ ወደህዝብ ሀብት መለወጥና የኮሞዲቲ ልውውጥ(ኮሞዲቲ ሰርኩሌት) ወደ የእቃ—ተእቃ ልውውጥ (ፕሮዳክት ኤክስቸንጅ) እንዲካሄድ በማድረግ ነው። ቀጥሉም ጠቅላላው የኢኮኖሚ ዘርፍ ለህዝቡ ጥቅም እንዲውል በአንድ ማእከላዊ ድርጅት ቁጥጥር ሥር ማድረግ፣ በተጨማሪም የህብረሰቡ በህል የሚበለጽግበትና ጠቅላላው የህብረተሰብ የሰውነትና የአእምሮ ችሎታዎች የሚዳብሩበትን ማለትም ትምህርት ለህብረተሰቡ በሙሉ እንዲዳረስ በማድረግና አያገዳኝ የህብረተሰብ ክፍል በፍላጉቱ በአንድ የሥራ መስክ ውስጥ ሳይታሰር እያቀያየረ እንዲሰራ ማድረግ ናቸው። ስሬ ትምህርት እንዲያገኙና የህብረተሰብ በህል እንዲዳብር ደገሞ የሥራ ሠአቶች ማጠር አስፈላጊ ይሆናል። ብዙ ትርፍ ሰዓቶች ካገኙ ደግሞ አጠቃላዩና አእምሮውን የሚያነፅበት፣ ሰውነቱን የሚያዳብርበት ትምህርት እንዲያገኙ ይደረጋል። ቢያንስ እነዚህ ስስት ቅደመ ሁኔታዎች ሳይሟሉ ''ራሽናል''በሆነ መንገድ ወደ ኮሙኒስት ህብረተሰብ ለመሸጋገር አይቻልም።

ሌላው ስህተት አያገዳገቱ የህብረተሰብ እድገት (ፊውዳሊዝም፣ ካፒታሊዝም፣ ሶሻሊዝም) እራሱን የቻለ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ አለው በማለት የህብረተሰብን አጠቃላይ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ የሚጻረር፣ ማርክሲዝምን የሚጻረር ሃሳብ ሰነዘሩ። ነገር ግን አያገዳገቱ የህብረተሰብ እድገት(ባርያ፣ ፊውዳል፣ ቡርዣ፣ ሶሸሊስት) እራሱን የቻለ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ በይሆን ያለው እነዚህን በአጠቃላይ የሚመረምር፣ የህብረተሰብ ፎርሜሽኖችን የሚያጠና አጠቃላይ የፖለቲካ ኢኮኖሚ ህግ አለ። ኢንገልስ ይህን ሲያስይ፦

> "Political economy is the science of the conditions and forms under which the various human societies have produced and exchanged... Hence, political economy investigates the laws of economic development not of any one social formation, but of various social formations".

ማንኛውም ሶሸል ፎርሜሽን በተወሰነ የኢኮኖሚ እድገት ደረጃ ላይ በራሱ የኢኮኖሚ ህጎች ብቻ ሳይሆን የሚገዛው ለሶሸል ፎርሜሽኖች አጠቃላይ በሆነው የኢኮኖሚ ህጎችም ጭምር ነው።

ማለትም በምርት ሃይሎችና በምርት ግንኙነቶች ቅንጅትና የእነዚህም በተለያዩ የህብረተሰብ እድገት ደረጃዎች በሳቸው የእድገት ሂደት ነው:: ስለዚህም ምንም እንኳ የህብረተሰብ እድገት በራሱ የተወሰነ ህግ ቢከፋፈልም ቅሉ እያንዳንዱን እድገት የሚያስተሳስር የጋራ የሆነ የኢኮኖሚ ህግ አለ:: ለማብራራት ያህል ለምሳሌ የካፒታሊስት ኢኮኖሚ መሠረታዊ ህግ ከፍተኛ ትርፍ ማካበት ነው:: እንዲሁም ከዚህ ህግ ጋር ጎን ለጎን ተያይዘው የሚሄዱ የቀጋ ህግ(ሎው ኦፍ ቫልዩ)፣ ውድድር (ሎው ኦፍ ኮምፒትሽን) እንዲሁም ሌሎች የካፒታሊስት ምርት ጠባዮች አሉት:: ነገር ግን በመጀመሪያ እነዚህ ስፔሲፊክ ሁኔታዎች ከመኖራቸው በፊት እነዚህን የሚወስኑት የምርት መሣሪያዎች ገሳጭ ይዞት እንዲኖር ያስፈልጋል:: ይህ ካለ ደግሞ የካፒታሊስት ምርት ይኖራል ማለት ነው:: ለካፒታሊስት ስልተምርት መኖር ደግሞ የምርት ግንኙነትና የምርት ሃይል ቅንጅት ያስፈልጋል::

እንደዚሁም የሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርአት የራሱ የሆነ ስፔሲፊክ ህግ አለው:: ሶሻሊዝም ቀና አላማው ከፍተኛ ትርፍ ማካበት ሳይሆን የህብረተሰቡን የማቴሪያልና የባህል ፍላጎት ለማሟላት የምርት መሣሪያዎች በከፍተኛ ቴክኒክ ላይ በመመሥረት በማያቋርጥ ምርት ከብዛት ወደ አይነት በመሸጋገር ማምረት ነው:: ነገር ግን ያኛውም ይህ አንዱ አጠቃላይ የሚያገናኛቸው የኢኮኖሚ ህግ አለ:: ይህም የምርት ግንኙነትና የምርት ሃይሎች በአንድ ኢንተግሬል ክፍል መጠቃለልና እነዚህን ሁለቱን የሚያቀናጀው ህግ በእድገት ሂደት ውስጥ የህብረተሰብን ኢኮኖሚ ስርአት መፍጠር ነው:: ተጠማሪው የአድርባዮች ስህተት የማርክስ ''ሪፕሮዳክሽን ቲዎሪ''ለካፒታሊስት ምርት የሚያገለግል እንጂ ለሌሎች የህብረተሰብ ፎርሜሽኖች የሶሻሊዝምን ጭምር አጠቃሎ ተቀመጠ(ቫሊዲቲ) የለውም የሚል ነው::

ሪፕሮዳክሽን ማለት ምን ማለት ነው? ሪፕሮዳክሽን ያል በቃል ቢተረጎም እንደገና ማምረት፣ ምርትን መሳልስ ማምረት፣ የምርት ሂደትን(ፕሮሴስ ኦፍ ፕሮዳክሽን) ማደስ ማለት ነው::

ለማብራራት ያህል:—

በምርት ሂደቶች ውስጥ የሚሰራው ወይንም ከማሽን ጋር ቢዳረቅ የሚውለው ወዝአደር በምርት ሂደቶች ውስጥ ያጠፋውን ጉልበት እንደገና ለመጠገን (ለመመለስ) መመገብ፣ ማረፍና መተኛት አለበት:: የምርት መሣሪያዎችም በምርት ሂደት ውስጥ የሚበተሩት እንደገና ይጠሩ ዘንድ መታደስ መጠገን፣ የቴክኒክ መሸሻል መደረግ አለበት:: እንደዚሁም ለምርት የሚያገለግሉት ቀሬጥሬ ሀብቶች(ማእድን፣ የእርሻ ውጤት እነዚህን የመሳሰሉት)



በየጊዜው መተካት አለባቸው:: ካለበለዚያ ግን ማሽኑ ተሰብሮ ያኑሁ ካልታደሰ፣ ከበሬቶ የምርት ውጤት የተሸለ የቴክኒክ መሸሻል ካልተደረገ፣ ያለቀው ማእድን ያኑሁ በሌላ ካልተተካ እንደገና ማምረት አይቻልም ማለት ነው:: ይህ አጠቃላይ በምርት ሂደቶች ውስጥ ማምረትና እንደገና መመረት መኖሩን የሚያመለክት ነው::

ነገር ግን ይህንን ቲዎሪ ትንሽ አለፍ ብሎ መመልከት ያስፈልጋል:: ለምሳሌ በካፒታሊስት ስልተምርትም ሆነ በሶሻሊስት ሁለት ምርት የሚመረትባቸው ክፍሎች አሉ:: አንደኛው የምርት ማምረቻዎችን ማምረቻ ሲሆን ሁለተኛው ሰው ለእለት ተእለት ጥቅም የሚገለገልባቸው፣ የሚበላቸው ይህንን የመሳሰሉትን የሚመረትበት ክፍል ነው:: በነዚህ ሁለቱ የምርት ሴክተሮችም ሆነ በራሱ በመሣሪያ ማምረቻዎች በሚገኙት ዘርፎች የልውውጥ ግንኙነት አለ:: ይህም ማለት በአንዱ የመሣሪያ ማምረቻ ክፍል የሚመረተው በሌላኛው አይመረትም:: ስለዚህም በሁለቱ መሀከል የተሟላ የሥራ ቅንብር ይካሄድ ዘንድ በአንደኛው የተመረተው በሌላኛው የምርት ዘርፍ ውስጥ በምርት ሂደት ውስጥ እንዲገባ ይደረጋል::

በእርግጥ ማርክስ የካፒታሊስትን ስልተምርት ሲመረምር ይህ መሳልስ የማምረትን በኢንዱስትሪ ዘርፎች የሚደረገው ልውውጥ(ሪፕሮዳክሽን) በካፒታሊስት ምርት ውስጥ የኮሞዲቲ ቀጋ (ኮሞዲቲ ቫልዩ) ግንኙነትን ለማቀየትና ዝሬት(ኮሞዲቲ ሰርኩሌሽን) ያለውን ሚና ለማሳየት ነው::

ለምሳሌ ካፒታሊስቱ ያመረተውን ምርት(ኮሞዲቲ) በገበያ ላይ ሲያቀርብ በዚህ መልክ ይተመነዋል:: ለምርት መሣሪያዎች የወጣውን ካፒታል(ኮንስታንት ካፒታል)፣ ለጉልበት ሥራ ያወጣውን ካፒታል(ቫሪያብል ካፒታል)ና ተትርፍ(ስርፕለስ) በዚህ ሁኔታ እያውን ይሸጣል:: ካፒታሊስት በመሠረቱ ለከፍተኛ ትርፍ ነው የሚያመርተው ከዚህ ቀጥሎ መሳልስ በማምረት ትርፍን ለማካበት የኢንዱስትሪ መስኮችን ያስፋፋል:: ምርቱን ያባዶጋል:: እንደዚሁ ይቀጥላል::

ነገር ግን ማርክስ የምርትን ሂደት(ፕሮሴስ ኦፍ ፕሮዳክሽን) በምርት ማምረቻ መሣሪያዎች ክፍል1፣የምግብ ሌሎች የቀበቀስ ማምረቻ ክፍል 2 ከመረመረና በሁለቱ መሀከል የሚደረገውን ልውውጥ እንዲሁም በክፍል.1 የሚደረገውን የምርት መሣሪያዎች መሽከርከር በሰራው ካጨነ በኋላ ይህ ሂደት በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ውስጥም ተቀመጠ(ቫሊዲቲ)እንዳለው ሲያመለክት:—

> "If production were socialised instead of
> capitalistic, these products of department I
> would evidently just as regularly be redistributed
> as means of production to the various branches
> of this department, for purpose of reproduction."

## ስለ ኮሌክቲቭ አርሻዎች አንዳንድ ስህተቶች

የህብረት አርሻን በሚመለከት በኩል ሁለት ስህተተኛ ሃሳቦች ተሰነዘሩ:: አንደኛው የህብረት አርሻዎችን በመንግሥት ቁጥጥር (ናሽናላይዝድ) ማድረግ ሁለተኛው በህብረት አርሻዎች ላይ የተሰማሩትን የምርት መሣሪያዎች መሸጥ ነው የሚሉ ናቸው::

በሶሻሊስት ኢኮኖሚ ሥርአት ሁለት የኢኮኖሚ መስኮች ይኖራሉ:: አንደኛው የህዝብ ሲሆን ሁለተኛው የህብረት አርሻዎች ናቸው:: ምንም እንኳ በህብረት አርሻዎች ላይ የሚመረተው ምርት አምራቾች ገበያ አውጥቶ ቢሸጠውም (በመንግሥት በተተመነ ዋጋ) የምርት መሣሪያዎች የግል ባይሆን በመንግሥት ቁጥጥር ሥር ያሉ ናቸው:: በመሆኑም የህብረት አርሻዎች በይዞት (ኢን ኢሴንስ) የሶሻሊስት ኢኮኖሚ አውታር ስለሆኑ በዘፈቀደ እንደግል ሀብት ናሽናላይዝድ አይደረጉም:: ነገር ግን ይህ ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን ከሶሻሊስት ኢኮኖሚ እድገት ጋር እንዲሁም በገጠርና በከተማ፣ በጭንቅላትና በጉልበት ሥራ ያለው ልዩነት ቀስ በቀስ ሲወገድ፣ የምርት ልውውጥ (ፕሮዳክትስ—ኤክስቼንጅ) በታውን እንዲወስድ ይደረጋል:: ይህ ደግሞ የራሱ ዲያሌክቲካዊ እድገት ያለው እንጂ በማንኛውም ጊዜና ሁኔታ የሚደረግ አይደለም::

ሁለተኛው ስህተት ለካፒታሊዝም መንሰራራት ለሶሻሊዝም መዳከም በር የሚከፍት ፀረ—ሶሻሊስት ገምገማ ነው:: በኮሌክቲቭ አርሻ ላይ የተሠማሩትን የምርት መሣሪያዎች ከተሸጡና ግላዊ ይዞት እንዲኖራቸው ከተደረገ ካፒታሊዝም እንደገና እንዲመጣ እድል መስጠት ነው:: አያይዞም ኮሞዲቲ ፕሮዳክሽን እንዲኖር ማድረግና የምርት አናርኪ እንዲፈጠር ማድረግ ነው:: ሶሻሊዝምን መክዳትና ወዝአደሩ በቡርዣው እንዲተካ አመቺ ሁኔታ መፍጠር ነው::

በአውሮ፣ የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር
የጽሑት አዘጋጅ ቦርድ
The Ethio; on Students' Union in Europe
Editorial Board

## ማሳሰቢያ

ውድ አ ባቢያኖቻችን

የውጭን ገዥና ተ ከውስጥ ሆኖ በርበር ለማደከም ያደረገው ሙከራ ሰላሳ ት ዓለት አርባን ከገዥና ቱያችን ያገለለው ፀረ ሕዝብ ቡድን ከተርበ ጊዜ ጀምሮ፣ አስር ዓመት በላይ ሰፊው ሕዝብ ጉን በመሰለፍ ያለማቋረጥ ያለ ዕክት ፀረ ኢ ፔሪያሊስትና ፀረ ፊውዳሊስት ትግሉ ሲያካሄድ በኖረው ማህበራችንና በነ ዚህም ፡ ኀር ዓመታት ያስተባበረውን ነፃነት በመገጠት የሰፊውን ሕዝብ ድምፅና ትግሉ ሲያበ ተ ኑ በኖረት ፓክ የተናወም የተማሪ ማህበራት መድረክ በላይ የሰፊው ሕዝብ ማስ ተማ ያና መ ዘነ ተቫ ሆነው በቀጥተ በቱጠቅና በትገለቻን ስም መጠቀም ጀምረዋል፡፡ የዚህ ፡ ረ ሕዝብ ቡድን ዓላማ ማህበራችን እንደዚሁም ቱጠቅና ትገለቻን በ.1 4. ዓመት የሩቅ ገስ ባተረፈት ስም ተጠቅሞ ፀረ ሕዝብ ፖለቲካውን ለመሸፈን ነው፡፡እንዲሁም ከውስጥ ሆኖ ያታውን የኢት ዮጵ ያ ተገንጀዎችና ተራማጆች አንድነት የማፍለስ ሙከራ ከውጭ ፡ ና ወጀነገበር በመገዛት ለማፋፋም ነው፡፡ይህም እንደሚደብ የተረጋገጠ ነው፡፡ ለማገና፣ ዎች የተለመደው ጽሕፈት አዘጋጅ ቦርድ አድራሻ/ማለትም P.O.BOX 3198 1( )64 STOCKHOLM - SWEDEN ያለ ያዙ፣ የዓለም ዓቀፍ የኢት ዮጵ ያ ተማሪ ያ ማህበር አባለነትን የማይመለከተ ገገ የማህበራችን መጽ ሄቶች ስም የያዘ መጽ ሄተ ፡ ወዘተ በአውሮፓ የኢት ዮጵ ያ ተማሪያች ማህበር መጽ ሄቶች አለመሆናቸውን እንገለጽ ፡ ቀለንና እንድታስታውሱን እንጠይቃለን፡፡ለእነዚህ አይነተ መጽ ሄቶች ተጠያቂው ''ዓለ ፡ ዓቀፍ ፊዴሬሽን '' በሚባለ ስም የታወቀው የነ እስፋወሰን - መንገሻ ሥዩም የወጣቶ፣ ድርጅት ነው፡፡

ከፋፋዮችና አወናባጆች ከፊውዳሊዝምና ከኢምፔሪያሊዝም ጋር ይውደሙ!
የእውነተኛ አብዮታዊያንና ተራማጆች አንድነት ይኑር!
ድሉ የሰፊው ሕዝብ ነው!

በስኢተማ ጽሕፈት አዘጋጅ ቦርድ